የሚመከተው ጋሻ የሚጠጋበት ዋሻ የለውም
- ለችግር ደራሽ የለውም መጠጊያ የለውም

የሚመጣውን እንድታውቅ ያለፈውን ዕወቅ
- ሁሉም ነገር መሠረት ስላለው ያለፈውን ማወቁ ይጠቅማል

የሚሞት ልጅ አንገቱ ረጅም ነው
- ከሁኔታው ያስታውቃል

የሚሞት ሽማግሌ አይርገምህ የሚያልፍ ዝናብ አይምታህ
- የሚያልፍ ነገር ስለሆነ ተጠንቀቁ

የሚሮጡበት ሜዳ የሚወጡበት ቀዳዳ
- ከደረሰበት አደጋ የሚያመልጡበት መንገድ ያስፈልጋል

የሚሠራ ምንም አያጠራ
- ለወሬ ጊዜ የለውም

የሚስርቀው ያጣ ሌባ ስላማዊ መስሎ ይገባ
- የፈለጉትን ሲያጡ የጠሉትን ይቀላውጡ

የሚስት መናኛ የናት አገር ለማኝ
- ዞር ዞሮ ውርደቱ ያው ለባለቤቱ

የሚስት እምባሻ የጉረቤት ውሻ የደጅ እርሻ
- ንብረት በአግባቡ ካልተያዘ የሌላ መጠቀሚያ ይሆናል

የሚስት አሳቢ የጥድ በሬ ሳቢ ይስጥህ
- ትዳርህ ይባረክ ኑሮህ የደስታ ይሁን

የሚስት ወይዘሮ አርሻው ጋራ ዞሮ
- እመቤትነት ከሥራው ባሕርይ ጋር አልተጣጣሙም

የሚስት ዘመድ የማር እንጉቻ
- የሚስት ዘመዶች ለባሏ ጥሩ አስተሳሰብ የላቸውም

የሚሸሹበት አምባ ሲሸሽ ተገኘ
- ለችግር ጊዜ ይሆናል ብለው ያስቀመጡት ነገር ሳይገኝ ቀረ

የሚበላው ካጣ ይበላበት ያጣ
- ከተቸገረው ይልቅ ኖሮት አጠቃቀሙን ያላወቀው ይበልጥ ይጉዳል

የሚበጀውን ባለቤት ያውቃል
- ከባለቤቱ ያወቀ ቡዳ ነው

የሚከርመውም የማይከርመውም በአንድነት ዝናብ ይሰምናል
- የነገውን የሚያውቀው አንድዬ ብቻ ነው

የሚካኤል ስለት ለገብርኤል ምኑ ነው
- ለአንዱ የሚያስደስተው ለሌላ ሰው ትርጉም ላይሰጠው ይችላል

የሚከድ ሰው አደራ ሲያስቀምጡበት እጅ ይነሳል
- ጅብ ላይ ሥጋ አይጫንም

የሚወዱትን አቅፍ የሚጠሉትን ንቅፍ
- የሚወዱትን አቅፎ የሚጠሉትን ነቅፎ

የሚውል ሆድ ማለዳ ያረግዳል
- ሥራን ሳይጀምሩት ተስፋ መቁረጥ



የሚውል ሆድ ማለዳ ይርበዋል
- ስራን ሳይጀምሩት ተስፋ መቁረጥ

የሚዛንን አባይ ለአሳት የዳኛን አባይ ለሰንሰለት
- አጭበርባሪ ሰው መቅጣት

የሚያልቅ እህል ከማያልቅ ዘመድ ያጣላል
- የሚያልፍ ነገር የማያልፍ ስም ያስጣል

የሚያልፍ ቀን የማያልፈውን ስም ይወርሳል
- የገንቦ ጠላ ባልና ሚስት አጣላ

የሚያልፍ ነገር የማያልፍ ስም ይስጣል
- የገንቦ ጠላ ባልና ሚስት አጣላ

የሚያልፍ ውኃ አደረገኝ ድሃ አስች ልጅዋን ጉርፍ የወሰደባት
- ጊዜንና ቅዝምዝምን ጉንበስ ብለው ያሳልፉታል

የሚያልፍ ዝናብ አይምታህ የሚያድግ ልጅ አይጥላህ
- የሚሞት ሽማግሌ አይርገምህ የሚያልፍ ዝናብ አይምታህ

የሚያማ ጠበኛ ዘወር ይበል ክኛ
- ሐሜተኛ አጠገብህ ሆኖ አያማህም

የሚያስፈራውን ለሚነግርህ የሚያስቀዝነውን ንገረው
- ሳትሸበር የርስን ሽር አጢኑህ የባለ የሚያስፈራውን ንገረው

የሚያብረቀርቅ ሁሉ ወርቅ አይደለም
- ውጭውን አይተው መገመት አይቻልም

የሚያድግ ልጅ በእናቱ እጅ
- ያስእናት ያደገ ልጅ ጥሩ አይደለም

የሚያድግ ልጅ አትበድል የሚሞት ሽማግሌ አታታልል
- የሚያልፍ ውኃ አይውሰድህ የሚሞት ሽማግሌ አይርገምህ

የሚያድግ ልጅ አይጥላህ የሚሞት ሽማግሌ አይርገምህ
- ለሚያልፍ ነገር ታገስ

የሚያድግ ዛፍ በቁጥቋጦው ያስታውቃል
- የሚጠግብ እንጀራ በመሶቡ ያስታውቃል

የሚያጠግብ ቂጣ ከምጣዱ የሚወጣ ጥጃ ከገመዱ
- የሚያድግ ዛፍ በቁጥቋጦው ያስታወቃል

የሚያፈስ ቤት ጨቅጫቃ ሚስት
- ከቤት ያስወጣል

የሚዳቋ ብዛት ለውሻ ሠርግ ነው
- የአይጦች ዝላይ ስነውሮ ሲባይ

የሚዳቋ ግርግርታ ለውሻ ሠርግ ነው
- የአይጦች ዝላይ ስነውሮ ሲባይ

የሚጠጉበት ገደል የሚንጠለጠሉበት ቅጠል
- ምንም ምን በሌለበት አንዳችም ተስፋ በማይገኝበት ሁኔታ

የሚጣፍጥ ምግብ ሲርብ የበሉት ነው
- የምግብ ማጣፈጫው ረኃብ ነው

የሚጮህ ውሻ አይናከስም
- ጉልበቱን በጩኸት ጨርሶታል

የሚፈልግ ያገኛል የሚተኛ ያልማል
- የተጋና የጣረ ሰው የትጋቱንና የጥረቱን ውጤት ያገኛል

የሚፈርስ ከተማ ነጋሪት ቢመታ አይሰማ
- ዐውቆ የተኛ ቢቀሰቅሱት አይሰማም

የሚፈታ ከተማ ነጋሪት ቢመታ አይሰማ
- ዐውቆ የተኛ ቢቀሰቅሱት አይሰማም

የማሽላ ዘር ከነአገዳው ቸር
- ቅርንጫፉ አንደዛፉ

የማታ ማታ እውነት ይረታ
- እውነት ይቆይ እንጂ ይወጣል

የማታ ማታ ጭምት ይረታ
- ትዕግስት ያለው በመጨረሻ ያለበበት ይደርሳል

የማታ ምግብ ለእንግዳ የጧት መጠጥ ለዕዳ
- ጧት የሚጠጣ ልማደኛ ጠጪ በመሆኑ ከዕዳ አያመልጥም

የማታ ሩጫ እንቅፋት ነው ትርፉ
- ግልጽነት በጐደለው ነገር ላይ ለመሥራት መሞከር አጉል ድካም

የማታርፍ ጣት አር ጠንቁላ ወጣች
- መቅበዝበዝ ያልታሰበ ችግር ማስከተሉ አይቀርም

የማታ አፍ ከጋን ይሰፋል
- በስካር የተወራ ወሬ አያስተማምንም

የማታድግ ውርንጫ እናትዋን ትመራለች
- ምጥ ለእናቷ አስተማረች

የማትሔድ መበለት ዞራ ዞራ ትሰናበት
- ቆራጥ ውሳኔ ያልወሰነ ሰው ከሁኔታው ይታወቃል

የማትረባ ፍየል ዘጠኝ ትወልዳለች ልጆቿም ያልቃሉ እሷም ትሞታለች
- ከብዛት ጥራት ወሳኝ ነው

የማትሰማው ስድብ ከቀረርቶ ይቆጠራል
- ያላዩት አገር አያናፍቅም

የማትሸሸውን ባልንጀራ ዙረህ ዙረህ አትየው
- አንዴ የሆነው ሆኗልና አትጨነቅ

የማኅበር አሽከር በልቶም አይጠገን ታሞም አይድን
- የጋራ የሆነ ነገር ብዙ ጊዜ ትኩረት አያገኝም

የማነው እህል? ያለኝሃል ክምር የማነው ቤት? ያሰኝሃል አጥር
- እህል በክምር ቤት በአጥር ያምራል

የማን እርሻ ብለህ እረስ የማን ሚስት ብለህ ውረስ
- ዋናውን ወይም መነሻውን ጠይቀህ መረዳቱ ተገቢ ይሆናል

የማን ዘር ጐመን ዘር
- በቤተሰቡ ወጥቷል



የማን ገበሬ ሹርባ ይሠራል
- የትኛው ጊዜ ተገኝቶ

የማያመሽ ባል ቅንድብ ይሰማል
- ሥራ ጠፍቶ ጢስ ይሞቃል

የማያምኑበት ተዘግቶ ይታወቃል ተከፍቶ
- ማንኛውም ነገር ምንነቱ ሲገለጥ ምስጢሩ ይታወቃል

የማያስተኛ ነግረውት ሳይተኛ አደረ
- ያሰቡት አይገድም

የማያበላ ቢገላምጥ አያስደነግጥም
- ለማይጠቅምህ ሰው ቁብ የለህም

የማያበድር ደመኛ የማይመልስ ቀማኛ
- በልቶ ጠጥቶ ዝም የጋን ወንድም

የማያበድር ገዳይ የማይመልስ አባይ
- ውሽታም በተናገረበት አይገኝም

የማያዋጣ ባል ቅንድብ ይሰማል
- አገባሻለሁ ያለሽ ላያገባሽ ከባልሽ ሆድ አትባባሽ

የማያውቁት ስድብ ከዘፈን ይቆጠራል
- የማትሰማው ስድብ ከቀረርቶ ይቆጠራል

የማያውቁትን መሥራት ከጥቅሙ ጉዳቱ ይብስ
- ያለ ዕውቀት ያለ ሙያ የሚሠራ ሥራ ውጤት አልባ ነው

የማያውቁት አገር አይናፍቅም
- ያላዩትን ያላወቁትን አይመኙትም

የማያውቅ ምን ያውቅ
- ያላዋቂ ምን ይላል ያሉትን መልስ ይላል

የማያዛልቅ ጸሎት ለቅስፈት
- ከፍፃሜ የማያደርሉት ነገር ለአደጋ ይዳርጋል

የማያድሩበት ቤት አያመሻሹበት
- ጊዜን በከንቱ ማባከን አያስፈልግ

የማያድግ ልጅ ባራሱ ቤቱ ዳንኪራ ይመታል
- የማያዛልቅ ማኅበር በጠጅ ይጀምራል

የማያግዙ በፈር ያግዛሉ በከንፈር
- በገንዘብ በጉልበት ባያግዙም በማስተዛዘን ይረዳሉ

የሚያጠግብ እንጀራ ከምጣዱ ያስታውቃል
- የሚያድግ ዛፍ በቁጥቋጦው ያስታውቃል

የማያፍር እንግዳ ባለቤቱን ይጋብዛል
- በሰው ቤት አጉል ድፍረ

የማይሆን ነገር የተገላቢጦሽ ያንችን ላንቺ ማን አለሽ
- የአንዱ ለአንዱ የማይሆንበት ጊዜ አለ

የማይመለስ ማር ሹመኛ ይበደረዋል
- አንበሳ ምን ይበላል ተበድሮ ምን ይከፍላል ማን ተናግሮ

የማይመስል ነገር ለሚስትህ አትንገር
- የማይታመን ነገር አታውራ

የማይሙት ልጅ ሲቆጡት ያለቅሳል
- ሲጠባ ያደገ ጥጃ ሲይዙት ያጓራል

የማይሰማ ሰው ልቡን አፈረሰው
- ቢነግሩት የማይሰማ አብሮት ያለውን ሰው ያስቸግራል

የማይሠራ አይብላ የማይረዳ አይጥላ
- ሠርተህ ጥረህ ግረህ በላብህ ወዝ ብላ ተብሎ ተነግሯልና

የማይስማሙ ዝንቦች ጥንብ ይልሳሉ የሚስማሙ ማር ይጐርሳሉ
- ስምምነት ፈጥረው የሚኖሩ ሰዎች ይጠቀማሉ

የማይቀና ባይወልድ የማያስብ ባይነግድ ይሻላል
- መሻሻል የሚገኘው ጥሮ ግሮ በእቅድ በመመራት ነው

የማይበሉት እህል ከዐፈር እኩል ነው
- የኔነው የማይሉት ወርቅ ከብረት እኩል ነው

የማይበላ የሰም የማይጠግብ ባለ
- ማንኛውም ሰው ቢበላም የበላው ሁሉ ጠዝበ ማለት አይቻልም

የማይተማመን ባልንጀራ በየወንዙ ይማማላል
- ተጠራጣሪ ሰዎች እርስ በእርስ እምነት የላቸውም

የማይተች አይፈርድ የማያተርፍ አይነግድ
- ውጤት ለሌለው ነገር አትልፋ

የማይቻል ጠላት ስለወዳጅ ይቆጠራል
- የማትችለውን ጠላት አክብረህ መኖር አለብህ

የማይችሉት ድንጋይ ሲያወጡት ደረት ሲያወርዱት ጉልበት ይመታል
- የማይችሉትን ሥራ አለመሞከር ይመረጣል

የማይከፍል ባለዕዳ የሰጡትን ይቀበላል
- ብድርን እንደ ስጦታ ይቆጥረዋል

የማይዘልቅ ማኅበር በጠጅ ይጀምር
- የማያድግ ልጅ ባራስ ቤት ዳንኪራ ይመታል

የማይደርሱበትን አያኩም
- የማይቻል ነገር አይሞከርም

የማይድን በሽታ በጥር እሸት እምጡ ይላል
- የሌለውን በሌለበት ፍለጋ መሔድ

የማይድን በሽታ የማይመለስ ኃጢያተኛ
- በጀመረው የሚቀጥል የማይለቅ

የማይድን ባሕታዊ ወተት አምጡ የማይድን ፋቅራ ጠላ ስጡ
- ካሉበት ቦታና ሁኔታ አንፃር ሊስማሙ የማይችሉ ነገሮች

የማይገባ ሉሪ የማይበቅል ዘር
- ልክነና ሁኔታን መጠንን ያላገናዘበ

የማይገዙ በፈር ያግዛሉ በከንፈር
- በተግባር ቢቀርም በወሬ ማገዛቸው አልቀረም



የማይጠረጥር ቤቱን አያጥር
- በራስ የሚተማመን ጥበቃን አይሻም

የማይጣሱ መላዕክት የማይታረቁ አጋንንት
- በአጋንንት ዘንድ ሁልጊዜ ግጭት መኖሩን

የማይጽፍ ደብተራ ክንፍ የሌለው አሞራ
- ለተግባሩ አስፈላጊ የሆነው መሣሪያ መታጣት

የማይፈርስ ምሽግ የለም
- ሁሉም ፈራሽና ወዳቂ ነው

የማይፈነቀሰው ድንጋይ የለም
- የማይሞከረው ሙከራ የለም

የማይፈወስ ድውይ የማይመለስ ጊጉይ
- ከከፋቱ ከተንኮሉ የማይመለስ ሰው ሁልጊዜ እንደተጨነቀ ነው

የማይፈጭ ማስጣት ሰዶሮ ማስበላት
- ቆጥ ሳይሠሩ ዶሮ

የሜዳ ንስንሱን የቤት ጉስጉሱን
- ከቤት ውጪ አምሮ መታየትና በቤት ውስጥ የተገላቢጦሽ መሆን

የምላስ ጦር ቢታከም አይድንም
- የዱላ ቁስል ሲድን የክፉ ንግግር ቁስል ምንጊዜም አይድንም

የምሮጥበት ሜዳ የምወጣበት ቀዳዳ የለም
- በዚህም በዚያም ምንም ማምለጫ የለኝም

የምስራች በቃሏ ወጣች
- የምስራች በቃሏ መላች

የምስጢረኛ ምላስ የለውም
- ምስጢረኛ ሰው አይናገርም

የምበላው ሳጣ ልጄ ጥርስ አወጣ
- እኔውም የምበላው አጥቻለሁ ሌላ በላተኛ ደግሞ መጣብኝ

የምበላው እህል ከሚታየው መሬት ይበቅላል
- አንድ ነገር ከየት እንደሚነሳ ማወቅ አትችልም

የምትመክተው ጋሻና የምትለወርበት ዋሻ
- ከክፉ ነገር መደበቂያ ወይም መሰወሪያ አዘጋጅ

የምትታጠቀው የሌላት የምትከናነበው አማራት
- መሠረታዊ ነገር የሌላት ሌላ ተመኘች

የምትነቃነቅ ግንድና የምትሥቅ ሴት ልብ ሩቅ ነው
- ሣቅ የደስታ ምልክት ነውና ብሩህ ቀን ይመጣል በማለት ታስባለች

የምትኮነን ነፍስ ጉረቤት ያውቃል
- ከጉረቤት የሚሰወር ነገር የለም

የምትጠላው ሰው ፈስ ሆዱ ውስጥ ሳለ ይሸታል
- የጠሉት ሰው ምኑም አያምርም

የምትጠላውን የምትወደውን ለጥተህ ሸኘው
- በረቀቀ ዘዴ ከአጠገብህ አርቀው

የምትጠባ ጥጃ አትጮህም
- የፈለገውን ያገኘ ሰው ምንም ተቃውሞ አያደርግም

የምኞችን ፈረስ ልጓም አይገታውም
- የሰው ምኞት ሰፊ ነው

የምድሩን በአፍ የሰማዩን በመጣፍ
- በቅርብ ያገኘነውን እየተመገብን በመጽሐፍ በተደነገገው ሥርዓት መሠረት ለሰማዩ አባታችን እንጸልያለን

የምጣዱ እያየለ የእንቅቡ ተንጣጣ
- የተጐዳው እያለ የማያገባው ቡራ ከረዩ አለ

የምጥ መድኃኒቱ አንድ እግር ማስቀደም ነው
- ሁሉ ነገር የሚሠራው በዘዴ ነው

የሞላስት ድመት ሣንባ ያማርጣል
- የደላው ሙቅ ያላምጣል

የሞተ ልጅ አንገቱ ረጅም ነው
- ሲያዩት አጅግ ያሳዝናል

የሞተ ቢሞት ያለን እንጫወት
- ከሞተው ጋር አብሮ አይሞትም

የሞተ አይከሰስ የፈሰሰ አይታፈስ
- አንዴ የሆነ ነገር ሲመለስ አይችልም

የሞተውን አያ ይሰዋል
- ያለፈውን ብትጠራው ወይም አይልህም

የሞተው ወንድምሽ የገደለው ባልሽ ኃዘንሽ ቅጥ አጣ ከቤትሽም አልወጣ
- የተቆረጠው እጅሽ የቆረጠው እጅሽ እንግዲህ ምን ይበጅሽ

የሞተ ያልነበረ ይመስላል ያለ የማይሞት ይመስላል
- ሞት ቢዘገይ የቀረ ይመስላል

የሞት በደለኛ አይያዝ በዳኛ
- ሞትን የሚዳኝ ዳኛ የለም

የሞኝ ለቅሶ መልሶ መላልሶ
- ሞኝ ነገር መደጋገም ይወዳል

የሞኝ መንገዱ አንድ ነው
- አማራጭን ያለመጠቀም ከሞኝነት ያስቆጥራል

የሞኝ ሚስት በምልክት
- ሞኝ ካልሆነ ምልክት ሊሸወድ ይችላል

የሞኝ ምስጋና የግንቦት ደመና
- ሞኝ ካመሰገነህ በኋላ መልሶ ይነቅፍሃል

የሞኝን ቂጥ ዶሮ ይጠቀጥቀዋል
- የሞኝን ገንዘብ ማንም ይበላዋል

የሞኝ በትር ሆድ ይቀትር
- ሞኝ ሲማታ ቦታ አይመርጥም

የሞኝን ጠላ በሰው ባንኮላ
- የሞኝ ንብረት ማንም ነው የሚጠቀምበት



የሞኝን ጥርስ ብርድ ፈጀው
- በሆነ ባልሆነው በመሣቁ ጉዳት ደረሰበት

የሞኝ አሳሳሌ ለዘመድ አይሰጥም
- ይሉኝታ ዘመድ እንዲበደል ያደርጋል

የሞኝ እጁን ሁለት ጊዜ ነክሰው አንድ ጊዜ ሳያይ ሁለተኛው ሲያሳይ
- ካለፈው ስሕተት የማይማር ሰው ለተጨማሪ አደጋ ይጋለጣል

የሞኝ ዘመድ ያፍራል
- ሞኝ ማፈሪያ ነው

የሞኝ ዘፈን ሁለጊዜ አበባዬ
- ሁልጊዜ አይለወጥም አይሻሻልም

የሞኝ ጀርባ ሲመታ ለዐዋቂ ይስማማል
- ሞኝነት ወይም ድንቁርና ሲጠፋ ዐዋቂ ደስ ይለዋል

የሞኝ ገበሬ አርሻ በሰኔ
- ወቅቱን ጠብቆ አንድን ሥራ አስመሥራት

የሠራው ቢረሳ የተሠራው አይረሳ
- ወርቁ ቢጠፋ ሚዛኑ አልጠፋ

የሣር ክምር የጭሰኛ ክብር
- የሣር ክምር ትንሽ እሳት እንደምትበላው ሁሉ የጭሰኛ ክብርም ይህን ያህል አይደለም

የሥራ ቅሌት ያስለምዳል ሌብነት
- ለአንድ ሠራተኛ ሌብነት ከፍተኛ ቅሌቱ ነው

የሥንዴ ንፍሮ ያተር ድብልቅ፤ከዚያችው ወጥተው አዚያችው ጥልቅ
- እርስ በርሱ የተደበላለቀ የተቀየጠ

የሥንዴ አራራ የሴት መራራ
- የሴትን መራራ ማንም እንደማይፈልጋት ነው

የሥንዴ አራራ የቆንጆ መራራ
- መልክ ታጥቦ አይጠጣም

የሥጋ ልል ጭቅና፤ ያመትባል ትልቅ ገና
- ከዓመት በዓል ትልቁ ገና ነው

የሥጋ መድኃኒት ላም፤ የነፍስ መድኃኒት ማሪያም
- ማሪያም አማላጅ ናት

የሥጋ መጨረሻ አጥንት፤ የነፍስ መጨረሻ ግዝት
- አታድርግ የተባልከውን አለማድረግ ግዝትን መስማትና መቀበል ነው

የሥጋ መጨረሻ አጥንት፤ የነፍስ መጨረሻው የእግዛብሔር መንግሥት
- ከሞት በኋላ ሕይወትን ያመነ ነፍስ የምትኖረው በመንግሥተ ለማያት ነው

የሥጋ ቁራጭ፤ የብርሌ ጭላጭ
- ትንሽ ሥጋ እንደ መርፌ ትወጋ

የሥጋ ትል የዘመድ ጥል
- ከዘመድ ጋር ቂም አትያያዝ

የሥጋዬ ቁራጭ የአጥንቴ ፍላጭ

- ከአብራክ የተገኘ ልጅ

የረከሰ አይጠደድ የመነነ አይለደድ

- መናኝ እንዴ መንኖ ገዳም በመግባቱ ማንም የሚያሳድደው የለም

የረዘመውን በጥፍር ያጠረውን በድግር

- በሚያመች መንገድ ሁሉ አስፈላጊውን እርምጃ መውሰድ

የረገመ የተረገመ

- ረጋሚ ደርጋሚ
- የሚራገም እራሱ የተረገመ ነው

የረጋ ወተት ቅቤ ይወጣዋል

- እርጋታ ለሁሉም ነገር ጠቃሚ ነው

የሩቁን የሚመለከት የፊቱን ያፈሳል

- ሩቅ አሳቢ ቅርብ አዳሪ

የራሱን ትቶ የሰው አክባሪ የበላበትን ወጪት ሰባሪ

- የራሱን ጥሎ የሰው አንጠልጥሎ

የራሱን እንዳይበላ ገንዘብ የለው የሰው እንዳይበላ ዓመል የለው

- ምንም የሌለው ደሃ ሆኖ በዚህ ላይ ደግሞ ጸባይ የለውም

የራሱን ጥሎ የሰው አንጠልጥሎ

- የራሱን ትቶ የሰው አክባሪ

የራስን ሳያውቁ ለሰው አይጨነቁ

- በሌላው ላይ አስተያየት ለመስጠት ከመነሳሳት በፊት ራስ በትክክል ማወቅ ያስፈልጋል

የራስ ጌጥ ስለ ጨርቅ የሌለው ያስጨንቅ

- የአደራ ገንዘብ ያስጨንቃል

የራሷ ቢያርባት የሰው ታማስላለች

- የራስን ሳያውቁ ለሰው ይጨነቁ

የራሷን አበሳ በሰው ላይ እብሳ

- የራሷን ጥፋት በሌላ ሰው ለጠፈች

የራሷን ዐታውቅ የለው ትንቅ

- አመድ በዱቄት ይሥቃል

የራበውን ገበያ አታውጣው

- ፍላጐት ሲበረከት ችግር መጋበዙ አይቀሬ ነው

የራበው ይጠግብ አይመስለው

- ለዚሁ ነው በሬዬን ያረድኩት እለ እለ /ገበሬ ርቦት በሬውን አርዶ/

የለሰጠነ ለየጠነ

- ሥልጣኔ የሰይጣን ሥራ ነው

የሰማዩ ንጉሥ እስኪረዳኝ የመሬቱ ንጉሥ ይጉዳ

- ከሩቅ ያለ የበላይ እስኪወሰን በቅርብ ያለ የቅርብ አለቃ ብዙ ይጉዳ

የሰማዩን ያህል እንጀራ ይስጥህ ብለው የኮከቡን ያህል በሳተኛ እለበ፥ እለው

- ሀብት ሲበረከት የዚያኑ ያህል ችግር ሳያስከትል አይቀርም



የሰማይ ርቀቱን የምድር ስፋቱንን የፀሐይ ድምቀቱን

- ያህል እንደምን አለሽ /አለህ/ ጥንታዊ የሰላምታ ደብዳቤ መግቢያ ነበር

የሰማ ይሰማ ያልሰማ ይግማማ

- ካልሰማህ የራስህ ጉዳይ

የሰባን እርዶ የጠራን አውርዶ

- የቀረበን የተመቻቸን ነገር ጠጋ ብሎ እንደሚሆን ማድረግ ነው

የሰነፍ ምላሰኛ የበሽተኛ በላተኛ

- ሥራ በወሬ ሳይሆን በተግባር ነው መሆን ያለበት

የሰነፍ አበላል ይበረድልኝ የሰነፍ ምክር ይማልልኝ

- ደካማ ሰው ሌላው ቀርቶ በሚመገበው ምግብ እንኳ ብርታት ያጣል

የሰከረ አወዳደቁ አያምር

- ራሱን የማይቆጣጠር ሰው አደጋ ያጋጥመዋል

የሰከረ ይተፋል የገደለ ይደነፋል

- ሰካራም እንደሚያስመልስ ሁሳ ገዳይም በሠራው ሥራ መፎከሩ አይቀርም

የሰው ሆዱ የወፍ ወንዱን የሚያውቅ የለም

- ሰው ካልተናገረ በስተቀር ምን እንዳሰበ አይታወቅም

የሰው ልጅ መከራው እንጀራው ያልቅና ወጡ ይተርፍና

- አንድ ሰው ከአንድ ቤተሰብ ጋ ሲኖር እህል ውኃው ካለቀ እሱ መኖር ቢፈለግ እንኳ የተደመደመ ጉዳይ ይሆናል

የሰው ልጅ በምን ይታፈራል? በወንበር አይደለም በወንበር በከንፈር

- ከሁሉም በላይ የሚያስከብረው ሥልጣን ሳይሆን ከአንደበትህ የሚወጣው ንግግር ነው

የሰው ልጅ  ቢወልድ ሎሌውን ባሰጌ ቢወልድ ጌታውን

- የጨዋ ልጅ ሁልጊዜ ጨዋ ነው

የሰው ልጅ ከማሳደግ የውሻ ልጅ ማሳደግ

- ውሻ ጊዜ አይቶ የማይከዳ የጌታው ጽኑ ወዳጅ ነው

የሰው ልጅ ካለአገሩ ጉራዴ ካለለፋ

- የሰው ልጅ በአገሩ እንጂ ከአገሩ ውጪ ክብር የለውም

የሰው መሠረቱ እናትና አባቱ

- ልጅን ኮትኩቶ ለማሳደግ እናትና አባት ወሳኝ ናቸው

የሰው መዋደጃው በየምድጃው

- የቀድሞ መኳንንት ከሠራተኞቻቸው ጋር በየምድጃው ስለሚባልጉ ነው

የሰው ማስጠንቀቂያ የመዝጊያ ማጥበቂያ

- አንዱን በደንብ አድርገው ከቀጡት ለሌላው ትምህርት ይሆናል

የሰው ምላስ መንታ አንዱ ለሙገሳ አንዱ ለሐሜታ

- ሰው እንደሁኔታው የወደደውን ሲያሞግስ የጠላውን ሲያማ ይውላል

የሰው ሞኝ አንድ ዕንጨት ያስራል

- ውጤት በሌለው ሥራ ላይ ጊዜን ያባክናል

የሰው ሞኝ የአባቱን ሀብት ያወራል
- የቤተሰብ ሀብትን ከማውራት ራስ ሠርቶ ማግኘት

የሰው ሥጋ ቢጠብሱት ያራል ቢበሱት ይመራል
- ሠርተው ለፍተው ያላገኙ የሰው ገንዘብ ብዙ ትርጉም አይሰጥም

የሰው ቀሳል እራሱ ይቀሳል የልብስ ቀሳል ባለቤቱን ያቀሳል
- ባለጌ በራሱ ድርጊት ይቀሳል

የሰው ቀሳል እራሱ ይቀሳል የልብስ ቀሳል ለባሹን ያቀሳል
- የምትሠራው ሥራ ወይ ያስከብርሃል ወይ ያዋርድሃል

የሰው ቁስል አይነዝርም
- የሰው ችግር እንደራስ ችግር አይታይም

የሰው ቃሪያ እስቲሞት ድረስ አይበስልም
- በተፈጥሮው ቢመክሩት የማይሰማ ሰው ዕድሜ ልኩን አይሻሻልም

የሰው በልቶ አያድሩም ተኝቶ
- ደሞዝተኛ አርፈህ አትተኛ

የሰው ባሕርይ ሳይደርሱ የድንጋይ ሥር ሳይምሱ
- ሰው ካልደረሰክበት ባህርዩ ምን ዓይነት እንደሆነ ልታውቅ አትችልም

የሰው ቤት ሲቀጠቅ ቋያ ይመስሳል
- በራስ ላይ ያልደረሰ ችግር ችግር መስሎ አይታይም

የሰው ብልሃቱ ለፈጣሪ መንገር ነው መድኃኒቱ
- የሰው ብድር አይቀርም በምድር

የሰው ታናሽ ያደርጋል ታናሽ
- ትንሽ ሰው ትንሽ ነው አንሶ ያሳንሳል

የሰው ታናሽ ይገዛል በግማሽ
- የሰውን ልክ የማያውቅ ሰው ሰውን ዝቅ አድርጐ ይመለከታል

የሰው ታናሽ ይጥሳል ጭራሽ
- ትንሽ ሰው ሰውን ያዋርዳል

የሰው ነገር አለመናገር
- ሰውን ማመን ቀብሮ ነው አለች ቀበሮ

የሰውን በአህያ የራስን በጉያ
- ሰው የሰውን ጠባይ በይፋ ያወራዋል የራሱን በጉያው ይደብቀዋል

የሰውን ነገር ስንቱን ልናገር
- ሰው በሰው ላይ የሚሠራው ስንትና ስንት ክፉ ነገር አለ

የሰውን አባት የሚሰድብ አባቱን ያሰደብ
- የሰው አባት የሚሰደብ አባቱን የጠላ ነው

የሰው ዓመሉ ዳውላ ሙሉ መች ያስታውቃል አብረው ታልኖሩ
- አብረው ካልኖሩ የሰው ባሕሪ አይታወቅም

የሰው አባቱ ሽማ የሽማ አባቱ ጥለቱ
- ሽማ ወይም ልብስ ሰውን ያስከብራል

የሰው አትበይ ምግባር የለሽ የራስሽን አትበይ ገንዘብ የለሽ
- ምንም የሌላት ድሃ ሆና በዚህ ላይ ደግሞ ጸባይ የላትም



የሰው አገሩ ምግባሩ
- ሥነምግባር ያለው ሰው ከሰው ተስማምቶ መኖር ይችላል

የሰው አገር ዝናብና የእንጀራ አባት አይምታህ
- የእንጀራ አባት ባልተወለደ አንጀቱ ከመታህ ይጐዳሃልና ተጠንቀቅ

የሰው ዕርስት ከማልማት አይሻልም ወይ ያባት
- ለሌላ ከማገልገል ለራስ መልፋት ይሻላል

የሰው እጅ የግዜር ደጅ
- የሰውን እጅ ከመጠበቅ ከግዜር ደጅ መጠበቁ ይበልጣል

የሰው እንግዳ ያገር ባዳ
- የሰው አገር ሰው

የሰው ከማየት የራስን መብላት
- ከመመቅኘት ሠርቶ ማግኘት

የሰው ከርፋፋ ሲሰድቡት አይከፋው
- ክፋውንና ደጉን ለይቶ የማያውቅ

የሰው ኩራቱ በናትና ባባቱ
- አባት ሳለአጊጥ ጀንበር ካለሩጥ

የሰው ክብረቱ ያሰኘዋል እንቱ
- ሠርተው ደክመው ያገኙት ሀብት ያስከብራል

የሰው ክፉ ዋሾ የዕጽ ክፉ አብሾ
- አብሾ ሰውን የሚያሳብድ ዕጽ በመሆኑ ከርሱም ከውሸታምም መራቅ

የሰው ክፉ ጠማማ ነው አፉ
- ነገርን ወደ መጥፎ ሁኔታ እያጣመመ የሚተረጉም

የሰው ወርቅ አያደምቅ
- የወርቅ ጥርስ ቢሥቁበት አያደምቅ ቢያንኙበት አያደቅ

የሰው ግብሩ አይለየው እስከ መቃብሩ
- ተፈጥሮን ተመክሮ አይመልሰውም

የሰው ግብር ቢመለከቱት ደሃ ይከናል ባመቱ
- የሰውን ክፉ ሥራ ላይ ከማተኮር በርትቶ መሥራት ይበጃል

የሰው ጠላቱ ይወጣል ከቤቱ
- ጠላት ከሩቅ አይመጣም

የሰው ፈላጊ የራሱን ያጣል ዓሣ ጉርጓሪ ዘንዶ ያወጣል
- አተርፍ ባይ አጉዳይ

የሰው ፊት አይቆረስ የሰው ገንዘብ አይወረስ
- የሰው ቢመኙ ላያገኙ

የሰው ፊት የሚያፍር በቅሉ አይቀመጥ
- በይሉኝታ ብዙ ቤት ተፈታ

የሰው ፊት ደግነቱ አለመፋጀቱ
- የሰው ፊት ነበልባል ቢሆን ኖሮ ስንቱ ተለብልቦ አልቆ ነበር

የሰይጣንን አመጣጥ አማያውቅ አይመነኩስ
- የነገሮችን አመጣጥና አካሔድ የማያውቅ ሰው ችግር ያጋጥመዋል

የሰይጣን ክፋቱ ያለመታየቱ
- የሚደርሱብንን ችግሮች አስቀድመን ለማወቅ አንችልም

የሰይጣን ገንዘብ የተበደረ ሳይበላው ተቀበረ
- ከክፉ ሰው ጋር የተዋዋለ መከራው ብዙ ነው

የሰዳጅ ለወዳጅ
- ለብርቱ ወዳጅ መልካም ነገር የሚሰድ

የስጋ ቤቱን ዘጋ የዘነጋ ተወጋ
- ለሥጋው ሳይሆን ለነፍሱ አደረ ይህን ማድረግ የተሳነው መከራ ይጠብቀዋል

የሰጠ ቢነሳ የሰበት ወቀሳ
- በገዛ ሀብቱ በገዛ ንብረቱ ቢሰጥ ቢከለክል ማንያዘዋል

የሰጠኸኝ ሽማ ከደጅህ ተቀማ
- ነጣቂዎች እዚሁ ደጅህ ላይ የሰጡኸኝን ሽማ ነጠቁኝ

የሰጡህን ተቀበል ያደረጉልህን ቻል አትበል
- ውለታን አትዘንጋ

የሰጡህን አትንሳ ያደረጉልህን አትርሳ
- ምንጊዜም የሰው ውለታ ሊዘነጋ አይገባም

የሰጡን ይለጧል የገዙን ይነዷል
- አንድ ሰው በራሱ ሀብት አዛዡ እሱ ራሱ ነው

የሰጡን ይለጧል ያጠቡን ያለጧል
- ሰው ለሰው የፈለገውን ያህል ወይም መጠን ሊሰጥ ይችላል

የሳተ ይምክርህ የዋለ ይንገርህ
- ልምድ ካለው ተማር

የሴት ልቧ እንጂ ሆዷ አይመርጥም
- ያገኘችውን የቀረባትን ሁሉ ትወዳለች

የሴት መልኳ ምንድነው? እጇን ታጥባ እንክ ስትል ነው
- የሴት ባለሙያነት እንጂ መልክ ብቻ ዋጋ የለውም

የሴት መጠጥ ደፋር የወንድ ዓይን አፋር
- የሴት ጠጪና የወንድ ቅልስልቅ ለትዳር አይሆኑም

የሴት ምክር የሾህ አጥር
- የሴት ምክር ጥሩ ነው

የሴት ሞቷ በማጀቷ
- ትዳር ያላት ሴት ቤቷን ትወዳለች

የሴት ረዥም የማቅ ውዥምዥም አጅግ አያስጐመጅም
- ረዥም ሴት አትስብም

የሴት ስካር ያጭር ሰው ኩራት አይታይም
- የዳመና ውኃ ጥምና የእናት ክፍት አይታወቅም

የሴት ቀበጥ የበቅሎ መድን ለመሆን ገበያ ትወጣለች
- የሴት ወበራ ትታጠቃለች ካራ

የሴት በራ የበቅሎ ደንባራ /ቦራ/
- ፀጉር የሌላት ሴት አትስብም



የሴት ብቻዋን ሒያጅ የቁስ አርፍጅ ሁለቱም ነገር ወዳጅ
- ሴት ብቻዋን ከሔደች ትደፈራለች ለማለት

የሴት አመዳም የአሮጌ ሆዳም
- አመዳም ሴት ቅባትም ብትቀባ አትወዛም

የሴት አመዳም ያህያ ሆዳም
- አመዳም ሴት ቅባትም ብትቀባ አትወዛም

የሴት አገሯ
- ቤቷና ትዳሯ

የሴት አገሯ ባሏ ማደሪያዋ ዓመሏ
- ዓመል ያላት ሴት ባሏ ያከብራታል

የሴት አጭር ወይዘሮ የወንድ አጭር አውራ ዶሮ
- ወንድ ዘለግ ሲል ይወደዳል

የሴት እንግዳ የመርፌ ጐዳ
- ሴትም መርፌም በደረሱበት ያገለግላሉ

የሴት ከርፋፋ ዕቃውን በዕቃ ደጋግፋ አንዱን ስታነሳ ሁሉም ይደፋ
- የተንከረፈፈች ሴት ሥራዋን በደንብ አትሠራም

የሴት ክፉ ምላሰኛ የበሽታ ክፉ መጋኛ
- ምላሰኛ ሴት ለትዳር አትመችም

የሴት ክፉ አፈኛ የጐረቤት ክፉ ምቀኛ
- የጐረቤት ምቀኛ ጥሩ አይደለም

የሴት ወበራ /ቀበጥ/ ትታጠቃለች ካራ
- እዩኝ እዩኝ ማለት ደብቁኝ ደብቁኝ ማለትን ያስከትላል

የሴት ዘበናይ የፊቷን እንጂ የኋላዋን አታይ
- በሬ ሆይ ሣሩን አየህና ገደሉን ሳታይ ገብተህ ቀረህ ወይ

የሴት ዘንገኛ የናት ምቀኛ
- የናት ምቀኛ ከቶውንም አስቸጋሪ ናት

የሴት ዶሮ ኩኩሉ ለባለጌ ኩሩ
- አለሁ አለሁ የምትል ነገር ግን ከባለጌ ጋር የማትውል

የሴት ጉልበቷ ምላሷ
- ሴትን በስድብ የሚያክላት የለም

የሴት ጠጪ የግመል ፈንጪ
- የሴት ጠጪን የሚወዳት የለም

የስራት መቋሚያው ፍጥምጥም የሥጋ መቆሚያው ቅልጥም
- የጠቡ መነሻ የቆየ ጉዳይ ነው

የስሱ ልጅ ስሱ መደቆሻ ሲልስ ተሰበረ ጥርሱ
- አተርፍ ባይ አጉዳይ

የሰብሰቱ እርሻ የጠቡ መነሻ
- ላለመግባባት መሠረት የሆነው አንድ ነገር ነው

የስድብ እበጥ የለውም
- የስድብ ጥሩ የለውም

የስድብ ክፉ አባት የበትር ክፉ እናት
- በበትር እናት ከተመቱ አደገኛ ነው
የስጦታ ፈረስ ጥርሱ አይታይም
- የስጡህን ሳታመነታ እመስግነህ ተቀበል
የሷ ጊዜ ተንሰቀሰቀች የሰው ጊዜ ሣቀች
- በሰው ቁስል ዕንጨት ስደድበት
የሻማ ጥቅል የወርቅ እንክብል
- ጥሩ ሀብት ይሰጥህ ምርቃት
የሽምበቆ በትር ቢመረኮዙት ይሰበራል ቢመቱበት እጅ ያቆስላል
- የጉሎ ዘንግ ብትር አይሆንም
የሽንኍ ዓይን ጉልበትን ይሰብራል
- የሰው ዐይን እርጥብ ያደርቃል
የሹም ሰነፍ አንዱን ሳይጨርስ አንዱን ይወዝፍ
- ሰነፍ ሰው የሚጨርሰውን ሥራ ለነገ እያለ ያስተላልፋል
የሹም ሰነፍ ይለፈልፍ
- ድክመቱን በመጮህ ሊሸፍን ይጮሃል
የሹም ክርፋፋ አገር ያጠፋ የእህያ ጀላፋ መስክ ያጠፋ
- የአሰቃ ልል በጥፊ ያወላውል
የሹም ጦር እቅፍ ሙሉ
- የፈሪ ዱላ ዘጠኝ ነው
የሹክሹክታ ግቢ ለፍች ያስቸግራል ገርጋሪ በቅሎ ይደነብራል
- በድብቅ የተደረገ ነገር ሁሉ በኋላ ለፈራጅ ያስቸግራል
የሺህ ሞት ሠርግ ነው ያንድ ሞት ጉዳት ነው
- የአንድ ጠቃሚ ዋና ሰው ሞት ኅብረተሰቡን ይጐዳል
የሺህ ቃል ንቁፍ የዋና ቃል ጽሑፍ
- ነፋስ ከነፈስ ንጉሥ ከተነፈስ
የሺህ አባላት መሰብሰቢያው እናት
- ከሺህ ውስጥ የሚመረጡ መሪዎች እሱ
የሺህ ፍልጥ ማሰሪያው ልጥ
- ድር ቢያብር አንበሳ ያስር
የሺ ገንዘብ ብላ ከሺ ወንድም አትጣላ
- የጋራ የሆነ ገንዘብ ብዙ ተቆርቋሪ የለውም የሺ ወንድም ግን ተቆርቋሪ አለው
የሺ ገንዘብ ተቀበል የሺ ወንድሙን አትግደል
- ብዙ ወገን ያለውን ሰው አትንካ
የሺ ገንዘብ ብላ ወንድሙን አትንካ
- ወንድም ያለውን አትንካ ከነካህ ተበቃይ ይኖረዋል
የሻፈደች እርግብ መሬት ወርዳ ዶሮ ይደፍራታል
- ክብሩን ያልጠበቀ ሰላማዊ ሰው ማንም ያዋርደዋል
የሽሮ ድንፋታ እንጀራ እስኪመጣ
- ዝንብ ቢሰበሰብ መግላሊት አይከፍትም



የሽሮ ፉከራ ከምጣዱ እስኪወጣ እንጀራ
- ተልባ ቢንጫጫ ባንድ ሙቀጫ
የሽንኩርት ሌባ አታላይነቱ ልሸተት ማሰቱ
- የሌባ ዐይነ ደረቅ መልሶ ልብ ያድርቅ
የሽኮኮ ዳቦ ለመስበኪያ ቀጭን ሽማ ለማረግረጊያ
- ተስማሚ የሥራ መሣሪያ ለተስማሚ ሥራ
የሽኮኮ ጸሎት
- የማይዘልቅ ጸሎት
የሾተላይ ልጅ የገበታ ውኃ ይወስደዋል
- ብርቅ የሆነ ነገር ተጻራሪው ብዙ ነው
የቀማኝ የሰው ልጅ የበቅሎ የሰው ልጅ
- ንጥቂያውን የፈፀመብኝ የሰው ልጅ ነው
የቀበረ ተቀበረ
- ምስጢሩን የደበቀ በዚያው ቀረ
የቀበሮ ባሕታዊ ከበጐች መሃል ይጸልያል
- አስመሳይ ሰው
የቀበጠች አይጥ የድመት አፍንጫ ታሸታለች
- የቀበጡ ዕለት ሞት አይገኝም
የቀበጡ ዕለት ሞት አይገኝም
- አይጥ ለሞቷ የድመት አፍንጫ ታሸታለች
የቀበጡ ዕለት አይገኝም ሞት
- ካልቀበጡ አይዘሉ ካልዘለሉ አይሰበሩ
የቀባጣሪ አፍ ጠማማ ነው
- ቀባጣሪ ነገሮች እንደፈለገው አጣምሞ ያወራል
የቀና ሲታጣ ይመስመሳል ጐባጣ
- ዋርካ በሌለበት እምቧጮ አድባር ይሆናል
የቀን ጨዋታ አይገኝም ማታ
- ጊዜ በአግባቡ ተጠቀምበት ያለበለዚያ ጊዜ ተመልሶ እንደማይመጣ ዕወቅ
የቀደመ ያገሳል ደግሞ ደግሞ ያጐርሳል
- አተርፍ ባይ አጉዳይ
የቀድሞ እርበኛ የቅምጥ ይዋጋል
- ልምድ አለኝ ባይ
የቀድሞ ወዳጅህን በምን ቀረብከው በሻሽ የኋለኛው እንዳይሸሽ
- ወዳጅን እንደዓመሉ መያዝ ሌላ ወዳጅ እንዳይርቅ ይጠቅማል
የቀጂ ልጅ ጠጪ
- ከእህያ የዋለች ጊደር ፈስ ተስተምራ ትመጣለች
የቁራ መልዕክተኛ
- ተልኮ በጣም የሚቆይ
የቁጥር መጨረሻ ዝም
- ዝም አይነቅዝም

የቂል በትር ሆድ ይቀትር
- ቂል ልክንና መጠንን መገመት አይችልም

የቂል ጓደኛው ቂል
- ግም ለግም አብረህ አዝግም

የቂጣ እንደሁ ይጠፋል የማርገገሮ እንደሁ ይገፋል
- እውነትና ንጋት እያደር ይታያል

የቄስ ልጅ ባገባ በሜሮን ፈትፍቼ እበላ ነበር አለ
- አንድም ከደግ ተወለድ አንድም ከደግ ተጠጋ

የቄስ ሚስት ዐወቅሽ ቢሏት መጣፍ አጠበች
- ብዙ ሙገሳ ለስሕተት ይዳርጋል

የቄስ ምንዳኛ የሴት በትረኛ
- የሴት በትረኛ በራሷ ላይ ችግር ትጋብዛለች

የቄስ ሞገደኛ የሴት በትረኛ አያድርስ ከኛ
- ቄስ የሕዝብ አስተማሪ ሆኖ ሳለ ሞገደኛ ከሆነ ለሕዝቡ አይጠቅምም

የቄስ ቀማኛ የዳኛ ምቀኛ
- አያድርስ ነው

የቄስ ቃል አንድ ይበቃል
- ቄስ ያለው ይለማል

የቄስ ነጋዴ ይሆናል ወንበዴ
- ዓለማዊ ሥራ የሚሠራ ነጋዴ የጽድቅ ሥራ አይሠራም

የቄስ ነጋዴ ይመስላል ወንበዴ
- ከዓለማዊ ኑሮ ጋር የተዋሃደ ቄስ አጨበርባሪ ነው

የቄስ አባይ የደበሎ ተባይ
- የቄስ ዋሾ ኅብረተሰቡን ያጠፋል

የቅማል ስደት ከራስ ወርዶ አንገት
- ዕውር ቢሸፍት ከጓሮ

የቅርቡን በደጅ የሩቁን ባዋጅ
- በሕግና በደንብ መሥራት ተቀባይነት አለው

የቅርብ አራሽ በእንቅብ አፋሽ
- ወደማሰሮና ወደ እናት የተጠጋ አንድ ነው /የገንፎ ማዕረግ/

የቅርብ አዝመራ ለጤና
- አዲስ ሹም ብዙ አይተናኮልም

የቅርብ ጠበል የልጥ መንከሪያ ይሆናል
- በቅርቡ ያለ መድኃኒት አይንከባከቡትም

የቆለኛ ምስክር ከጥይት ይፈጥናል
- ቆለኛ ተኩሶ አይስትም

የቆመ ሌባ የተቀመጠውን ይቀማል
- ሁኔታውና ጊዜው ያመቸው የማያደርገው የለም

የቆመው እግር ቢሆን አሳቢው ራስ ነው
- ሁሉንም የሚመራው ዋናው አንጎል ነው



የቆረጠ አመለጠ
- ቆሎ መወሰን እንጂ ማመንታት አጉል ነው

የቆቅ ለማዳ የካይላ አንግዳ ከቤት ሲሉት ወደ ሜዳ
- ሁሉ እንደጠባይ እንደባሕርዩ እንደለመደው ነው

የቆቅ አውራ ይውላል ተራራ
- አውራ ሰው ውሎው አደባባይ ነው

የቆዳ ጓንታ ለውሻ ሠርጉ ነው
- የሁኔታዎች ግርግርታ ለሌላ ሰው ምቹ ሁኔታ ይፈጥርለታል

የቆጡን ስታይ የብብቷን ጣለች
- ጥሩ ነገር ስትመለከት የራሷን ጥሩ ነገር አጣች

የቆጡን አወርድ ብላ የብብቷን ጣለች
- አተርፍ ባይ አጉዳይ

የበላ በለጠኝ የሮጠ አመለጠኝ
- ያገኘውን የማይበላ የሚጠየፍ ሰው ቀስ በቀስ አካሉ እየደከመ ይሔዳል

የበላ ቢያብል ገላው ይናገር
- ግመል ሰርቆ አጐንብሶ

የበላበትን ወጪት ሰባሪ
- ውለታ ቢስ

የበላች ብትዘፍን ያበላች ታዝን
- የሌላዋን ንብረት በመውሰዷ

የበላችው ያገሳታል በላይ በላይ ያጐርሳታል
- ቢቃኝን አለማወቅ አልጠግብ ባይ

የበላን ሆድ የወጋ ከንድ ያውቃል
- አፍ የሚጐርሰውን እጅ ይመጥናል

የበላውን ያብላላዋል የለበሰውን ይበርደዋል
- ያለበት ይጉላላበት

የበላይ አዳባይ
- ትንሹ ለትልቁ የሚበጅ ነገር መፈጸም

የበላ ዳኛ የወጋ መጋኛ
- ጉቦ የበላ ዳኛ ለሰጠው መፍረዱ አይቀሬ ነው

የበረታ ከራሱ የሰነፈ ከዋሱ
- ብርናትና በራስ መተማመን ካለ በራስ ለራስ የሚበጅ ተግባር ይፈጸማል

የበረደውን አሙቆ የረጠበውን አድርቆ
- ሁኔታዎች ምቹ አድርጐ ማዘጋጀት

የበሬ ሆዳም ቢሞት አይጐዳም
- ብዙም የሚጠቅም ባለመሆኑ ቢሔድም ጉዳቱ ይህን ያህል ነው

የበሬም ዋይ ይውላል ገበያ ሥጋው ለመብል ቆዳው ለጠፍር
- ክብት በሕይወቱም ያገለግላል ሲሞትም የሚጣል የለውም

የበሬ ሳቢ የቤት አሳቢ ይስጥህ
- ኑሮህ የተሳካ ይሁን

የበሬ ሻኛማ የላም ግታም
- የተስተካከለ ሀብት ይስጥህ

የበሬ ቀንዱን የወይራ ግንዱን
- ጠንካራና የማይደፈር

የበሬን ምስጋና አህያ ወሰደችው
- የሠራ እያለ ያልሠራ ተመሰገነ

የበሬ ዕቃ እየራሱ አለቃ
- ሁሉም በራሱ ራሱን የቻለ

የበሬ ዳተኛ እመሀል ይተኛ
- ልግመኛ ሰው እየሠራህ እያለህ ችግር ይፈጥራል

የበሬ ዳተኛ የሴት ምላለኛ አታምጣ ወደኛ
- ችግር የሚፈጥር ሰው ወደኛ እንዲቀርብ አንፈልግም

የበሬ ዶለኛ የሴት ምላሰኛ አያድርስ ወደኛ
- ነገረኛን አርቅልን

የበለለ ይበላል ጥሬ በምጣድ ይቆላል
- እንደአመቺነቱ ተግባር ላይ ማዋል

የበሰበሰ ዝናብ አይፈራም
- የለየለት ምን አለበት

የበሶ አቁማዳ ተፈቶ የሴባ አፍ ነጥቶ
- ሌባ ተይዞ ዱላው አይጠየቅም

የበሶ አቁማዳ ተፈቶ የተሸካሚው አፍ ነጥቶ ይመስላል
- በአደባባይ የተሠራ ወንጀል መሸሸግ አይቻልም

የበሽታ ክፉ ቁርጥማት የኃጢያት ክፉ ቅናት
- ከመቅናት ሠርቶ ማግኘት

የበሽታ ክፉ እህል ያስወድዳል
- በችግር ላይ ችግር ሲደራረብ

የበቅሎ ዕቃ እየራሱ አስቃ
- ሁሉም በራሱ ራሱን የቻለ መሆኑ

የበቅሎ ክባድ የሐር ገመድ
- በእውኑ ዓለም የበቅሎ ከበድን ለማግኘት ያስቸግራል

የበደለ ይከሳል የቀማ ይመልሳል
- እውነት ተናግሮ የመሸመበት ያድራል

የቡና ስባቱ መፋጀቱ
- ቡናና ፍቅር በትኩሱ ነው

የቡና ቀዝቃዛ የሹም ፈዛዛ
- አይጥምም አይፈለግም

የባህር ዳር ሲታረስ ጓንንቸር ሆድ ይብሳታል
- ትርፍ የሚለጥ የሚያስገኝ ነገር ሲበላሽ ያናድዳል

የባለሥር ምላሱ አሥር
- ወገንና ዘመድ ያለው ያሻውን ይናገራል



የባስቤት ለነፍ ቤቱን ያዋርዳል
- የቤቱ ውርደት የሱ መሆኑን ያለማወቅ ያለማጤን

የባለቤት አዳይ ጦም ያሳድራል
- የነገውን አለማሰብና አለማስተዋል

የባሰቤት ዕውር ዕቃውን ያነሳል
- የማያስተውል ሰው የማይጐዳውን እንደሚጐዳ አድርጐ ይወስደዋል

የባለጌ ኃይማኖት ከዥማት ይከራል
- አዲስ አማኝ ኃይማኖት አጥባቂ ነው

የባለጌ ልጅ መብል ያፍር ነገር ይደፍር
- ሥራ ከመሥራት ይልቅ ነገር ማመላለስ ይወዳል

የባለጌ ልጅ መንገድ ይፈጃል ከነገር ይጃጃል
- የነገርን ብልት የማያውቅ ሰው በቀላሉ ይሞኛል

የባለጌ ልጅ መንገድ ይፈጅ ነገር አይፈጅ
- የነገርን አካሔድ የማያውቅ በክርክር ወይም በሙግት አይረታም

የባለጌ ልጅ እያደር ይተኛል የጨዋ ልጅ እያደር ይበጃል
- ባለጌ ዕድሜም አያስተምረውም ጨዋ ግን ዕድሜ እያስተማረው ይሔዳል

የባለጌ ባለሟል ቂጥ ገልቦ ያያል
- ባስጌ አጸያፊ ተግባር ይፈጽማል

የባለጌ ባሰሟል ካፍ አትለዩኝ ይላል
- ሞኝ ሰው ከወንድምህ እኩል አድርገኝ ይላል

የባለጌ ተለጣጭ ከድንጋይ ላይ ተቀማጭ
- ቂጥ ገልቦ ተከናንቦ

የባለጌ ኃይለ ቃል እንደሸመል ይወቃል
- የሞኝ በትር ሆድ ይቀትር

የባለጌ ኩራቱ እንዲያው ነው በከንቱ
- ቢከፍቱት ተልባ

የባላባት ልጅ ሲሠራልህ ነው ያሉት እንደሆን ከስቶ ያድራል
- ስጋት እሰበት

የባላገር ሥልጡን እሰው ፊት ይቆርሳል
- ዐወቅሽ አወቅሽ ቢሏት መጣፍ አጠበች

የባላገር ሥልጡን እጅ ይዞ ያጫውታል
- ያልሆኑትን መስሎ ለመታየት

የባላገር እንግዳ ሞት የባልቴት ሳዱላ መሬት
- የባልቴት ሳዱላ የማይሆንና የማይታመን

የባላገር ዱለት ይፈታል በኩበት
- በኩበት የተጠበሰ ዱለት ሽታው ጠረኑ አያስበላም

የባልቴት ወበራ የክረምት ብራ
- የማይሆን እንዳንዴ ግን የሚያጋጥም

የባል ዘመድ ባይኑ አመድ
- የባል ዘመድ በሚስቱ ይጠላል

የባል ዘመድ እጻርቻ ሲከስም ቆይ ብቻ
- የባል ዘመድ በዓይኑ አመድ

የባበ አለ ሚስትህን አትፍታ
- በእጅ የያዝከውን አትልቀቅ የሚመጣው አይታወቅም

የባሰ አለ አገርህን አትልቀቀ
- የባሰ አለ ሚስትህን አትፍታ

የባብ ለማዳ ያህያ ፍሪዳ የሰውም
- ምን ቢቸግር ሊሆን የማይችል

የባብ ልጅ በቅን ብቻ ሰንቅ በሰልቻ
- የማይሆንና የማይታመን ስንቅ በአገልግል ሊያዝ ይችላል

የባብና የሴት ፍለጋ ማነው የሚያወጋ
- ብዙ የሚያደክም ሰወሬም አይመች

የባብ ዱካ ሆነ
- ፈጽሞ ሊገኝ አልቻለም

የባዳ ሞኝ ከልጅህ እኩል አርገኝ ይላል
- የባለጌ ባለሟል ካፍ አትለዩኝ ይላል

የባዕድ ሞኝ ከዘመድህ እኩል አርገኝ ይላል
- የዘመድ ሞኝ ከልጅህ እኩል አርገኝ ይላል

የባዕድ ፍቅር የውኃ ጌጥ አንድ ነው
- የባዕድ ፍቅር ከጥቅም ጋር ነው የሚሔደው ጥቅሙ ከቀረበት ፍቅሩም አለቀ

የቤቴ መቃጠል ለትኋኑ በጀኝ
- ችግሩ ባንድ በኩል ሲጐዳኝ በአንድ በኩል ጠቅሞኛል

የቤት ቀጋ የሜዳ አልጋ
- ጥሩ መስሎ አተሳ ፍሬ መበሎ ገለባ

የቤት ቀጋ የውጭ አልጋ
- ጥሩ መስሎ አተሳ ፍሬ መስሎ ገለባ

የቤት ቤት አለው ማጀት የሆድ ሆድ አለው አንጀት
- ሁሉም እንደአቅሙ የሚኖረው ይኖረዋል

የቤት ዓመል ገበያ ያወጣል
- እቤት የሚያስቸግር ሰው በውጭም ያበቸግራል

የቤት ጥጋብ አለ ሰንቅ ያዘምታል
- አጉል ጥጋብ ለችግር ይዳርጋል

የብልጥ ዓይን አስቀድሞ ያለቅሳል
- አስመሳይ ነው

የብረት ቆሎ የድንጋይ ንፍሮ
- የማይሆን የማይደፈር

የብራ ዳጥ
- የማይታወቅበት መሰሪ

የብርቱካን ውኃውን የሽማግሌ ምክሩን
- የሽማግሌን ምክር ስማ



የብትር ትሕትና ያበመታል የነገር ትሕትና ያስረታል
- ነገርን በአንክሮ መከታተል ተገቢ ነው

የብዙ ሕዋሳት መበብሰቢያው አናት
- የሺ ፍልጥ ማሰሪያው ልጥ

የብዙ ኪሎ ሜትሮች መንገድ በአንድ እርምጃ ይጀመራል
- ከፍተኛ ቦታ የሚደረሰው ከትንሽ ተነስተህ ነው

የብድር ሽሮ ምን ሲል ተጀምሮ
- እንዲህ ዓይነቱ ከመጀመሪያውም መታሰብ የሌለበት

የቧልተኛ ሎሌ ላይለለፍ ያረጃል
- ዱባና ቅል አበቃቀሉ ለየቅል

የተለፋን ቆዳ ሳልተለፋ መለወጥ ትርፉ ዘጥ ዘጥ
- ያለቀለትን ጥሩ ነገር መለወጥ ለመልፋት ነው

የተላከ በአፉ ለከከ
- እሺ ከሺ ይበልጣል

የተሳጠ ዕንጨት ዳግም አይሳጥም ሰው አለ አንድ ጊዜ አይበለጥም
- ሰው የአንድ ጊዜ ስሕተት ስሁስተኛው እንዳይሳሳት ይረዳዋል

የተልባ ስፍር የሕልም እንጀራ
- በአንድ ቦታ የማይረጋ

የተመረረ ድሃ ይገባል ከውኃ
- ኑሮ የመረረው ራሱን ያጠፋል

የተመረቀ ከሰይጣን የራቀ
- ከከፉ ሥራዎች መራቅ አለብህ

የተመሰከረ ይፈርዳል የሰባ ይታረዳል
- ያለው አይቀር

የተመታ ዳነ ደም የተፈናጠቀበት ሞተ
- የምጣዱ እያለ የእንቅቡ ተንጣጣ

የተመቸው ገንፎ ያሳምጣል
- የደላው ሙቅ ያኝካል

የተመኘ አገኘ
- የምኞቱ ሆነለት

የተማማሉ ማለኛ የተጋደሉ ጠበኛ
- የማይተማመን ጓደኛ በየወንዙ ይማማላል

የተማረ መልካም ጥቃት አያስነካም
- የተማረ ለዘመዶቹ ጥቃትን ይከላከላል

የተማረ ነፍሱን የመረመረ
- የተማረ ከፉና ደጉን ይረዳል

የተማረ ክብሩን የመረመረ
- የተማረ ክብሩን የሚያስነካ ድፍረት አይፈጽምም

የተማረ የተሟረ
- መማር አንዳንዴ ለጉዳት ለችግር የሚዳርግበት ጊዜ አለ

የተማረ ጋፍ መልከ ያጋፍፍ
- ዐዋቂ ነኝ ባይ መልካምን ሊሽ ይኖራል

የተማከሩት ዳኛ ያግዛል የመተሩበት እጅ ይወዛል
- የተማከሩበት ነገር ጥሩ ነው

የተሟጋች ሚስቱ ባጋች
- ባልና ሚስት ከአንድ ምንጭ ነው የተቀዱት

የተረገዘ በሆድ የታዘለ በሰምድ
- የሚያውቁትን በጥንቃቄ በዘዴና በስልት መያዝ

የተራበ አይዘፍንም የጠገበ አያርፍም
- ካልጠገቡ አይዘሉ ካልዘለሉ አይለበሩ

የተራበ ከባቄላ የተበደለ ከሰቀላ
- እያንዳንዱ እንደችግሩ ዓይነት መፍትሔ መሻት ይኖርበታል

የተሳለ ብረት አንገትን ከደረት ሥጋን ከጅማት ይለያል
- እውነት ወይም ሐሰት እውነተኛውንና ሐሰተኛውን ይለያል

የተሸሸገ ምግብ ሆድ አይጠፋለትም
- ንብረትና ገንዘብ ፈላጊ ወሳጅ አያጣም

የተሸሸገ ምግብ የተሸሸገ ሆድ አያጣም
- የተሸሸገ ንብረትና ገንዘብን ያልታወቀ ሰው ሊጠቀልለው ይችላል

የተሸከመው ከብዶታል አንደገና ይጨመርበታል
- በላይ በላዩ ያጉርሳታል የበላችው ያገሳታል

የተሾመ ወደ ግምጃ የተሻረ ወደ ሙጃ
- ሲሾም ያልበላ ሲሻር ይቆጨዋል

የተሾመን ይሟገቱበታል የተሻረን ይመሰክሩበታል
- ለሒያጅ የሰው ወዳጅ

የተቀመጠ ማርና ልጃገረድ የሚሆኑት አያጡም
- ክብሩን ጠብቆ የቆየ በመጨረሻ ላይ ጥሩ ደረጃ ይደርሳል

የተቀማጭ ምላሱ ይላጭ
- የሚሠሩትን መተቸት ቀላል ነው

የተቀማጭ አፉ ምላጭ
- የሚሠሩትን መንቀፍ ቀላል ነው

የተቆለፈ ወርቅ ያልተቆለፈ ጨርቅ
- ትኩረት ይበዛበታል

የተበደለ ከነጋሽ የተጠማ ከፈሳሽ
- ሁሉም ወደሚመለከተው ቦታ ይሔዳል

የተራበ ገመዴ የተቆፈረ ጉድጓዴ
- ያረፈ ያፈጀ ለሞት የተቃረበ

የተነቃነቀ ጥርስ ሳይወልቅ አይቀርም
- የተጀመረ ነገር ማለቁ አይቀርም

የተናቀ መንድር ባህያ ይወረራል
- ባለቤቱን ካልናቁ አጥሩን አይነቀንቁ



የተናካሽን ውሻ የጅብ መቋደሻ
- ከዚያም ከዚያም ጋር የሚጋጭ ሠራተኛ ዐይንህ ላፈር ይሉታል

የተናገሩት ከሚጠፋ የወለዱት ይጥፋ
- ቃልህን አክብር

የተኛውን አንበሳ አስነሳችው ላም ልሳ
- አቅምን ዐውቆ መኖር

የተከፋ ተደፋ
- የሚበሳጭ ሰው ራሱን ነው የሚጐዳው

የተወለዱት ይራባሉ እንደገና ይወለዳሉ
- በችግር ላይ ችግር መጨመር

የተዘጋ ተጠበቀ ያልተዘጋ ተሰረቀ
- ግዴለሽ ሰው ችግር ላይ ይወድቃል

የተደረገ ተደርጐ እንዳስመሰማት በጐ የሰም
- ያልሰሙት ነገር አይቆጭም

የተገኘ ጥበብ ከዶሮና ከንብ
- ለፍቶና ጥሮ ለሕይወት የሚበጅ ነገር መሥራት

የተገዘተች ነፍስ የተለጐመች ፈረስ
- ከወዲያ ወዲህ መላወስ ያልተቻላት

የተጠማ ከፈሳሽ የተጠቃ ከነጋሽ
- ሁሉም ወደሚመለከተው ቦታ ይሔዳል

የተጠራጠሩበት ድንጋይ ይጥሉበት
- ጥርጣሬ ጥሩ ነው

የተጠገነ እጅ እንደቀድሞው አይሆንም
- ተበላሽቶ የተሠራ ነገር እንደአዲስነቱ አይሆንም

የተጣደፈን ቅቤ ያንቀዋል
- ችኰላ ለአደጋ ያጋልጣል

የተጻፈ ይወረሳል በቃል ያለ ይረሳል
- በጽሑፍ የሰፈረ ነገር ጥሩ ነው

የተፈተለ ከሁለት የተታታ ከሦስት
- ከአቅም በላይ ለማድረግ የሚሞክር

የተፈተለ ይለበሳል የተጀመረ ይጨረሳል
- የተጀመረ ነገር ማለቁ አይቀርም

የተፈጠመ አይናገር አንካሳ አይሻገር
- ያለቀለት ነገር መሻሻል አይችልም

የተፈጠመ ያርፋል የተኛ ያኮርፋል
- አንድ ሰው ቃል ከገባ በኋላ ቃሉን ማክበር ይገባል

የተፋትን ነገር መልሰው ቢውጡት ተራራ ያክላል
- ወደ መጥፎ ዓመልህ ከተመለስክበት ከፋቱ የባሰ ነው

የታለህ ያላሉት አዚህ አለሁ ይላል
- ሳይጠሩት አቤት

የታመመውን ሙት ጠየቀው
- ወደዚያው ወደማይቀሩበት መንዝ

የታመነ ሎሌ ጠጅ የሞላበት ብርሌ
- በሰው ላይ ተአማኝነት ካለህ ያስደስታል

የታቀፈችው እናቲቱ የሚላጨው አባቱ
- በእንክብካቤ ሕፃናትን ማሳደግ

የታነቀ የልቡን ቢናገር የሚያምነው የለም
- ሳይሆን እንጂ ከሆነ ወዲያማ ማን ሊሰማ

የታናሽ ልጅ አሳናሽ የዘንጋዳ ወጥ አህል አበላሽ
- ባሰኔ የሰውን ክብር ያስደፍራል

የታደለ ተደላደለ
- ዕድለኛ የተመቻቸ ኑሮ ይኖራል

የታደለች ሴት በፊት ትወልዳለች ሴት
- ሴት ልጅ እናቷን ስለምትረዳ የመጀመሪያ ልጅ ሴት ቢሆን ይመረጣል

የትሕትና በትር ያስመታል የትሕትና ሙግት ያስረታል
- የነብርን ጅራት አይዙም ከያዙም አይለቁም ጠንክር ማለት ይበጃል

የት ላይ ተቀምጠሽ እግዜርን ታሚያለሽ
- ያለሽበትን በትክክል ያልተረዳሽ ነሽ

የትምህርት ሙግት አንድ ተናግሮ ጉልት
- በቂ ያልሆነ ዕውቀት

የትም ተከስስ አሰቃህ ድረስ
- ለውሳኔውም ቢሆን ምንነትህ በግልጽ የምታሳውቅበት ቦታ ይሻላል

የትም ተወለድ እንክብር እደግ
- ልዩ ሙያ ልዩ ባሕርይ ለማዳበር ሊባል

የትም ፍጪው ዱቄቱን እምጪው
- የሚፈለገው ነገር ከየትም ቢሆን መምጣት አለበት

የት ትሔዳለህ? እሑዳዳቸው ምን ያሮጥሃል? ውቃቢያቸው
- የበላን ያብላላዋል ያሯሩጠዋል

የትንሽ ሰው ፍቅር መቀምቀሚያው ጥቁር
- ከስድ አደግ መጋባት መጨረሻው አያምርም

የት ዐውቅሽ ብሎ አጥብቆ ሳመኝ
- በስሕተት የተፈፀመ ተግባር

የትዕቢት መድኀኒት ጭንቀት
- እዩኝ እዩኝ ማለት ደብቁኝ ደብቁኝ ማለትን ያስከትላል

የትውልድ ጉልበቱ ኀብረቱ የሕዝብ ሀብቱ አንድነቱ
- መተባበር ኃይል ነው

የቸኮለ እፍሶ ለቀመ
- የቸኮለ ሰው ዘግይቶ ነው የሚደርሰው

የቸገረው እርጉዝ ያገባል የባለበት እመጫት ያገባል
- አማራጭ ያጣ ሰው ማድረግ የሌለበትን ነገር ያደርጋል



የቸገረው ዱቄት ከነፋስ ይጠጋል
- የቸገረው እርጉዝ ያገባል

የችግር ክፉ እህል ማጣት የኃጢያት ክፉ ነፍስ ማጥፋት
- የሰውን ሕይወት እንደማጥፋት ያለ ከባድ ወንጀል የለም

የኃጢያት ክፉ ጉቦ የበሽታ ክፉ ተስቦ
- ጉቦ በእግዚአብሔርም የማይወደድ ሥራ ነው

የኃጥእን ዳፋ ጻድቁን እዳፋ
- የአንዱ ጦስ ለሌላው ጦስ ሆነ

የኂላ ኂላ አይቀርም ዱላ
- ይቺ ባቁላ ያደረች እንደሆን አትቀረጠምም

የነሐሴ ውኃ ጥሩ ነው የሚጠጣው የለም የድሃ ነገር ፍሬ ነው የሚሰማው የለም
- ለድሃ ትኩረት የሚሰጠው የለም

የነቂሎ ቤት ግርግዳው ስንበሌጥ
- የቸኮለች አፍሳ ለቀመች

የነበረ ይናገር ያየ ይመስክር
- ምስክር ሊሆን የሚችለው ያየና የሰማ ብቻ ነው

የነበረ ገብርኤል ተወገረ
- ወንጀል የፈጸመ ፍርዱን አገኘ

የነብር ልጅ አይታቀፍ የጨዋ ልጅ አይነቀፍ
- የጨዋን ልጅ ምንም ስለማያጠፋ አይነቀፍም

የነብር ዓይን ከፍየል የፍየል ዓይን ከቅጠል
- ማንኛውም ነገር ትኩረት የሚሰጠው የሚፈለገው ነገር ላይ ነው

የነብር ጅራት አይዙም ከያዙም አይለቁም
- አስቸጋሪ ነገር አይሞክሩ

የነ ቶሎ ቶሎ ቤት ግርግዳው ስንበሌጥ
- በጥድፊያ የተሠራ ነገር አይረባም

የነገሩ ሁነኛ የጦር አርበኛ
- አርበኝነት ከትውልድ የሚጠበቅ ነው

የነገሩትን የማይረሳ የለመኑትን የማይነሳ እግዜርን አትርሳ
- ዓምላክ የለመኑትን ስለማይነሳ እግዜርን ልታስበው ይገባል

የነገር ትሕትና ያስረታል የብትር ትሕትና ያስመታል
- ነገርን ስአንክሮ መከታተል ተገቢ ነው

የነገር ወጡ መደመጡ
- ነገርን በጥሞና ካላዳመጥከው መረዳት አትችልም

የነገር ጠማማ በሽማግሌ ይታረቃል
- ከባድ የሆነን ጸብ እንኳን በሽማግሌ መፈታቱ አይቀርም

የነገር ጠማማ ያስከትላል ሳማ
- ጥፋት ማጥፋት ቅጣት ያስከትላል

የነገር ጣዕሙ ዝግታ ያዋቂ ጣዕሙ ዝምታ
- በዝግታ የሚቀርብ ነገር ተደማጭነት አለው

የነገር ጣዕም በጆሮ የእህል ጣዕም በጉሮሮ

- ለሁሉም አስፈላጊ የሥራ መሣሪያ ይጠቅማል

የነገን ነገ ይፍረደው

- ለነገ እግዚአብሔር አለ

የነገደ አተረፈ ያለፈ ተራገፈ

- የሠራ የልፋቱን የጥረቱን ያገኛል

የነጋሪት በቅሎ ከላይሽ ማን ወርዶ

- ነጋሪቱ ተጐስሞ እስኪያልቅ ነጋሪት ጐሳሚው ከበቅሎዋ ላይ አይወርድም

የነፍሰ ገዳይ ምልክቱ ደም በጣቱ

- ክፉ ሠሪ ክፋቱ የሚገለጥበት ባሕርይ ነው

የነፍስ ትቶ የገብስ

- ሰው የዕለት የዕለቱን ያስባል

የኑሮ ክፉ ደባል የመንገድ ክፉ በደል

- የደባል ኑሮ አስከፊ ነው

የኑሮ ገለባ እያገርህ ግባ

- ያልተሟላ ኑሮ ጥፋልኝ ዘንድሮ

የናት ሆድ ዥንጉርጉር እንደ ነብር ወገር

- አንዱ መልካም አንዱ ክፉ

የናት ሆድ ዥንጉርጉር ወላጅ ቀይና ጥቁር

- ከአንድ እናት የሚወለዱ ሁሉም አንድ ዓይነት አይሆኑም

የናት ልመና ፊት አያስመልስ አንገት አያስቀልስ ሲሆን በውድ አስበለዚያ በግድ

- የእናትን ልመና ማንም ረግጦ አያልፍም

የናት ልጅ ቢጣላ እውነት ይመስላል

- እህያ ላህያ ቢራገጥ ጥርስ አይሳበር

የናት ልጅ የሌለው አይበላ ጆሮ የሌለው ምንቸት አይፈላ

- አንድ አንጀት ተንተርሰው የተወለዱ አይጨካከኑም

የናት ልጅ የጉን እጅ

- አለኝታና ረዳት ነው

የእናት ሞትና የእግር እሳት እያደር ያንገበግባል

- የእናት ሞት እየቆየ ይሰማል

የናት ሞትና የድንጋይ መቀመጫ እያደር ይቆረቁራል

- የናት ሞት እያደረ ይሰማል

የናትን ክፋት የደመናን ውኃ ጥማት ባለቤቱ ያውቃል

- ሌላው ማንም ይሆናል ብሎ አይገምትም

የኔነህ በለኝ ደስ እንዲለኝ

- በጣም እወድሃለሁ

የኔ ነው የማይል የሞተ የራሱን የማይተው የሞተ

- ለእራሱ የማይሆንና ንብረቱን የማይጠብቅ ሰው አይረባም

የኔን ችግር ለማን ልንገር

- ችግሬን ለማን ሳዋየው



የኔን ወጥ በቀመስሽው ያንቺን በደፋሽው

- የኔን ብትቀምሽ ኖሮ ያንቺ ጥሩ አለመሆኑን ትገነዘቢ ነበር

የንጉሥ ቃል አነሰ ብሎ አይጨመር በዛ ብሎ አይቀነስ

- ንጉሡ ከተናገሩት ነገር ላይ መጨመርም መቀነስም አይቻልም

የንጉሥ አሽከር ስሙ ወርቅ ልብሱ ጨርቅ

- ክብሩ በጣም ከፍተኛ ነው

የንጉሥ እድር እናት አያስቀብር

- ማን ላይ ቆመሽ ማንን ታሚያለሽ

የንጉሥ ግንቡን የሹም ልቡን

- ማንም ሊያውቅ ሊደፍር አይችልም

የንጨት ምንቸት ራሱን አያድን ሰው አያድን

- ለራሱ አይሆን ለሌላው አይሆን

የንጨት ክፉ አባሎ የዳኛ ክፉ መድሎ

- አድልዎን ሕዝብ ፈጽሞ አይወድም

የንጨት ወልጋዳ የመንገድ አንጋዳ

- የማያውቁት ሄደውበት የማያውቁት መንገድ ያስቸግራል

የንፉግ ለጋስ የሰጠውን ይመልስ

- ያለባሕርዩ የሚደረግ ነገር ዘለቄታ የለውም

የንፉግ ገንዘብ በለጋስ እጅ የጠላት ገንዘብ በወዳጅ

- ገንዘብ ባይኖርህም የጠላትህን ገንዘብ በወዳጅህ በኩል ታገኛለህ

የንፍጣም ነገሩ አይጥም

- ልክስክስ ሰው ሥራው ሁሉ ደስ አይልም

የአልኮል ፍቅር እስከ መቃብር

- የአልኮል ሱሰ መጥፎ ነው

የአረፋውን ሲሏት የጀጀባውን

- የሰው ምክር የማትሰማ የቀኙን ሲሏት የግራውን ያሰኛታል

የእርበኛ ልጅ ይወጋል የአሮጌ ልጅ ያወጋል

- ወንድ ልጅ ተወልዶ ካልሆነ እንደአባቱ ስጡት አመልማሎ ይፍተል እንደእናቱ

የእሥር እናት ጅብ በላት

- ብዙ ዘመድ እያላት ሳይደርሱላት አደጋ ደረሰባት ወይም ገጠማት

የእሽኮኮ ዳቦ ለመስበኪያ ቀጭን ሽማ ለማረግረጊያ

- ለተወሰነ ተግባር ተስማሚ የሆነ የሥራ መሣሪያ ያስፈልጋል

የእቡነ ዘበሰማያት ጦር ሲወጋ እንጂ አይታይም ሲወረወር

- ጸሎት ሰይጣንን የሚያሸንፈው ሰይጣን ያደረበት ሰው ሲጮህ ነው

የአባይ ልጅ ወዳቂ የዘማ ልጅ ሣቂ

- ተማሪ ማንን ይመስላል ቢሉ መምህሩን

የአተር ክምር የጢስኛ ክብር

- የማይረባ ዋጋ የሌለው

የአንበሳ ልጅ ሲሞት ቀበር አንበሳ ሲሞት እቤት ዋል

- የሀብታም ልጅ ሲሞት ቀባሪው ሺ ባለቤቱ ሲሞት ቀባሪው ሃምሣ

የአዋጁን በጆሮዬ
- የአደባባይ ወሬን በምስጢር

የአውሬ ሥጋ ለወሬ
- የአውሬ ሥጋ የሚገኘው በአደን አደን ደግሞ ጀግንነትን ስለሚያመለክት

የአይጥ ምስክሯ ድንቢጥ
- ለውሸታም ውሸታም ነው የሚመስክረው

የአይጥ ሞትዋ የድመት ጨዋታዋ
- የአንዱ ስቃይ ለሌላው ደስታ ጨዋታ ነው

የአይጥ ሞት የድመት ሠርግ ነው
- የአንዱ ስቃይ ለሌላው ፌሽታ ነው

የአይጥ እርጉቱ የድመት ወቱ
- የማይሆንና የማይታመን

የአይጥ እርጉዟ የድመት ወዟ
- ዞሮ ዞሮ በመጨረሻ ማጠቃለያው እዚያው ነው

የአይጦች ዝላይ ለነእቶ ውሮ ሲላይ ነው
- የሚዳቋ ግርግርታ ለውሻ ሠርጉ ነው

የአደባባይ ሚስጥር
- ሁሉም ሰው የሚያውቀው

የአዳኝ ውሻ መነጽሩ ከእፍንጫው ነው
- ውሻ ከዐይኑ የበለጠ የሚጠቀመው በአፍንጫው ነው

የአገር ልጅ የማር እጅ
- የአገር ልጅ ለችግር ጊዜ ደራሽ ነው

የአገር ጠላት ሽፍታ የገንዘብ ጠላት መሸታ
- ገንዘብን የሚያባክን የመጠጥ ሱስ ነው

የአጭር ኩራት የሴት ለካር አያዋጣም
- የሴት ጠጪ የግመል ፈንጪ የለውም

የአፍ ብልሃት ጌትነት የእጅ ብልሃት ባርነት
- አፍ ያለው ከፍተኛ ደረጃ ይደርሳል /የቀድሞ አስተሳሰብ/
- ባለሙያነት ክብር ነው

የአፍንጫ እድፍ ለእጅ ይተርፋል
- ለእግር የፈሩት ለቂጥ ይተርፋል

የአፍ ወለምታ በቅቤ አይታሽም
- አፍ ሲያመልጥ ራስ ሲመለጥ አይታወቅም

የአፍ ዘመዶች ከገቢያም አይገድ
- የአፍ ወዳጅ ከገበያም ሞልቷል

የእህል ክፉ ክርትፉ
- ያልተስተካከለ ነገር ሁሌም ችግር አለው

የእህል ጌታ ፈርዛዛ የወርቅ ጌታ ቀበዝባዛ
- ሀብታም ሰው ለሀብቱ በጣም ይጨነቃል



የእህል ጣዕም በጉሮሮ የነገር ጣዕም በጆሮ
- ሁሉም በተገቢው መንገድ ሲፈጽም ትርጉም ይኖረዋል

የእህት ልጅ ባይወልዱትም ልጅ ነው
- የእህት ልጅ እንደራስ ልጅ ይታያል

የእረኛ ፈሱ መርዘኛ
- ከከብቶች ጋር ሲሮጥ ስለሚውል ፈሱ የቆነሰ ነው

የእሬትን ምሬት ያልቀመሰ የማርን ጣዕም አያውቅም
- መከራን ያላየ የደስታን ጣዕም በሚገባ አያውቅም

የእርኩስ መውጊያ አደረገኝ
- ሰዎች እንዳይወዱኝ አደረገኝ

የእሳት ልጅ አመድ
- የጀግና ልጅ ፈሪ

የእሳት እራት አያውቅም መብራት
- ጠፊ የሆነ ነገር ጠቃሚ የሆነውን አያውቅም

የእቡይ ልጅ ውዳቂ የዘማ ልጅ ሣቂ
- ተማሪ ማን ይመስላል ቢሉ መምህሩን

የዕብድ ቅል ማንጠልጠያው ፈትል
- ተው እንዳይሆን

የዕብድ በሶ
- እርጋታ የሌለው

የዕብድ እሞራ ሲላ ደንገጡሯ
- የሰውን ንብረት የሚያውድም

የዕብድ እጫዋች ሙር ነው
- ሁሉም እምሳያውን እያጣም

የዕብድ ዘመድ ሳያማስን አይሰድ
- ይሉኝታ ቢስ ሰውን ያሰለቻል

የዕብድ ገላጋይ ሾተል አቀባይ
- የዕብድ ገላጋይ ድንጋይ ያቀብላል

የእነሽክሽኩታ ግቢ /ጋብቻ/ ለፍቺ ያስቸግራል
- ከመጀመሪያው በሐሜት የተጀመረ ነገር መጨረሻው አያምርም

የእናት ልጅ የጉን አሳጭ
- ያመኑት ፈረስ በደንደሰ

የእንቢተኛ መድኃኒቱ ዳኛ
- እንቢተኛን ለሕግ ማቅረብ ነው

የእንቧይ ካብ
- ቶሎ የሚፈርስ

የእንጀራ ሊጥ ይበላል
- ትዳሩ ጥሩ ነው

የእንጀራ ቀንጣቢ የድመት አላቢ
- አይጥ ቤት ብቅል

የእንጀራ አብራጃውን የወጥ ለብታውን
- ሁሉም ነገር እንደየአስፈላጊነቱ መጠቀም ያስፈልጋል

የእንጀራ እናት ምን አጠናሽ እንደ ጅማት
- የእንጀራ እናት ዐረመኔ ናት

የእንጀራ ወጡ ረኃብ ነው
- ሲርብህ ደረቅ እንጀራ እንኳን ይጣፍጥሃል

የእንግዳ ሰማዳ ያመጣል ብዙ ዕዳ
- እንግዳ በመመሳለስ ባለቤቱን ያከስራል

የእንግዳ ለማዳ ይገባል ከጓዳ
- መለማመድ ቀስ በቀስ ያዛምድ

የእንግዳ ቀበጥ ባለቤት ያጉርሳል
- እንግዳ ሲያፍር ባለቤቱን ይጋብዛል

የእንጦጦ መምህር ሲናገሩ ባመት ያውም ሬት
- ብዙ ጊዜ መልካም ነገር ጠብቆ ክፉ ነገር ሲደርስ ልብ ይሰብራል

የእከክ መድኀኒቱ አለመቅረብ አለመቀራረብ ነው
- ችግር ሊያመጣ የሚችል ቦታ አለመቅረብ ጥሩ ነው

የዕውር ልቡ እየሩሳሌም ሐሳቡ
- የማይሳካን ነገር ሳይ ምኞች መመኘት

የዕውር ሞቱ የጨረቃ ንጋቱ አይታወቅም
- ገጣጣ ሰው ሞቶ የሣቀ ይመስላል

የዕውር ቀበጥ ከመሪው ጋር ይጣላል
- አጉል ጥጋብ ችግር ላይ ይጥላል

የዕውር ነፍጠኛ የወንበር ፈረሰኛ
- ዕውር በጦር መሣሪያ የመገልገል አቅም አይኖረውም

የዕውር አስተናባሪ የድውይ አጋፋሪ
- ለየሥራው ዓይነት ተስማሚ ሰው መመረጥ አለበት

የዕውር አዝማሪ የደንቆሮ ተጠሪ
- አንዳንድ ሙያዎች ከአካላዊ ብቃት ጋር የሚሄዱ ይሆናል

የዕውር አፍጣጭ የንጉሥ ቀላዋጭ
- ሊሆን የማይችል ነገር

የዕውር ግልምጫ የአንካሳ ሩጫ
- ሊሆን የማይችል ነገር

የእውነት በትር ትቀጥናለች እንጂ አትሰበርም
- እውነት ለጊዜው ትጠፋለች እንጂ ዞሮ ዞሮ ሐቁ ይወጣል

የእውነት ዘንግ ትመነምናለች እንጂ አትሰበርም
- እውነት ለጊዜው ይለወር እንጂ ዞሮ ዞሮ ሐቁ ይወጣል

የዕዳ ጉደሎ ይንቦጫቦጫል
- ፈልጌ ያደረግሁት ስለሆነ እቀጥልበታለሁ

የእጅ ሌባ ይያዛል የአፍ ሌባ ያስገርፋል
- የአፍ ሌባን ለመያዝ ያስቸግራል ተጨባጭ የሆነ ነገር በእጁ ላይ ስለማይገኝ



የእጅ ብልሆቱ ባርነቱ የአፍ ብልሃቱ ጌትነቱ
- ከእጅ ብልሃት የአፍ ብልጠት ይበልጣል /የቀድሞ አስተሳሰብ/
- ከአፍ ብልሃት ይልቅ ሙያዊ ችሎታ ጠቃሚ ነው /የአሁን አስተሳሰብ/

የእግር ጌጡ መርገጡ
- የአንድን ነገር ትልቅነት በተሰጠው ሙያ በቂ ግልጋሎት መስጠት

የከረረ ይበጠሳል የተበደለ ይካሳል የበደለ ይወቀሳል
- ተቻችሎ ተስማምቶ መኖር ጠቀሜታ አለው

የከሳ አሪያ ይገራል
- አንድ ሰው አንዳች ሥልጠና ለመውሰድ የሚሠለጥን ዓይነት መሆን አለበት

የከብት አገሩ ባለቤቱ የሰው አገሩ ምግባሩ
- የቤቱ ባለቤት በሥሩ ላሉት ሁሉ የሚያስብና የሚመራ ነው

የከተማ ዳንዴ የበረሃ ወንበዴ
- ጠባዩ አኗኗሩ ለኅብረተሰቡ የማይስማማ

የከተማን ወሬ መስማት ትልቅ አዳራሽ መሥራት
- የከተማ ወሬ ብዙ ነው ምን ቅጡ

የከፈተውን ጉሮሮ ሳይዘጋው አያድርም
- ዓምላክ ጾም አያሳድርም

የከፋ እውነት የተፈጠረ ነው ከውሸት
- አንዳንዱ እውነት ወይም ሐቅ ለማመን የሚያስቸግርበት ጊዜ አለ

የከፋው ሰው ሲሔድ አይለናበትም
- የተበደለ ሰው ጉዞውን በጨረቃ ይጀምራል

የካሕን ዓይን አፋር የአህያ ዕውር የሴት ደፋር አይረቡም
- ለሁሉም ቦታ ቦታ አለው

የክረምት ጥማትና የመከር ጊዜ ራብ አለባለቤቱ የሚያውቀው የለ
- የውስጥ ችግሩን የሚያውቀው ያው ባለቤቱ ነው

የክፉ ልጅ እናት ሁልጊዜ ታለቅስ
- ልጁ በሚፈጽመው ተግባርና በሚደርስበት ችግር ምክንያት

የክፉ ሰው ተዝካሩ ያቅራል
- የክፉ ሰው ምኑም ምኑም አይጥምም

የክፉ ሰው ተዝካር ውኃ ያስወስዳል በኅዳር
- የክፉ ሰው ጣጣ ያልታሰበ ችግር ውስጥ ሰውን ይጥላል

የኮራ ተጕዳ አይዋጋም የበሬ ቆዳ
- አጉል ኩራት ይገኝ ከነበረ ጥቅም ያስገልላል

የኮሶ ማግስት እናት በሆነች አራት አምስት
- በኮሶ ማግስት ረኃብ ስለሚጠና

የኮሶ እሪያ ይገራል
- በአስፈላጊው ነገር ቀስ በቀስ ለውጥ ማምጣት ይቻላል

የወለደ ይልላል የበደለ ይከሳል

- ቅርበትን ወዳጅነትን ለማመልከትና ተፈጥሮአዊና ማኅበረሰባዊ ሁኔታዎች ያስገድዳሉ

የወለደውን ሲስሙለት ያቀረበውን ሲበሉለት ደስ ይለዋል

- ሰው ያቀረበውን ሲበሉለትና ልጁን ከወደዱለት በጣም ደስ ይለዋል

የወለዱት ሁሉ ካደገ የዘሩት ሁሉ በጸደቀ

- ያሰቡት ሁሉ እንዳሰቡት ትክክል ላይሆን ይችላል

የወለፈንድ ሰልቻ ጤፍ ይቋጥራል ባቄላ ያፈላል

- ነገሩ ሁሉ የተዘባቢጠሸና የማይታመን

የወለፈንድ ኑሮ በሑዳዴ ቋንጣ በፋሲካ ሽሮ

- ሁኔታዎቹ የተዟዟሩ መሆናቸው

የወላጅ ሆድ ቀጥቀጥ የልጅ ሆድ ቀጥ

- ወላጅ ለልጆቹ በጣም ያስባል ልጅ ግን ምንም

የወረት ኮሶ ይጣፍጣል

- የወረት ነገር ሁሉ ደስ ይላል

የወረት ውሻ ስሟ ወለተ ጴጥሮስ

- የወረት ነገር ሁሉ ደስ ይላል

የወረወርኩት እንካሴ ተመልሶ ለራሴ

- ሌላውን እጐዳለሁ ብዬ እኔኑ መልሶ ጉዳት ላይ ጣለኝ

የወረደ መዓቱን የመጣ ምጣቱን

- የከፋ ነገር መድረሱን ለማመልከት

የወሬ ቆርፋዳ ዋንጫ ቅቤ አያርሰውም

- የሚያስለች ወሬ መስማት አያስፈልግም

የወርካ ልጅ ሣንቃ የአሰቃ ልጅ አሰቃ

- የአሰቃ ልጅ አሰቃ እንኳ ባይሆን እንደ አባቱ ይከበራል

የወሰን ላይ ሰዎች ሌቦች ወይም ሽፍቶች

- ጠረፍ ያሉ አንዳንዴ ቅሚያ ስለሚያካሒዱ የሚነገር

የወታደር ፈዛዛ የእናት ነዝናዛ የሴት ቀበዝባዛ

- ወታደር ከፈዘዘ እናት ከተነዛነዘች ሴት ከተቅበዘበዘች በማኅበረሰቡ የማይጠበቁ ባሕርያት ናቸው

የወንበዴ ዋሻ የሌባ መሸሻ

- አባሪ ተባባሪ

የወንድ ልጅ ሞት ያደረገውን የዘነጋለት

- ወንድ ልጅ ዝንጉ ከሆነ ምንም ዕድገት የለውም

የወንድምህ ጢም ሲላጭ ጢምህን ውኃ አርስ

- የወንድምህ ዕጣ እንደሚደርስህ አስብ

የወንድም ልጅ ባይወልዱትም ልጅ ነው

- ያው እንደራስ ልጅ የሚቆጠር ነው

የወንድ አልጫ የእንጆድ ሙቀጫ

- የማይረባ ፈሪ



የወንዶች ባል አይተህ ማር

- ጀግና ጨካኝ አይደለም

የወንጭፍ ድንጋይ ባልነበር የማሽላ አሽት መልካም ነበር አለች ወፍ

- ሁሉም ለራሱ በማሰብ

የወይራ ዘለላ ጋን ይሞላ የሥንዴ ዛላ እፍኝ ይሞላ

- ወይን ሲጨመቅ ሲበረክትና ለመጠጥ አገልግሎት ይውላል

የወደቀ ተነጠቀ

- ደካማ የሆነ ሰው በእጁ ያለው ይወስድበታል

የወደቀን እንሳ የሞተን አትርሳ

- ከድንበሩ አትለፍ በሰጡህ አትሰነፍ

የወደቀ ግንድ ምሳር ይበዛበታል

- የተቸገረ ሰው ካለ በላይ በላይ ነገር ይመጣበታል

የወደደ ሰው ዐይንም የለው

- ፍቅር ዕውር ነው

የወደደውን አቅፎ የጠላውን ነቅፎ

- የወደደውን ይንከባከባል የጠላውን ደግሞ ያንጓጥጣል

የወደዱትን ቢያጡ የጠሉትን ይቀላውጡ

- ተፈላጊው ቢጠፋ የማይፈለገውም ነገር ከምንም ይሻላል

የወደድከው ቂጣ ሰተት ብሎ መጣ

- ያመኑት ፈረስ በደንደስ

የወዳጅ ሚዛኑ መከራ ነው

- ወዳጅ ወዳጅነቱ የሚታየው በመከራ ጊዜ ነው

የወዳጅ ሰልቻው ለየብቻው

- እያንዳንዱን እንደባሕርይውና እንደጠባዩ ማስተናገድ

የወዳጅ ተጋፊ የጠላት ደጋፊ

- ወዳጅ መስሎ መሰሪን በጥንቃቄ ይመለከቷል

የወዳጅና የኮርቻ አሰመንካቱ ብቻ

- ወዳጅ ለወዳጁ ኮርቻም ለተቀማጩ ምቹ ነው

የወዳጅ ከዳተኛ አዱኛ

- የወዳጅ ከዳተኛ አያድርስ በዓለም ውስጥ ከፍተኛው መጥፎ ነገር

የወዳጅ ወዳጅ ወንዝ ያሻግራል

- ሰው ማወቅ ጥሩ ነው ለችግር ጊዜ ሊደርስ ይችላል

የወጋ መጋኛ መቅበጥ የሰመደ ዳኛ

- የሰመደች ጦጣ ሁልጊዜ ሽምጠጣ

የወጋ ቢረሳ የተወጋ አይረሳ

- ሰውዬው ቢረሳ የተበደለው ሰው አይረሳ

የወጣ ሰው አንዱን ጥሎ አንዱን አንጠልጥሎ

- ሰው ሁልጊዜ ያሰበው አይሟላለትም

የወጣ ቢገባ የገባ ይወጣል

- ጊዜው እንካ በእንካ ነው

የወፍ ዞላ /ዝላ/ ክቤት ይውላል እሸት /አሸን/ ሲፈላ
- የሚፈለገው በቅርብ ከተገኘ ምን ያለፋል

የወፍጮ እንጉርጉሮ አይሆንም ለሠርግ
- ያ ሌላ ይሄ ሌላ

የዋሀ ፊቱን ቢመልስ ማጅራቱ ጋር ይመስለዋል
- በጐ ነገር በጣም ይከብደዋል

የዓመል ታናሽ ይጥላል ጭራሽ
- ዓመሉ መጥፎ የሆነ ሰው ከብዙ ሰዎች ጋር አይስማማም

የዓምላክ ነገር አይመረመር
- ሳትመራመሩ በእምነት ኑሩ

የዓባይ ልጅ ኩሬ
- የእሳት ልጅ አመድ

የዓይን ሕመም ክሱት ነው የሆድ ሕመም ልግም ነው
- አንዳንድ የሰው ባሕሪያት በግልጽ ሲታዩ አንዳንድ ባሕሪያት ግን ድብቅ ናቸው

የዓይን ጨንቋራ ሰው ያየዋል፤ የልብን ጨንቋራ እግዛብሔር ያየዋል
- ሰው ላይ ላዩን እንጂ ውስጡን የሚያይ ዓምላክ ነው

የዕብድ ቅል ማንጠልጠያው ፈትል
- ተው እንዳይሆን

የዕብድ በሶ
- እርጋታ የሌለው

የዕብድ አሞራ ሲላ ደንገጡሬ
- የሰው ንብረት የሚያወድም

የዕብድ አጫዋች ሙር ነው
- ሁሉም አምላያውን አያጣም

የዕብድ ዘመድ ሳይማለን አይለድ
- ይሉኝታ ቢስ ሰውን ይሰለቻል

የዕብድ ገላጋይ ሾተል አቀባይ
- የዕብድ ገላጋይ ድንጋይ ያቀብላል

የዕውር ልቡ እየሩሳሌም ሐሳቡ
- የማይሳካ ነገር ላይ ምኞት መመኘት

የዕውር ሞቱ የጨረቃ ንጋቱ አይታወቅም
- ገጣጣ ሰው ሞቶ የሣቀ ይመስላል

የዕውር ቀበጥ ከመሪው ጋር ይጣላል
- አጉል ጥጋብ ችግር ላይ ይጥላል

የዕውር ነፍጠኛ የወንበር ፈረሰኛ
- ዕውር በጦር መሣሪያ የመገልገል አቅም አይኖረውም

የዕውር አለተናባሪ የድውይ አጋፋሪ
- ለየሥራው ዓይነት ተስማሚ ሰው መመረጥ አለበት



የዕውር አዝማሪ የደንቆሮ ተጠሪ
- አንዳንድ ሙያዎች ከአካላዊ ብቃት ጋር የሚሔዱ ይሆናሉ

የዕውር አፍጣጭ የንጉሥ ቀላዋጭ
- ሊሆን የማይችል ነገር

የዕውር ግልምጫ የአንካሳ ሩጫ
- ሊሆን የማይችል ነገር

የዕዳ ጐዶሎ ይንበጫበጫል
- ፊልጌ ያደረግሁት ስለሆነ እቀጥልበታለሁ

የዋለበት ዐረም በላው
- የለፋንበት ነገር አልሆነልንም

የዋርካ ልጅ ዋርካ ያለቃ ልጅ አለቃ
- የአቡይ ልጅ አቡይ

የዋስ ተሚጋች የቆማጣ ፈትፋች
- እያገባው ገብቶ እያወዛው ተቀብቶ

የዋስ ወንድም አይታገት የአባያ ወንድም አይጐተት
- በአንዱ ሥራ ሌላው አይጠየቅም

የዋና ይሻገራል የሠራ ይከብራል
- ሁሉም ነገር በጥረትና በትጋት ይገኛል

የዋጋ ብልጥ ልብ ይግጥ የልጅ ብልጥ እየቀደመ ይውጥ
- ለአንድ ነገር የተሰጠው ዋጋ ከፍ በሚልበት ጊዜ ገዢውን ያበሽቃል

የውሎ መንገድ በሩጫ
- ረጅም ጊዜ የሚፈጀውን ሥራ በአጭር ጊዜ ለመሥራት መሞከር

የውስጥ እንጀቴን የላይ ቁርበቴን
- መከራና ስቃይ አጋጠመኝ

የውሻ ትሕትና የካሕን ዕብድና መች ይጋጥምና
- እንዲህ ዓይነቱ አልፎ አልፎ ካልሆነ በስተቀር አያጋጥምም

የውሻን ጥርስ በአጥንት ይፈሯል
- ወዳጅህ ሲታማ ለኔ ብለህ ስማ

የውሻ አፍንጫ አለው
- አንድን ነገር ተከታትሎ የመያዝ የመድረስ ችሎታ አለው

የውኃ ውኃ ምን አለኝ ቅሃ
- የዚህ የዚህ ምን አለፉኝ ነበር

የውኃ ጡር በእድፍ ያስታጥባል
- የውኃ ጥቅም የሚታወቀው ምንጩ የደረቀ ቀን ነው

የውድማ ዘንዶ ይቀጠቀጣል እንደ በረዶ
- ሌባ ተይዞ ዱላ አይጠየቅም

የውጭ አልጋ የውስጥ ቀጋ
- በቤት ውስጥ አለቺጋሪ ከቤት ውጪ ላለ ሰው ቸርና ለጋስ ሆኖ የሚታይ ሰው

የዘሳን ቤት ሁልጊዜ ስደት
- በየደረሱበት የሚጣል ዳስ /ጐጆ ቢጤ/

የዘላን ጠመኛ ከጥጃ ጓዳ አታስገቡኝ ይላል
- ከሥጋው ጠመኛ ነኝ ከመረቁ አውጡልኝ

የዘመተ ይመለስ የገደለ ይንገሥ
- አሸናፊ ምንጊዜም የበላይ ነው

የዘመኑ ሰው ምላሱ መንታ አንዱ ለፍቅር አንዱ ላሜታ
- ሰው መልካም በተናገረበት ክፉም ነገር ይናገራል

የዘመኑ ሰው ሲያቀርቡት ያርቃል ሲወዱት ይጠላል
- የዘመኑ ሰው ጠባይ መላ ቅጡ የጠፋ ነው

የዘመኑ ወሬ ይቀዳል ባቦሬ
- በዚህ ዘመን ወሬ በዝቷል

የዘመድ ለማኝ ከዝምድናው ወጥቶ የለመነውንም አጥቶ
- ላይሳካ ነገር ራስን ዝቅ ማድረግ አይገባም

የዘመድ ሎሌ የፈረስ ጭሌ ሲወጣ ወጥቶ ነው
- ከባለቤቱ ሥር አይታጣም /ባለቤቱ ሲወጣ አብሮ ይወጣል/

የዘመድ ቁስ እየፈታ ያለቅስ
- የሙያውን ተግባር እየፈጸመ ውስጥ ውብጡን የዝምድናውንም ሁኔታ ያካሒዳል

የዘመድ አዳይ ጦም ያላድራል
- በይሉኝታ የታሰረ ሰው

የዘመድ ዘመድ ወንዝ ያሻግራል
- ምንም ቢከፋ ዘመድ ምንም ቢጠብ መንገድ

የዘመድ ጥል የሥጋ ትል
- የዘመድ ጥል ቂም አይያዝበትም

የዘማ ልጅ ሣቂ የእቡይ ልጅ ውዳቂ
- የባለጌ ልጅ ባለጌ ነው

የዘራ ምን ያመጣ ፍሬና ፊንጣጣ
- ሰው የዘራውን ያጭዳል

የዘሬን ብተው ያንዘርዝረኝ
- የቤተሰቤን ወግ እከተላለሁ

የዘነጋ በሩን ዘጋ
- የሮጠ አመለጠ የቆመ ቀለጠ

የዘነጋ ተወጋ
- ዝንጉ ሰው ለአደጋ ይጋለጣል

የዘገነ አዘነ ያልዘገነም አዘነ
- ያገኘው አነሰኝ ያላገኘውም አጣሁ በማለት ማዘን

የዘገዩ ተለዩ
- በሰዓቱ ያልተገኙ ከኅብረቱ ራቁ

የዘፈን መጀመሪያው እስክስታ ነው
- የነገር ዳር ዳርታ ማለት ነው



የዚህ ዓለም ፍቅር ሰኞ አዲስ ማክሰኞ ልብስ ረቡዕ ብጥስጥስ
- የዘመኑ ፍቅር ሲጀምሩ ሞቅ ሞቅ ይላል ከትንሽ ጊዜ በኋላ ቀዝቀዝ መጨረሻ ይከስማል

የዛሬን ለቀባሪ የነገን ለፈጣሪ
- ስለዛሬው አስብ እንጂ ለነገ አትጨነቅ እግዚአብሔር አለልህ

የዛሬ ዘመን ጫጩት ካውራ አኩል ትውጣለች ወይ ያንቃታል ወይ ትሞታለች
- መስገብገብ ለችግር ይዳርጋል

የዝሆን ከላቱ የባለጸጋ ድህነቱ አይታወቅም
- ባለጸጋ ቢደኸይም ሁሌ ያለው ነው የሚመስለው ለለው

የዝሆን ጆሮ ይስጠኝ
- እንዳልሰማ ሆነ

የዝንብ ሽውታ የነገር ስልት ይበጥሳል
- የሰው ንግግርን ካቋረጡበት ውሉ ይጠፋዋል

የዝንብ ተላላ ካንድ በሬ ደም ይቀርባታል
- ትልቁን ትቶ ትንሹ ላይ ማተኮር

የዝንብ ተባቱ የሴት ጭምቱ ሳይታወቁ ሞቱ
- የሴት ጭምት የላትም እንደማለት

የዝንጀሪትዬ ዝንጀሪት ባሌ ገደለ በነጋሪት
- አንድ ነገር በይፋ ሲደረግ ወይም ይፋ ሲሆን

የዝንጀሮ ልጅ ከዛፍ የመምህር ልጅ ከመጽሐፍ
- መልክ ሰጠኝ እንጂ ሙያ ከጕረቤት እማራለሁ

የዝንጀሮ መነኩሴ የስንበሴጥ አንካሴ
- የማይሆንና የማይታሰብ ነገር

የዝንጀሮ መንገድ ከገደል ያደርሳል
- የተንኮለኞች ሥራ ሔዶ ሔዶ ለመከራ ይዳርጋል

የዝንጀሮ ንጉሥ እሱው ይከምር እሱው ያፍርሰው
- አዛዥ ናዛዡ ራሱ ነው

የዝንጀሮ አንካሳ የውሻ እራት ይሆናል
- ደካማን ያገኘው ሁሉ አይለቀውም
- ተናካሽ ውሻ የዝንብ መቋደሻ

የዞረ ምን አመጣ ፌራና ፈንጣጣ
- የዙረት ትርፉ ድካምና በሽታ መሸመት ነው

የዩጁ ቁስ ቅኔ ቢጉድልበት ቀረርቶ ሞላበት
- አንዳች ነገር ሲታጣ በሌላ ተመሳሳይ ነገር ሲተካ ይችላል

የያዘውን ከወረወረ ፈሪ አይባልም
- ሰው ባለው ይሰለፋል

የደላው ሙቅ ያኝካል
- ሐሳብ የሌለበት ሰው የማይሆን የማይደረግ ነገር ያደርጋል

የደላው ውሻ ማር ይቀላውጣል
- የማይሆን ነገር ያልማል

የደመና ውኃ ጥምና የእናት በደል አይታወቅም
- እናትን ትበድላለች ብሎ ማንም አያስብም

የደበሎ ተባይ የዳኛ አባይ ቢገለጡት አይታይ
- በደበሎ ውስጥ ያለተባይ እንዲህ በቀላሉ ሲታይ ወይም ሲገኝ አይችልም

የደባ ገበያ በሬው ባሥር ቆዳው በሃያ
- ተንኮለኛ የማይሆነውን እንደሚሆን አድርጎ ይናገራል

የደንቆሮ ለቅሶ መልሶ መላልሶ
- ያንኑ አንድን ሐሳብ መላልሶ መናገር ውጤት አይኖረውም

የደንቆሮ ተጣሪ የዕውር አዝማሪ ዘዋሪ
- የአካል ጉዳት ችግር ያለበት ሰው ለአንዳንድ ሁኔታዎች አያመችም

የደንቆሮ ዘፈኑ ያው አንድ ብቻ ነው
- የደንቆሮ ለቅሶ መልሶ ቀልሶ

የደጃዝማችን ሚስት አይቼ ሚስቴን ጠላሁ
- የማያገኙትን መመኘት ከንቱ ልፋት

የተደገመ ተረገመ
- ሁለቴ መታለል እርግማን ያስከትላል

የደግ ጊዜ ባዕድ የክፉ ጊዜ ዘመድ
- ዘመድ ለችግርህ ይደርስልሃል

የደፋት ሬሳ የጠበሱት ዓሣ
- ለሚቀጥለው ተግባር በዝግጅት ላይ ያለ ማለት ነው

የዳቦ ልብ ልቡን የዳገት ጥግ ጥጉን
- ለጥቅም መሯሯጥ ለሥራ ጊዜ መሸሽ ጥሩ አይደለም

የዳኛ ልል ያማታል የአባል ልል ያፋታል
- የአለቃ ልል በጥፊ ያወላውል

የዳኛ ጅሉ ያማታል ያመል ክፉ ያፋታል
- ዓመል ከሌላት መጣላትና መፋታት አይቀርም

የዳኛ ጅል ያማታል አባይ ምስክር ያስረታል
- የአለቃ ልል በጥፊ ያወላውል

የዳገት ሩጫ የባለጌ ጡጫ
- ያዳክማል

የዳገት በረዶ የቆላ ዘንዶ
- በጣም አስከፊ የሆነ ችግር

የዳጉሳ እንጀራ በትኩሱ የባዕድ ፍቅር በአዲሱ
- ፍቅርና ቡና በትኩሱ ይጣፍጣል

የድሃ ሃብቱ እንቅልፉ
- ድሃ የሚጨነቅለት ሀብት ስለሌለው እንቅልፉን ሲለጥጥ ያድራል

የድሃ መድኃኒቱ የድንገቱ
- ድሃ ሲያመው የሚያኝከው ድንገተኛ የተባለው ሥር ነው

የድሃ ማጀት ቃጢ ማር ለማስቀመጥ አይችልም
- አይጥ ቤት ብቅል



የድሃ ቁም ነገሩ ገብስ እስከ አስሩ
- ድሃ ገብስ በመብላቱ እንደጠላም አድርጎ በመጠጣቱ ጥቅም ጥንካሬ አግኝቶበታል

የድሃ ብድር አይውል አያድር
- የሰው በልቶ አያድሩም ተኝቶ

የድሃ ተዝካር የጉባጣ ስካር
- ምንም ይሁን ያህል የጐላ ነገር የማይታይበት

የድሃ ነገር ማንገቻ የሰው
- የድሃ ነገር የተሟላ አይደለም

የድሃ ጉልበት በገበያ ያልቃል
- ድሃ ሲወጣ ሲወርድ ጉልበቱን ያባክናል

የድሃ ግድርድር ሀብታም ይጋብዛል
- እንግዳ ሲያፍር ባለቤቱን ይጋብዛል

የድሃ ጠላ ጧት አልፈላ ማታ አተላ
- መጠኑ ያነሰ ወይም በቂ ያልሆነ ነገር

የድሃ ጮማ የዱባ ስንጋ ነው
- ላላዩ ልጅ ዳቦ ፍሪዳው ነው

የድህነት አሸከር ድህነት መስሎ ይታያል
- የፋሲካ ዕለት የተቀጠረች ገረድ ሁሌ ፋሲካ ይመስላታል

የድመት ማንቀላፋት አይጦችን ለማጥፋት
- ጅብ እስኪነክስ ያነክስ

የድመት ትዕግስት አይጥ እስክትይዝ ድረስ ነው
- ጅብ እስኪነክስ ያነክስ

የድንጋይ ልብ የኩበት ግንብ የሰውም
- ያለሙያ በሰው ሙያ ውስጥ ለመገኘት መሞከር ራስን ማዋረድ

የድንጋይ መቀመጫ የባዕድ ፍቅር እያደረ ይቆረቁራል
- ከባዕድ ከተፋቀሩ በኋላ ቀስ በቀስ ይቀዘቅዛል

የድንጋይ ንፍሮ የብረት ቆሎ
- የማይሞከር ነገር

የድንጋይ ጦርነት የሸሮን ቀለብነት የሚስት ባርነት
- የሚያውቅ ያውቀዋል

የድፍድፍ ኩራት ውኃ እስኪገባበት
- የባለጌ እብሪት በቁጥጥር ሥር እስኪውል ነው

የዶሮ እንገት ክምንቸት
- ዞሮ ዞሮ ይቆያል እንጂ አይቀርም

የጀመሩትን መጨረስ የቆረሱትን መጉረስ
- ተገቢ ነው

የጅብ ሁለት ስበሩ የባለጌ ወታደሩ አስቸጋሪ ነው
- ሥርዓት የሌለው ምንጊዜም ለኅብረተሰቡ ሸክም ነው

የጅብ ሰማዳ ያህያ ፍሪዳ የሰውም
- ምን ቢሆን ጅብ ከሰው ጋር ሊያኖር የሚያስችል ባሕሪ የለውም

የጅብ ችኩል ቀንድ ይነክሳል
- የአይጥ ችኩል የድመት አፍ ይልሳል

የጅብ እንግዳ ቁርበት አንጥፉልኝ ይላል
- ስደት ለወሬ ያመቻል

የጅብ ገበሬ የጦጣ ዘር አቀባይ የዝንጀሮ ጐልጓይ ሁሉም በየበኩሉ እበላ ባይ
- ለሥራ ሳይሆን ለመቀራመት የተሠማሩ ናቸው

የጅብ ጓደኛ ከጥንብ ያደርሳል
- ውሎም ምኞቱና ፍላጐቱ ያው በመሆኑ

የጅብ ፈሪ የሞት ቀሪ
- ሞት ለማንም የማይቀር ዕዳ ነው

የገላጋይ ትዕግስት የባለቤት መጠቃት
- ነገር ለማብረድ የተነሳ ሰው ቁጡና ተናዳጅ መሆን የለበትም

የገላጋይ ደም የለውም
- ገላጋይ ሲገላግል በሚደርስበት ጉዳት ማንንም መጠየቅ አይችልም

የገማ ሰው ለውን አይሸሽም ሰው ክሱ ይሸሻል እንጂ
- የበሰበሰ ዝናብ አይፈራም

የገበያ ሽብር ለሌባ ሠርጉ ነው
- ፍየል በግርግር እናቱን ይሰርራል
- የገበያ ግርግር ለሌባ ያመቻል

የገባ ወንድና የታሰረ አንበሳ በብላሽ ያገሳ
- ገሌ የገባ ወንድ ልቆጣ ቢልም አያምርበት

የገብስ ብዙ ነዶ የጤፍ ስሱ ነዶ
- ፍሬ ያለው ቁምነገር ያለው ትንሹ ይበቃል

የገንዘብ እርጌ ያባት ባለጌ የለውም
- ያበደርከውን ገንዘብ በተገኘበት ጊዜ ተቀበል

የገዛ ጌታ እግር ይዞ ይመታል
- ማን ላይ ቆመሽ ማንን ታሚያለሽ

የገደለው ባልሽ የሞተው ወንድምሽ አዘንሽ ቅጣ አጣ ከቤትሽ አልወጣ
- እዚያው በዚያው አስቸጋሪ የሆነ ነገር

የገደል ማሚቶ ዳቦ ልስጥሽ ድፎ
- ያሉትን መልሶ ማለት ትርፉ ጊዜ ማጥፋት

የጉልበት ገሚሱ ምላስ ነው
- ጠላትን ማዳከሚያ ዋና መሣሪያ ፕሮፖጋንዳ ነው

የጉልበት ግማሽ አፍ ነው
- ጠላትን ማዳከሚያው በአፍ ጉዱን በማፍረጥረጥ ነው

የጉልቻ መለዋወጥ ወጥ አያጣፍጥም
- የሰዎች መቀያየር ምንም ለውጥ አያመጣም

የጉም ሌባ ጉም ሲጠፋ ወዴት ትገባ
- ተደብቃ ትደንሳለች ሰው ሰብስባ ትወልዳለች



የጉሮሮን መታነቅ ያይን መደንቆል ያስጥለዋል
- ለአንዱ ያሉት አንዱን ይጐዳል ሌላውን ይጠቅመዋል

የጐብል ዱላ በክርከማ ያልቃል
- ሲያሽሞነሙነው ያልቃል

የጋራ እርሻ የፍቅር መጨረሻ
- እርሻው ሳይታረስ ወሬ በማውራት ጊዜውን መፍጀት

የጋራ ወንጋራ
- የፉከክር ቤት ሳይዘጋ ያድራል

የጌታ ሆድ ጠዋት ከባድ ማታ ወላድ
- ሲጀምረው ጉዳዩን አከብዶ ኋላ ግን ቀላሉን ተቀብሎ ይሔዳል

የጌታውን እመካከት ሎሌው ይመልከት
- የጌታውን ባሕርይ ተከታዩ ያውቀዋል

የግመል መጫኛ ቢበጠስ ላህያ ይበቃል
- ጋን ሲያሟጥጡት ምንቸት ይሞላል

የግፍ ግፍ በእንቅርት ላይ ጆሮ ደግፍ
- በመከራ ላይ መከራ በችግር ላይ ችግር

የጐረምሳ መልኩ እንጂ አነጋገሩ አያምርም
- በትዕቢት የተወጠረ በመሆኑ ንግግሩ አይጥምም

የጐረቤት ሌባ ቢያውቁበት ይሥቃል ባያውቁበት ይሰርቃል
- ቢያዩኝ እሥቅ ባያዩኝ እሰርቅ

የጐረቤት ሐሣብ ከገበያ አይወጣም
- በአንድ አካባቢ ያሉ ነዋሪዎች አስተሳሰብ ተመሳሳይነት ይኖረዋል

የጐበዝ ልቡ ክደረቱ የፈሪ ልቡ ከፊቱ
- የፈሪ ፍርኃቱ ከፊቱ ያስታውቅበታል

የጐበዝ ሹም የኅዳር ጉም አገር ይደረገም
- ጀብደኛ አለቃ ተከታዮቹን ለአደጋ ይዳርጋል

የጐበዝ አለሳ የወሬ አፈሳ ይደርሳል እግር ሳይነሳ
- ወሬ ቶሎ ይደርሳል

የጐበዝ ክምር እያደር ይጨምር
- ጐበዝ ሠራተኛ በሀብት እየበገለጸገ ይሔዳል

የጐበዝ ዲዳ ባመቱ ምድረ በዳ
- ተከታዮቹን በንግግር የማያግባባ ኃላፊ ተከታዮቹ ጥለውት ይሔዳሉ

የጐበዝ ጉልበቱ ከደረቱ
- ጐበዝ ልቡን ሞልቶ ደረቱን ነፍቶ ይናገራል

የጐደለው ሲሞላ የተረፈው ሲከላ
- ባለው ቦታ እዳዲሶችን መቀበል ቦታው ሲሞላ የተረፈውን መመለስ

የጐጃም አዝመራ ሽምብራ ነው አሉ እኛም እንዳንበላ ተነቀለ አሉ
- የተባለውን እነሱም እኛም አላገኘነውም

የጓደኛ ምቀኛ የከብት ቀበኛ
- ቀን አያስቀምጥ ሌት አያስተኛ

የጓደኛ ወሮ ያጠናግር ዞሮ
- ወሮበላ ጓደኛ አይጠቅምም
የጓጉንቸር ልጅ መሔድ ሳትማር መዝለል ተማረች
- እንደአገሩ ይኑሩ እንደወንዙ ይሻገሩ
የጠሉት ሰው ቢቀር ጠላ ማለቁ አይቀር
- መሆን የሚገባው ነገር ከመሆን ምንም አያግደውም
የጠላቴ ጠላቴ ወዳጄ ነው
- ጠላቴን ስለሚያጠቃልኝ
የጠላ ክፋቱ አለመገኘቱ የልጅ ክፋቱ አለመስማቱ
- ልጅ የመከሩትን አይሰማም
የጠመመውን አቅንቶ የጐደለውን ሞልቶ
- ሁሉን አሳክቶ መገኘት
የጠረጠረ ስንቁን ቋጠረ
- መጠርጠር ጥንቃቄ ማድረግ ደግ ነው
የጠረጠረ ቤቱን አጠረ
- መጠርጠር ጥንቃቄ ማድረግ ደግ ነው
የጠረጠሩበት ድንጋይ ይጥሉበት
- ጥርጣሬ ካለ ወደአንዳች ድርጊት ይመራል
የጠሩት እንግዳ አራቱ ፍሪዳ
- ለወደዱት ሰው አቅም የፈቀደውን ሁሉ ያደርጓል
የጠበቀ ከራራ ባጥና ጣራ
- ሁለቱም ተመሳሳይነት አላቸው /ባጥ-ጣራ ነው/
የጠበኛ ፊስ ዐይን ያፈስ
- ጠበኛ ሰው ምኑም ምኑም አይበጅ
የጠብ መነሻ የሰብሰቴ እርሻ
- የጠብ መጀመሪያው የማይረባ ነገር ነው
የጠብ መነሾ አበድሪኝ እርሾ
- የጠብ መጀመሪያው የማይረባ ነገር ነው
የጠንቀኛ ፊስ ዐይን ያፈስ
- ጠንቀኛ ሰው ጠንቁ ከባድ ነው
የጠዋት አር እንደመጣ የማታ አር ደም እስኪወጣ
- ለፍቅር ተመቻችቶና ተዘጋጅቶ መገኘት
የጠጅ ቤት አዛዥ እተላ አጋዥ
- ከምኑም ላላገኘ ስሙ ብቻ ተረፈኝ
የጠገበ ሰው ራብን አያስብም
- ዛሬ ያገኘ ሰው ነገ እጣለሁን አያውቅም
የጠገበ ሰው የተራበ ያለ አይመስለውም
- የተመቸው ሰው ለሌላው አያስብም
የጠገበች ዶሮ ከነጭልፊት ማኅበር ትገባ
- ዶሮ ጭራ ጭራ ታወጣለች ካራ



የጠገበ ዐበደ
- የተመቸው ያለሱ ሰው ያለ አይመስለውም
የጠገበ እንግዳ ሳይቶች አይወጣም
- ምን ይሰኝን የማያውቅ
የጠገበ ዕውር ዘንግ ይወረውር
- ዕውር ሲቀናጣ ዘንጉን ወርውሮ ፍለጋ ይሔዳል
የጠገበ ፍየል ካራ ይልሳል
- ጥጋበኛ ሰው ካለማወቅ ለሞት መንገድ ያበጃል
የጠጉር ጥቁሩ የነገር አጭሩ
- ነገር ቢበዛ በአህያ አይጫንም
የጠ.ስና የልጅ መውጫ አይታወቅም
- ደፋርና ጢስ መውጫ አያጣም
የጣት ሳያ ቅቤ ሆነች
- ይሳሱላታል
የጣመው ቀለጠመው
- የተሻለ ወይም በብዛት የፈለገውን ለማግኘት መሞከር
የጣታ በሬ ለነገ ብሎ ያጠጣል ዛሬ
- ለነገ ማሰብ ይበጃል
የጣውንት ደግ የእንቧጮ ዘንግ የለውም
- ጣውንታሞች አንዷ ለአንዷ ደግ አታስብም
የጥር በልግ የብር ዘንግ
- በጣም የሚወደድ የሚፈለግ
የጥርስን እድፍ የራስን ጉድፍ
- ባለቤቱ አይታየውም ሰው የራሱ ስሕተት አይታየውም
የጥርስ ደም ሆነባት
- የማይነገር ነገር ሆነባት
የጥቁር ሴት ንቅሳት የምንድነው? ቢለው የእግዜር ቁጣ ነው አለው
- የጥቁር ሴት ንቅሳት በደንብ አይታይም
የጥቅምት በረዶ የጫካ ላይ ዘንዶ
- በጥቅምት ወር ላይ በረዶ ከዘነበ የደረሰውን እህል ያበላሻል
የጥቅምት እርሻ የናት ጉርሻ
- ተፈላጊና ውጤት ያለው ሥራ
የጥቅምት እርሻ ያባት ውርሻ
- ተፈላጊና ውጤቱ ያማረ ሥራ
የጥጋብለት ሁሉ አንበሳ የራብ ለት ሁሉ ሬሳ
- ሰውን ሰው የሚያደርገው እህል ነው
የጦመኛ ምቀኛ
- አንደኛውን ባይጾም ይሻለዋል
የጦም ቆሎ የቁልቁለት በቅሎ
- በቁልቁለት በቅሎ መቀመጥ አስቸጋሪ ነው

የጠም ቆሎ የበዓል ዶሮ
- ሁሉም ነገር እንደጊዜውና እንደሁኔታው አስፈላጊነቱ ይጐላል

የጦርነትን ነገር ከፈሪ አትምከር
- ምን ከማን ጋር እንደምትነጋገር አስቀድመህ ዕወቅ

የጦጣ ልጅ በዛፍ የመናፍቅ ልጅ በመጽሐፍ ማን ይችላል
- ከኃዲና ተጣራጣሪ አላግባብ ከመጽሐፍ ውስጥ ጥቅስ ሲጠቅሱ ይታያሉ

የጦጣ ሞኛሞኝ የዝንጀሮ ብልጣ ብልጥ የለውም
- ሁሉም እንደየባሕርዩ እንጂ ከተፈጥሮው ውጪ ሊሆን አይችልም

የጨለማ አፍጣጭ የዕውር ገልማጭ
- ውጤት የማይገኝበት ከንቱ ድካም

የጨረቃ ሒያጅ የምስክር ፈራጅ
- ለትዝብት የተዳረገ ተግባር

የጨረቃ ንጋትና የዕውር ሞት አይታወቅም
- ገጣጣ ሰው ሳይሥቅ የሣቀ ይመስላል

የጨርቅ ነጩ የበራ ልጩ
- ሊሆን የማይችል ነገር ለማድረግ መሞከር

የጨነቀው ይዋጋል ያልደረሰበት ያዋጋል
- በሩቅ ያለ ችግሩን በደንብ አይረዳውም

የጨዋ ልጅ ሁሉ እርግዟል በሆዱ
- ሁሉም በሆዱ ቆሻሻ ነገርን ይዟል

የጨዋ ልጅ ሲያዝን ዓሣ በወንዝ ይመክን
- ከቤት ካልቀና በውጪም አይቀና አይሳካ

የጨዋ ልጅ ሲፋታ ይጋባ ይመስላል
- ሁሉንም በሣቅ በጨዋታ በመግባባት ይፈጸማልና ነው

የጨዋ ልጅና ቅል ተሰባሪ ነው
- ሰው ሁኖ ከሞት የሚቀር የለም

የጨዋ ልጅ ከከተማ የድሃ ልጅ ከውድማ
- ለሥራ ለልፋት የፈጠረው ያው በሥራ ላይ በድካም ላይ ይገኛል

የጨውን ባለዳ በጨው ቢያባብሉት ጨዋን ማለቱ አይቀርም
- ንብረቴን የእኔ የሆነውን ስጡኝ ማለቱ አይቀርም

የጨው ገደል ሲናድ ብልህ ያስቀሳል ሞኝ ይሥቃል
- ጠቃሚ ነገር ሲበላሽ ተቆርቋሪ ያዝናል ደንታ የሌለው ግን ያሾፋል

የጨው ክብት በየወጉ ይከተት
- ማንኛውም ነገር በወጉ በሥርዓቱ ይሁን

የጫማ ጠጠርና የእንጀራ ልጅ አያደር መቆርቆሩ አይቀርም
- አንድ ሐሳብ በአዕምሮ ውስጥ ከገባ እየዋለ እያደረ መጉላቱ አይቀርም

የጫማ ጠጠርና የእንጀራ ልጅ እያደር መቆርቆሩ አይቀርም
- በአዕምሮ ውስጥ የገባ ሐሳብ እየዋለ እያደር አሳሳቢ መሆኑ አይቀርም



የፈላ ጠጅ የደረሰ ልጅ
- የደረሰ ልጅ መመኪያ ነው

የፈረሰኛ ማቅ ለባሽ የቤት ትንባሆ ጉራሽ
- በጣም አስቀያሚና አስነዋሪ ባሕርይ

የፈረሰ አልጋ የተሸበረ ዜጋ
- አልጋ ፈረሰ የሚባለው ንጉሡ ሲወርዱ ስለሆነ ዜጐች ትንሽ ሲሸበሩ ይችላሉ

የፈረንጅ አሽከር ነጭ ለባሽ ሣህን አመላላሽ
- ምንም እንኳ የተመቸው ቢመስልም ያው ተራ ሥራ ላይ የተሠማራ ነው ለማለት

የፈሩት ይደርሳል የጠሉት ይወርሳል
- የጠሉት ነገር ይቆያል

የፈሪ ዱላ ሠላሳ ነው
- የማይጠቀሙበትን መሣሪያ መሰብሰብ ዋጋ የለውም

የፈሪ ገዳይነት ለማታ
- ፈሪ የሚፎክረው ማታ ምናምን ሲቀምስ ነው

የፈሰሰ አልታፈሰ
- የሔደ ካልተመለሰ

የፈሰሰ ውኃ አይታፈስም የሞተ አይመለስ
- ባለፈ ነገር መጨነቅ አይገባም

የፈሊታ ተቀጢታ
- በራስዋ ስሕተት ሌላውን ትቀጣለች

የፈላ የጥጋብም አይደል ሲረሳ
- አንድ ሰው ከሳተ መሳቱ አይረሳም

የፈስ ማደናገሪያው ዳቦ
- ሰዎች ትኩረት እንዳይሰጡት ማድረግ

የፈቷት ሚስት ያጠቡት ወጭት የወጡበት ቤት አንድ ናቸው
- ሚስት ከፈቷት ባዳ ማሽላ ከተቀረጠ አገዳ

የፉክክር ቤት ሳይዘጋ ያድራል
- ፉክክር ለሥራ መጥፎ ነው

የፊተኛውን አሳረርሽ ቢሏት የኋለኛውን ጥሬ አወጣች
- ተጠንቅቀና ሁኔታውን ተከታትሎ በሥርዓት ያለመሥራት

የፊት መሪ የኋላ ቀሪ
- እዩኝ እዩኝ ማለት

የፊት ምስጋና ለኋላ ሐሜታ ያስቸግራል
- ለማመስገን እትቸኩል

የፊት እድፍ በመስተዋት የኀጢያት እድፍ በካሕናት
- ያለብንን ጉድለት በመስታወት አይተን እንደምናርም ሁሉ ኃጢያትም በክሕናት በሚሰጥ ሉባኤ ሊወገድ ይችላል

የፊት ክብት የእጅ ወረት
- በእጅህ ያለ ክብት እንደገንዘብ ይቆጠራል

የፊት ወዳጅህን በምን ቀበርከው? በሻሽ የኋለኛው እንዳይሸሽ
- ጓደኞችህ እንዳይርቁህ በእንክብካቤ ያዝ

የፊት የፊቱ አለ ጓያ ነቃይ
- ያለፈውን ረስተህ የወደፊቱን ሁኔታ ተመልከት

የፋቂ ለነፍ አንዱን ሳይፍቅ አንዱን ይዘፍቅ
- በላይ በላዩ ሥራ መደራረብ የስነፎች ተግባር

የፋቂ ቆንጆ ቡድንት አይተወውም
- ያን የተለመደ ባሕርዩን አይለውጥም

የፌጦ መስሎሽ ለናፍጭ ትቀምሽ
- ላይ ላዩን በማለት መታለል

የፌጦ ብቅል የብሳና ጌሾ የተልባ አሻሮ ይህን ጠምቆ ለማ?
- የለው ነገር ሰማይሰማ

የፍቅር ጣዕሙ በመሳሳሙ
- የሚዋደዱ በመሳሳም ፍቅራቸውን ያጣጥማሉ

የፍየል ልጁን የሌባ እጁን
- ሌባ እጁን ከተያዘ ወዴት ሊሔድ ይችላል

የፍየል ጅራት ከብርድ አያድን ሐፍረት አይከድን
- እንዲያው ለምልክት ብቻ የሚገኝ

የፍየል ጭራና የሰው ሐሳብ ሁልጊዜ ወደ ላይ ነው
- ሰው ሁልጊዜ ለራሱ የሚመኘው ትልቅ ትልቁን ነው

የፍጅት ወራት እሳት በወንፊት
- በጣም አስጨናቂና የመከራ ወቅት

የፖሊስ ዘመድና የቤንዚን እመድ የለውም
- ምን ዘመድ ቢሆን ፖሊስ ያገኘውን ወደሕግ ከማድረስ አይዘናጋም

ያህያ ልጅ ጥሎ ይረግጣል የፈረስ ልጅ ጥሎ ይደነግጣል
- መልካም ባሕርይና መጥፎ ባሕርይ ያላቸው ለየቅል ናቸው

ያህያ ሥጋ ካልጋ ሲሉት ካመድ
- ለእህያ ማር አይጥማትም

ያህያ ሥጋ ውርደተኛ አልጋ ላይ ቢያኖሩት መሬት ይተኛ
- ያህያ ሥጋ ካልጋ ሲሉት ከመሬት ወደለመደው ቦታ

ያህያ ቀበጥ ከጅብ ጡት ይጣባል
- ሰው ሲጠግብ አደጋ ላይ ይወድቃል

ያህያ ባል ከጅብ አያስጥልም
- የፍየል ጅራት ከብርድ አያድን ሐፍረት አይከድን

ያህያ እንግዳ የጅብ ራት ነው
- ከጠላቱ ያልተጠነቀቀ ለጠላቱ ሲሳይ ይሆናል

ያህያ ውኃ ጠጭ ሳይታወቅ መጣጭ
- ዘማዊ ሰው ዘማዊነቱ አንዳንዱ አይታወቅበትም

ያህያ ደግነት ጭነት ማብዛት
- እህያ የተፈጠረችው ለጭነት ነው



ያህያ ጀላፋ መስከ ያጠፋ የሹም ዘፋፋ አገር ያጠፋ
- ያለቃ ልል በጥፊ ያወላውል

ያህያ ፍለጋና የጥሬ ራት በጊዜ ነው
- በጊዜ የሚደረገው ካልተደረገ ጊዜ ካለፈ አደጋ ሊደርስ ይችላል

ያህያ ፍሪዳ የእባብ ለማዳ የለውም
- አህያ ሰባ ካልተበላ ምን ረባ

ያለህ ምዘዝ የሌለህ ፍዘዝ
- ያሰው ይጠጣል የሌለው ያፈጣል

ያለመከራ አይገኝ እንጀራ
- ካልሠራህ የሚበላ የለም

ያስመከራ ጸጋ ያለድካም ዋጋ አይገኝም
- ሰፍተው ደክመው ነው ሀብት የሚገኘው

ያስመጥረቢያ ዕንጨት ለባሪ የቆማጣ ዘንግ ወርዋሪ
- ያለሥራ መሣሪያ ሥራን ማከናወን አይቻልም

ያለምቀኛ አይገኝ ፍቅረኛ
- ምን ቢሆን ምቀኛ አይጠፋም

ያለ ሴት ምን ያደርጋል ቤት
- ሴት ሰቤቷ አሳቢ ናት

ያለ ሴት ቤት ያለ በሬ መሬት
- ሴት ልጅ ሰቤቷ አሳቢ ናት

ያስሥራ መብል ያለዳኛ ውል
- ካልሠሩ ከየት መጥቶ ይበላል ያለዳኛ የተዋዋሉት ውል አይጸናም

ያለሥራ አይበላ እንጀራ ያለባል ቆጥ አይሠራ
- አንድን ነገር ለመሥራት ለዚያ ሥራ አስፈላጊው ነገር ካልተገኘ ያዳግታል

ያለስፍራው የተሰበረ ሊጠግኑት አስቸገረ
- ያለአግባቡ የተሠራን ሥራ ለማረም ለማስተካከል በጣም ያስቸግራል

ያለ በሬ ምን ያደርጋል ገበሬ
- ያለሥራ ማከናወኛ የዚህ ሙያ ባለቤት ነኝ ቢሉት ምን ፋይዳ አለው

ያለበት ይብላላበት
- ባለጉዳዩ ይጨነቅበት

ያለበት ይጉላላበት
- ባስጉዳዩ ይጨነቅበት

ያለባለቤቱ አይነድም እሳቱ
- ችግሩን የሚያውቀው እራሱ ባለቤቱ ነው

ያለአባቱ ቢዛቁን አባክኖ ያባክን
- የማይችሉትን ሥራ ለመሥራት መሞከር ማባከን ይሆናል

ያስአቻ ጋብቻ ቆይ ብቻ ቆይ ብቻ
- ያልተመጣጠነ ጋብቻ ውጤቱ አያምርም

ያለዕዳው ዘመቻ ዋ ብሎ መቅረት
- በማያገባው ገብቶ ትርፉ ጸጸት

ያለ ክንፍ መብረር ያለሥራ መክበር
- ሣይሠሩ ብልጽግናን መመኘት ከፈረሱ በፊት ጋሪውን ማስቀደም

ያለው ሳይዋደድ ለሞተው መናደድ
- በሕይወት ያሉት ሳይዋደዱ ለሞተው ማዘን

ያለውን ካልሰጡ በስም አይበሉ
- አንድን ሥራ በዘዴ ካልሠሩ ይከብዳል

ያለው ይመዛል የሌለው ይፈዛል
- ያለው ይጠጣል የሌለው ያፈጣል

ያለው ይበሳል የሌለው ያፈጣል
- ያለው ሲበላ የሌለው ይቀላውጣል

ያለዘዴ ጋሻ እንቅብ ነው
- ሳላወቀው ፎገራ ዱሩ ነው

ያለዝናብ ነጐዳ ያለብርድ ዕዳ
- ሁኔታው በሌለበት መሻት

ያለ የሚኖር ይመስላል የሞተ ያልነበረ ይመስላል
- ሞት ቢዘገይ የቀረ ይመስላል

ያለ ይበዛል አለ ወፍጮ
- አንድ ነገር ቆይቶ ሊበረክት የሚችልበት ሁኔታ ይኖራል

ያለጊዜው የተወለደ ልጅ አባቱን ጥሎ እያቱን ያሰረጅ
- ያለጊዜ የሚሆን ሁሉ ችግርን ማስከተሉ አይቀርም

ያለጐረቤት ቡና ያለሙያ ዝና
- ያለሙያ ታዋቂነት አይገኝም

ያለጕታ ደረባ ያለልብስ ካባ
- መሠረታዊ ነገር ሳይኖር ሌላ ተጨማሪ ነገር አያገለግልም

ያለጕታ ደረባ ምንድነው?
- ምንም

ያለጥርስ ቆሎ ያለጓዳ እምባጓሮ
- ያለአጋር አንድን ሥራ ለመሥራት ውጤታማ አይኮንም

ያለጨው በርበሬ ያለሞፈር በሬ
- ለሥራ ጠቃሚ መሣሪያዎችን ማሟላት ይኖርብሃል

ያለፈቱ አይቆርስ ያለቤቱ አይወርስ
- ሁሉም ነገር የሚከናወነው እሱ በተገኘበት ብቻ ነው

ያለፍርድ ማሰር በፈጣሪ ማማረር
- ምሬትን ሰቆቃን ለማስገወገድ ፍትሕን ማስፈን

ያለፍቅር ሰላም ያለደመና ዝናብ
- በሰዎች መካከል ፍቅር ካለ ሰላምም ይኖራል

ያለፍቅር ጸሎት ያለ ዕንጨት እሳት
- ለዓምላኩ እምነትና ጽናት የሌለው ቢጸልይ ጸሎቱ የሽኮኮ ጸሎት ይሆንበታል



ያሉሽን በለማሽ ገበያ ባልወጣሽ
- ስለእንቺ የሚወራው ጥሩ አይደለም

ያላረፈች ምላስ ሽማ ትልሰ
- መንቀዥቀዥ ለችግር ይዳርጋል

ያላረፈች እግር ክዘንዶ ጉድጓድ ትገባለች
- መንቀዥቀዥ ለችግር ይዳርጋል

ያላሰብከውን እግኝ
- በጕ ምኞት ወይም ምርቃት

ያላሳደጉት ውሻ ቤት ዘግተው ቢመቱት ዞሮ ይናከሳል
- የእራስ ያልሆነ ልጅ ቢቆጡት ከማጥቃት አይመለስም

ያላወቁ አለቁ
- ያላወቁ ለችግር ተዳረጉ

ያላዋቂ ቆራሽ ማዕድ አበላሽ
- የማያውቁትን እሠራለሁ ማለት ለማበላሸት ነው

ያላዞረ ሲዞር አደረ
- ይሉኝታን የማያውቅ

ያላዩ ልጅ ዳቦ ፍሪዳው
- ለድሃ ሁሉ ነገር ብርቁ ነው

ያላዩት አገር አይናፍቅም
- ያልሰሙት ነገር ክፉም መልካምም አይደለም

ያልሞላ ተርፎ አይፈስም
- በልኩ የሆነ ነገር አይበላሽም

ያልሞተና ያልተኛ ብዙ ይሰማል
- ካልሞትክ ብዙ ጉድ ታያለሀ

ያልሟል ይተረጉሟል
- አንድን ነገር ዐቅዶ በዕቅድ ይሠራል

ያልሰማ ጆሮ ከጐረቤት ያጣላል
- ነገርን በጥሞና ያለማዳመጥ ስሕተት ላይ ይጥላል

ያልሰማ ጥኑ ነው ባልሽ ወዳጁ ነው
- አልሰማሽም እንጂ ጠላትሽ ነበርኩ

ያልሰጡት ተቀባይ ያልጠሩት አቤት ባይ
- ሳይጠሩት አቤት ሳይልኩት ወዴት

ያልሳሉት አይላጭ ያላዩት አይቆጭ
- የማያውቁት አገር አይናፍቅም

ያልቆረጠ እግቡ አይደርሰም
- ካልቆረጠ ታታሪ ካልሆንክ አያልፍልሀም

ያልበሉት ዕዳ ያልጠሩት እንግዳ
- በጣም አስቸጋሪና አስጨናቂ ነው

ያልበላ ሬሳ ያልለበሰ እንስሳ
- ሰው ካልበላ መኖር አይችልም

ያልበላኝን ቢያከኝ አይገባኝ
- በማያገባው ነገር የሚገባ

ያልበሳ ዳኛ አያሚግት ያልጠጣ እንግዳ አይጫወት
- እንግዳን መጋበዝ አለብህ

ያልበጀው እላት ፈጀው
- ሳያዋጣው ጀምሮ ከሰረ

ያልተመታ ልጅ ሲቆጡት ያለቅሳል
- ባለጌ ሥርዓት የሌለው ሞልቃቃ ልጅ

ያልተማረ አይጸድቅ ያልተወቀረ አያደቅ
- በጥሩ ሁኔታ ያልተዘጋጀ የሥራ ማከናወኛ መሣሪያ ውጤት አይሰጥም

ያልተማረ ዋናተኛ ከዳኛ ፊት እንቢተኛ
- ከዳኛ ፊት ቀርቦ እንቢተኛ መሆን ሳልታሰበ እርቅና መቀጫ መዳረግ

ያልተረታ አይረታ ያልጠገበ አይማታ
- ወንድ ልጅ አንድ ቀን እንደአባቱ አንድ ቀን እንደእናቱ

ያልተሾመ አያዝ ያልቀሰለ አያናዝዝ
- ሁሉም የሚመራው በባለሙያና በተፈቀደለት ሰው ብቻ ነው

ያልተቀጣ ልጅ ያልታጠበ እጅ
- በሥነሥርዓት ያላደገ ልጅ ባሕሪው ብልሹ ይሆናል

ያልተነካ ግልግል ያውቃል
- ችግርን ያላየ ነገሮችን አቅልሎ ያያል

ያልተገላበጠ ያራል
- እልፍ ሲሉ እልፍ ይገኛል

ያልተገራ ፈረስ ይጥላል በደንደስ
- ያልተቀጣ ልጅ ያልታጠበ እጅ

ያልተጠናከረ ድንገት ተሰበረ
- በደንብ ያልተሠራ ነገር ጥንካሬ የለውም

ያልተፈተነ ወዳጅ ያልተተኮሰ ሽከላ ነው
- በችግር ጊዜ ያልታየ ወዳጅ አስተማማኝ አይደለም

ያልታረመ አፍ ከዋንጫ ይሰፋል
- ባለጌ ሰው ከአንደበቱ የሚወጣው ሁሉንም ሰው ያስቀይማል

ያልታየ እንጂ ያልተሰማ ያልተደረገ እንጂ ያልተበላ ነገር የለም
- ያልተዳሰሰ ነገር የለም ነገር ግን ዛሬ ጐልቶ አይታይ እንጂ

ያልታደለ በረዶ ከድንጋይ ላይ ያርፋል
- ዕድለቢስ ሰው መጥፎ ነገር ላይ ይደርሳል

ያልታደለች ወፍ ዓይኗ በጥቅምት ይጠፋል
- ዕድለቢስ ሰው በሚበላበት ጊዜ ይሞታል

ያልታደለ ከንፈር ሳይሳም ያረጃል
- ዕድለቢስ ሰው ሳይመቸው ያረጃል

ያልነበረ ያፈርሳል ቀዳዳ ያፈሳል
- ቤተሠሪ በኋላ ይመጣል



ያልወለደ አይነሳ የሽንብራ ማሳ
- ሰው ብዙ ጊዜ ስሙ የሚነሳው በልጁ ነው

ያልወለደ አንጀት ጨካኝ ነው
- ያልወለደ ሰው እንደወለደ አይራራም ጨካኝ ነው

ያልወለደ እጋድሞ አረደ
- ያልወለደ ሰው እንደወለደ አይራራም ጨካኝ ነው

ያልወለዱ ሁሉ ጊደሮች ይባላሉ
- ከማንም ጋር እየዋሉ ያላገቡት ሁሉ ወይዘሪት ይባላሉ

ያልወለዱት ልጅ ያልወቀሩት መጅ
- ያልወለዱት ልጅ እንደራስ ልጅ አይሆንም

ያልወለድኩት ልጅ አባባ ቢለኝ አፌን ዳባ ዳባ አለኝ
- የማይመስል ነገር ለሚስትህ አትንገር

ያልዘሩት አይበቅልም
- የሚወለደው ያው እንደአባቱ እንደእናቱ ነው /የነሱን ባሕሪያት ያንጸባርቃል/

ያልዘራሁት በቀለብኝ ዱባ ያልኩት ቅል ሆነብኝ
- ጥሩ ይሆናል ያልኩት መጥፎ ሆነብኝ

ያልዘራውን የሚበላ ዝንጀሮ ነው
- ሌላ የሠራውን ዘርፎ የሚበላ ሌባ ነው

ያልገደለ በሽታ ምስጋና የለውም
- አንድ ደረጃ ላይ ያላደረሰ ዝምድና ምን ፋይዳ አለው

ያልገደለ ዘማች ያልወለደ እማች
- የተሠማራበትን መለያ ነገር ባለመያዙ አይደነቅም

ያልጋ ሌሰኛ ሦስት ያስተኛ
- የሙት ቀናተኛ ሚስቴን አደራ ይላል

ያልጠረጠረ ተመነጠረ
- ያልጠረጠረ ሰው ጉዳት ይደርስበታል

ያልጠሩት መካሪ ያልሾሙት ፈታውራሪ
- አንድ ሰው ሳይፈልግ ልምከርህ የሚል ሰው አስቸጋሪ ሰው ነው

ያልጠሩት ሠርገኛ በትረኛ
- ሳይፈቅዱት መጥቶ ችግር የሚፈጥር

ያልጫ ድንፋታ እንጀራ እስኪቀርብ ነው
- ለጥጋበኛ ሕግ ፊት እስኪቀርብ ድረስ ነው

ያልፋል እስኪያልፍ ያለፋል
- ችግር እስኪያልፍ መጨነቅ አይቀርም

ያመል ትንሽ ይጥላል በጭራሽ
- መጥፎ ባሕሪ ለአደጋ ያጋልጣል

ያመነታ ተመታ
- መወላወል ለአደጋ ያጋልጣል

ያመኑት ሲከዳ ይቀላል ዕዳ
- የተማመኑበት ወዳጅ አንድ አንዴ ጠላት ይሆናል

ያመኑት ፈረስ ጣለ በደንደስ
- የተማመኑበት ሰው ካደ

ያመጣሁት ውሻ ነከሰኝ ያነደድኩት እሳት ጠበሰኝ
- ያሳደኩት ልጅ ጉዳት አደረሰብኝ

ያመጣል አንበሴ ይበላል ኮሳሴ
- ጉበዝ ያመጣውን ሰነፍ ይበላል

ያምላክ ነገር ሰንቱን አውቀሽው ወይ እኔ አበላው አንቺ አርመሽው
- አንቺ እንዳሰብሽው ላይሆን ይችላል /የዓምላክ ጥበቡ ብዙ ነው/

ያምራል ብለው ሰነብር ልጅ አይድሩም
- የሚያብረቀርቅ ሁሉ ወርቅ አይደለም

ያምራል ብለው ከመናገር ይከፋል ብሎ መተው
- የማይሆን ነገር ከመናገር መቆጠብ ይሻላል

ያምራል ብሎ ይሸልሟል ያውቃል ብሎ ይሾሟል
- ከዕንጨት መርጦ ሰታቦት ከሰው መርጦ ለሹመት

ያምሯል ይታደሏል
- ውበትን የሚሰጥ ዓምላክ ነው

ያምና ሞኝ ዘንድሮም ደገመኝ
- ያለፈው እንደገና ተመልሶ መጣ

ያምናውን ዘንድሮ አዋጁን በጆሮ
- ሁሉ ያወቀውን ምስጢር አደረጉት

ያሞላቀቁት ልጅ አይሆንም ወዳጅ
- ሞልቃቃ ልጅ ሰቤተሰቡ አስቸጋሪ ነው

ያሞሌ ጥጃ በወንዟ ትፋፋ
- አጥፊና ጠፊ

ያረረበት ያማስል
- ጉዳዩ የሚመለከተው ያስብበት

ያረሮ ልጅ ጠላፎ
- የሌባ ልጅ ሌባ

ያረሰ እንደልቡ ጉረሰ
- ጠንክሮ የሠራ እንደልቡ ያገኛል

ያረጀን ሹም ገባር ይከሰዋል ያረጀን ጅብ አህያ ይልሰዋል
- ካረጁ አይበጁ

ያረገዘች ታስታውቅ ከደረቷ ትታጠቅ
- እርግዝና አያደር ይገፋል

ያራስ ክፉ መበስት የአደጋ ክፉ እሳት
- እሳት ብዙ ጊዜ የተደከመበትን ንብረት ያጠፋልና ነው

ያራሷን በርጉዟ
- አንዱን በአንዱ

ያራሷን ገንፎ እርጉዟ ውጣ ሞተች
- ለእራስህ የማይገባህን ነገር ይገባኛል ማለት ለአደጋ ያጋልጣል



ያርጋጅ አንጓጅ
- በኃዘን ላይ ሁና ሌላውን ወደሩቅ ቦታ የምታነጉድ

ያሰረ ይፈታል የሰጠ ይረታል
- ወርቅ የሰጠ የፈለገውን ያደርጋል

ያሰቡት አይገድም ጉኄን ሳርገው ጋደም
- የሚታሰብ አይጠፋም እሰቲ ትንሽ አረፍ ልበል

ያሳደግኋት ጥጃ አሰችኝ በእርግጫ
- ያመኑት ፈረስ ጣለ በደንደስ

ያስለመዱት ሰው ሁልጊዜ እጅ ያያል
- የለመደ ሰው ሁልጊዜ ፋሲካ ይመስለዋል

ያስታርቀኛል ሙተራ እያንዳንዱ እየኮራ
- ያመኑበት ነገር አንዳንድ ጊዜ ችግር ላይ ይጥላል

ያሸላል ያሉት ኩል ዓይን ያጠፋል
- ያመኑት ፈረስ ይጥላል በደንደሰ

ያቀረቡልህን ጉረስ የተረፈህን መልስ
- በሰጡህ አትሰነፍ

ያበረ ወገኑን አስከበረ
- ኅብረት ጥሩ ነገር ነው

ያ በሬ ባላገደደ ያ በሬ ገደል ባልገባ
- ያሰቡት ነገር እንደነበር በቆየ

ያ በሬ ባገደደ ያ በሬ ገደል ገባ
- የማይፈልጉት ሰው ከአጠገብ እንዲርቅ የሚመኙት ምኞት

ያበደ ለኑሮው የፈረደ ለጉሮሮው
- ሰው የሚለፋው ለዕለት ጉርሱ ነው

ያበደች ጋሰሞታ እናቷን ትመታ
- ባጐረስኩ እጄን ተነከስኩ

ያበደና የወደደ አንድ ነው
- ፍቅር የያዘው ሰው ነገሮችን አያገናዝብም

ያበጠው ይፈንዳ
- የሆነው ይሁን

ያባ ሆይ መቋሚያ ላዩ በላ ታቹ ደላ
- ላይ ላዩን ጥሩ ውስጥ ውስጡን መጥፎ ነው

ያባበለሽ ሳያገባሽ ከባልሽ ሆድ አትባባሽ
- ባልተጨበጠ ተስፋ አብሮ ከኖሩት ሰው አትቃቃሪ

ያባቱን ቢሰጡት ሕይወቱ ያባቱን ቢነሱት ሞቱ
- በአባቱ ንብረት የሚመካ

ያባትህ ቤት ሲዘረፍ አብረህ ዝረፍ
- ሳም ሲበዘብዝ ጭራውን ያዝ

ያባትህና የናትህ ወገኖች ሲጣሉ ጥግህን ያዝ
- አታዳላ

ያባት ልጅ የደንደሰ ሥጋ
- ብዙም የማይጠቅም እንደእናት ልጅ የማይሆን

ያባት ልጅና ጆሮ አንድ ነው
- ብዙ ወደ ዋና አካል ያልተጠጋ እንዲያው ላይ ላዩን የሆነ

ያባት ምርቃት አያስገባም ጥቃት
- የአባት ምርቃት ለተሳካ ኑሮ ያመቻቻል

ያባት ሞቱን አይወዱ ረድኤቱን /ረዳቱን/ አይወስዱ
- እቤት የሌሰውና መሪ የሌሰው አገር አንድ ነው

ያባት አገር ከሞት አያስጥልም
- ከሞት የሚያስጥል የለም

ያባት እርግማን ሲዳፉ ማልቀስ
- አባት ልጁን ከልቡ አይረግምም

ያባት ዕዳ ለልጅ ያፍንጫ እድፍ ለእጅ የወፍጮ ዕዳ ለመጅ
- አባት ያጠፋው ለልጁ ይተርፈው

ያባት ወርቅ ባለዝና እህል ለቀጠና
- መቼም እህል ለችግር ጊዜ ነው

ያባት ደግ ይደልላል ያባት ክፉ ለእንጀራ ልጅ ያደላል
- የራሱን ትቶ ለውጪ ሰው የሚያደላ የሚያስገርም ሰው ነው

ያባያ ልጅ ወዳቂ ያራኝ ልጅ አጥባቂ
- ዋሾና ቤተሰቡ በሰው ዘንድ ተቀባይነት የላቸውም

ያባይ ምልክቱ እንደበቱ የገዳይ ምልክቱ ሽልማቱ
- አንድ ሰው በመጥፎም ሆነ በበጐ የሚለይበት ሁኔታ ይኖረዋል

ያባያ እናት አትታረድም
- ልጇ አባያ በመሆኑ አብሎ ያድናት ይሆናል

ያባያን እናት ውኃ ጠማት
- ሞልቶ ተርፎ ተቸገረች

ያባያ እንባ አይታገድም
- ያዞ እንባ ይስጠኝ

ያባያ ውኃ ተለያየ ሲሉት ተገናኘ
- ዞሮ ዞሮ መገናኘት አይቀርም

ያብሮ አደግ ልብ በቁና ይሰፍራል
- ልብ ለልብ ይተዋወቃሉ

ያብዬን እከክ ወደ እምዬ ልከክ
- የራሱን ስሕተት ወደሌላው ማላከክ

ያብዬን ወደ እምዬ
- የራሱን ስሕተት ወደሌላ ሰው ላይ ማላከክ

ያተር ክምር የጭሰኛ ክብር
- ገበሬ በከመረው ክምር ብርቱ ገበሬ በሚል ክብር ይሰጠዋል

ያንበሳ ልመና ጋማ ይዞ ነው
- ኃይለኛን ለማጥቃት በዘዴ ነው



ያንበሳ ልመና ጋማ ይዞ የቂስ ልመና አናዞ
- ኃይለኛን በዘዴና በብልሃት ይቀርቡታል

ያንበሳ እማላጅ ጋማ ይዞ ጅብን መውጋት አህያን ተገን ይዞ
- ኃይለኛን ለማጥቃት በዘዴ ነው

ያንበሳ ኮረዳና የጨዋ ልጅ ሞግዚት ከመሆን ይሰውርህ
- ቀስጥን መጠበቅ በጣም አስቸጋሪ ነው

ያንበሳ ገራም ይውላል ከላም
- በሬ ካራጁ ይውላል

ያንተን የሚመስል የኔም አለኝ ቁስል
- እኔም እንዳንተው ቁስል አለብኝ

ያንካሳ ልቡ እየሩሳሌም ነው
- ልብ እንቅርት ይመኛል

ያንዱ በሬ ሲሞት ላንዱ አጋዘኑ ያንዱ ፍስሐው ላንዱ ኃዘኑ
- የአንድ ኃዘን ለሌላው ፌሽታ ነው

ያንዱ ቤት ሲቃጠል ላንዱ ቋያው ነው
- የአንዱ ችግር ለሌላው ምንም አይደለም

ያንዱ ቤት ሳይጠፋ ያንዱ ቤት አይለማ
- የአንዱ ደስታ ለአንዱ ኃዘን ነው

ያንዱ ነገር ላንዱ የእንጀራ ልጁ ነው
- ለአንድ ቁምነገር የሆነው ለሌላው የማይረባ ተደርጐ ይወሰዳል

ያንዱ አገር መልከኛ ላንድ አገር ገባር ነው
- አንዱ አገር አዛዥ ሌላው አገር ታዛዥ ይሆናል

ያንድ ላም ወተት ያንድ እርሻ እሸት
- ከአንድ ምንጭ የተቀዳ

ያንድ ሚስቱን የሺ ከብቱን
- ማንም የእሱ የሆነውን እንዲነኩበት አይፈልግም

ያንድ ሰው ነገር ሰምተህ አትፍረድ
- አትቸኩል አገናዝብ

ያንድ ሰው ፍቅር ባንድ እጅ እንደማጨብጨብ ያለ ነው
- ፍቅር ተመጣጣኝ ሲሆን ብቻ ነው

ያንድ ቀን ስሕተት የዘላለም ጸጸት
- መጥፎ ስሕተት እስከ ሕይወት ፍፃሜ ድረስ ጸጸት ያሳድራል

ያንድ በሬ እሸት ያንድ ላም ወተት
- ለብዙ ሰው ሲዳረስ አይችልም

ያንድዋ እለት አንድዋ ባልቴት
- እንዷ በሌላዋ ሠርግ እንደባልቴት ትቆጠራለች

ያንጉራጓሪ ጉልበት የተጋጋጭ ወተት
- የምትራገጥ ላም ብዙ ወተት አትሰጥም

ያኖሩት እንቅርት ያገለግላል
- ያስቀመጡት ነገር ለችግር ጊዜ ያገለግላል

ያኩራፌ ምሳው እራቱ ይሆነዋል
- ባልሆነ ነገር የሚያኮርፍ ሰው ችግር ላይ ይወድቃል

ያኮረፈ ልብሱን አራገፈ
- ምኑም ምኑም ይቅርብኝ በሚል ሁኔታ

ያወረደ መዓቱን ያመጣ ምህረቱን
- መዓቱን በምህረቱ ይመልሰልን

ያወቀ ተጠነቀቀ የዘነጋ ተወጋ
- ችላ ያለ ሰው አደጋ ይገጥመዋል

ያወቀ ተጠነቀቀ ያላወቀ ተነጠቀ
- እያያዙን አይተው ጭብጠውን ቀሙት

ያወቀ ናቀ
- ሚስጥርን የሚያውቀ ሰው ይንቃል

ያወቀ ዘለቀ ያላወቀ አለቀ
- ያወቀ ይጠቀማል የማያውቅ ግን ይጐዳል

ያወቁ ሲታጠቁ ያላወቁ ተሣሣቁ
- ያወቀ ሲጠነቀቅ ያላወቀው ተዘናጋ

ያዋቂ ሴት ቤት አለው ውበት
- ቤቷን አሰውባ ነው የምትይዘው

ያዋቂ አጥፊ የእስራኤል ጣፊ
- ያዋቂ አጥፊ ምህረት አይደረግለትም

ያዋጁን በጆሮ የዕለቱን በቀጠሮ
- የተነገረውን በሚስጢር ድብቁን በግልጽ

ያውሬ ሥጋ ለወሬ
- አደን ውያለሁ ለማለት ለዝና

ያው በገሌ አለች ድመት
- ትንሽም ብትሆን ዕድሌ በፈቀደልኝ እጠቀማለሁ

ያዙኝ ልቀቁኝ
- እጉል ፉከራ

ያዛኘ ቤተክርስቲያን ላሚ ያጋፋሪ ራስጌ ቋሚ
- አንዱ ወደአንዱ ሲሔድ ሌላው ቤት ያጠፋል

ያየ ልናገር ቢል የሰማ ላውራ አለ
- ያላረጋገጡት ነገር ያስገምታል

ያየ ቢሔድ የሰማ ይመጣል የወጣ ቢገባ የገባ ይወጣል
- ከሚመለከተው ሰው የማይመለከተው ይብሳል

ያየ ቢሔድ ያልሰማ ይመጣል
- አልሰሜን ግባ በለው

ያየ ይናገራል የተወለደ ይወርሳል
- ተወላጅ ከቤተሰብ ንብረት ተቀራማች ነው

ያዩትን ሢሠሩ ዓይናቸውን ታወሩ
- ያልተረዳኸውን ነገር ማድረግ መሥራት ስጉዳት ይዳርጋል



ያዩትን ቢያጡ ያላዩትን ይቀላውጡ
- ከንቱ ምኞት መመኘት

ያይንን ጨንቋራ ሁሉ ያየዋል
- የልብን ክፋት ግን ያለዓምላክ ማን ያየዋል

ያይዘጌን ቤት ቡች ታውቀዋለች
- የግዴለሽን ቤት ብልጦች ይጐበኙታል

ያይጥ ምስክሯ ድንቢጥ
- አንድ ዓይነት ተመሳሳይ የሆኑ

ያይጥ እርዳታ በጭራንፎ ያልቃል
- ምንም የማይጠቅም ትንሽ የሆነች

ያይጥ ፉከራ ስመከራ ድመት ምን ሊበላ
- ያለአቅም መንጠራራት ስአደጋ ያጋልጣል

ያደለው ጀላ ቀለበት ያሰራል
- የተመቸው ሰው ያለው ሰው የሚያደርገውን ያጣል

ያደረገችውን ታስታውቅ ከደረቷ ትታጠቅ
- ያላትን እንዲያዩላት ፊት ለፊት ማውጣት

ያደሩበት ጭቃ ከጭድ ይሞቃል
- ከማያውቁት መልአክ የሚያውቁት ሰይጣን

ያደፈውን በእንዶድ የጐደለውን በሞረድ
- ያልተስተካከለን ነገር ማስተካከል

ያዳቆነ ሰይጣን ሳያቀስ አይቀርም
- አብሮ የኖረ መጥፎ ባሕሪ እየባሰ መጥቶ ችግር ላይ መጣሉ አይቀርም

ያዳኝ ውሻ ጠጉር ባፉ በትር ትርፉ
- ሮጠ ሮጠ አድኖ ምንም ሳያገኝ መቅረቱ

ያገሩን ሰርዶ ባገሩ በሬ
- ከባለቤቱ ያወቀ ቡዳ ነው

ያገሩን ስርዶ ያገሩ በሬ ይወጣዋል
- ከባለቤቱ ያወቀ ቡዳ ነው

ያገርህን ልጅ ብታገባት ሚስትህ፣ ብትፈታት እህትህ
- ካገርህ ልጅ ጋር ውስጥ ለውስጥ ስለምትተዋወቅ ትተባበራለህ

ያገር ልማት የገበሬ ህብት
- ልማት ሁሉ በገበሬ ትከሻ ላይ ነው

ያገር ልጅ በምን ይመታል በከብት ያም እንዳይሔድ ያም እንዳይሞት
- የአገር ልጅ ከበድ ያለ ቅጣት አይቀጣም

ያገር ልጅ የማር ጠጅ
- የአገር ልጅ አሳቢ ነው

ያገር አድር ለንጉሥ ያስቸግር
- ያገር ደንብ በማንም ሊጣስ አይችልም

ያገባሽ ይፈታሻል ይብላኝ ለወሰደሽ
- አስቸጋሪ ሴት ለቤተሰቦቿ ሸክም ነች

ያገኘ በራሱ ያጣ ከዋሱ
- ያለው በራሱ እምነት ይጣልበታል

ያጓጉት ድንጋይ ተመልሶ ራስን
- ተንጋሎ ቢተፉ ተመልሶ ካፉ

ያጣ ሰው ያገኘ አይመስለውም
- የተራበ ሰው የሚጠግብ አይመስለውም

ያጣጣመ የቆረጠመ
- ጣዕሙ ያለው ከሚቆረጠመው ላይ ነው

ያጥንት ፍላጭ የሥጋ ቁራጭ
- የሥጋ ዘመድ

ያፈን እስክውጥ ዕድሜ ይስጠኝ ይላል እርኩም
- የያዝኩትን አንድ ደረጃ ላይ እስክደርስ ጊዜ ሰጠኝ እንደማለት

ያፍላ አማኝ አደረገኝ ለማኝ
- አዲስ አማኝ ኃይማኖት አጥባቂ ነው

ያፍላ የለው ቀርፋፋ
- የወጣት ቀርፋፋ የለውም

ይህ ሁሉ ከርከሬሻ ባንቺ የተነሳ
- ይ ሁሉ ችግር ሲደርስ የቻለው በአንቺ ጣጣ ነው

ይህ ሁሉ ጠባሳ ባንቺ የተነሳ
- ይሄ ሁሉ ችግር ሲደርስ የቻለው በአንቺ ጣጣ ነው

ይሆች ባቂላ ካደረች አትቆረጠምም
- ስሕተቱ በቶሎ ካልታረመ ከቆየ ችግር ያመጣል

ይሆች ተፍ ተፍ እኔን ለመመንተፍ
- ይኼ ወዲያ ወዲህ አዘናግቶ ዘርፎ ለመሔድ ነው

ይሆን ብስጥ ምን እውጥ
- ለጥቼ እኔ እንዴት እኖራለሁ

ይሆን ፈርቼ ደጀን በቀን ዘግቼ
- ይሄ ታይቶኝ ነው የተጠነቀኩት

ይህ አንበሳ ደም ደም አገሳ
- ለጠብ እየተዘጋጀ ነው

ይህ ከርከሬሻ ዳባዬን ለማንሻ
- ይሄ ሁሉ ጣጣ አንዳች ነገር ለመውሰድ መሆኑ ነው

ይሆናል ብዬ ጉሽ ጠመድኩት የማይሆን ቢሆን ፈትቼ ለደድኩ
- ጥሩ ነው ብዬ የጀመርኩት ሥራ ስላልሆነ ተውኩት

ይሆን ቢሆን ዝሆን ይበላ በሆን
- አይቻልም እንጂ ቢሆን ኖሮ ሥጋው ብርካቱ ነበረው

ይሉሽን በሰማሽ ገበያ ባልወጣሽ
- ወሬውን አልሰማሽ እንጂ ብትሰሚው ኖሮ ሰው ጋር አትደርሽም ነበር

ይሉሽን ብትሰሚ ጉንደር ላይ ክረሚ
- የሚመከረውን የሚሰማ ጥንቃቄ ያደርጋል



ይሉኝታና መጠቀም አንድ ላይ አይገኝም
- ይሉኝታ ከገበያ ጋር አብረው አይሔዱም

ይሉኝታ የራስ አሊን ቤት የፈታ
- ይሉኝታ ከፍተኛ ችግር ውስጥ ይጥላል

ይሉኝ አይል ውሽማ ዶሮ ሲጮህ ይማልላል
- ይሉኝታ የሌለው ሰው ሰዓት ቦታ ጊዜ አይመርጥም

ይሉኝ አይል የኋላውን አያይ
- ይሉኝታ የሌለው ለምንም ለማንም አይጨነቅም

ይሉኝ አይል ጸሐፊ ከሙሴ ይገድፋል
- ይሉኝታ የሌለው ሰው ግልጽ የሆነ ስሕተት ይፈጽማል

ይመስከረዋል ለነፍሱ ይፈተፍተዋል ለከርሱ
- የሚያደርጉትን ሁሉ በትክክልና በእውነት ማድረግ ይገባል

ይመስል አይመስል የጠይብ እጅ ተከሰል
- ቀጥቃጭ /ቢላዋ ማረሻ/ የሚሠራ እጅ አይጸዳም

ይመታሉ የሚጠሉ ይመስል ይሰማሉ የሚወዱ ይመስል
- አይጠሉምም የዚያኑ ያህል አይወዱምም

ይሙት የገደለ ይካስ የበደለ
- ሁሉም እንደሥራው

ይማሩኝ እያልክ ከምትታማበት አትገኝ
- መልሰህ መሳልለህ ከጥፋት ቦታ አትገኝ

ይሰጠኝ መሰሉኝ ሊሸጠኝ
- ግዛኝ ግዛኝ ብለው ሊሸጠኝ አሰበ

ይሰጡኝ ብሎ ከሰጠ ቀጥቦ የበላ በሰጠ
- የበሰጠ አገኛለሁ ብሎ የሰጠ ዞሮ ዞሮ ችግር ላይ ይወድቃል

ይሰጣል መሰሎ ይሸጣል
- የሚሰጥ እየመሰለ የራሱን ጥቅም የሚያሳድድ

ይሰበረኝ ይለንጥረኝ የሚሉ የለውን ልብ ሊሰብሩ
- የውሸት መሃላ መደርደር

ይቅር ለእግዜር ወድቆ አይሰበር ሞቶ አይቀበር
- ከተቀያየሙት ሰው ጋር ይቅር ለእግዚአብሔር መባባል ተገቢ ነው

ይቅደም ደግነት ይከተል ቸርነት
- የተቸገሩን ሰዎች ሰመርዳት ሞክር

ይበላ እንደቤቱ ይሠራ እንደጉልበቱ
- በአቅሙ የሚችለውን ነው የሚሠራው

ይበላ እንደቤቱ ይሠራ እንደጉረቤቱ
- በሥራ ከጓደኛ ማነስ የለበትም

ይበላው ካጣ ይበላበት ያጣ
- ከሌለውና ካጣ ከነጣ ኖሮት አበላሉን ያላወቀው የበሰጠ ይጉዳል

ይበጃል ያሉት መድኀኒት ዓይን አጠፋ
- ያመኑት ፈረስ ይጥላል በደንደስ

ይብራና ይብራ ተጣሉ በሰው ሽንብራ

- እኔም ሌባ አንተም ሌባ ምን ያጣላናል በሰው ገበባ

ይታደሷል እንጂ ይታገሷል

- በአድልህ እንጂ በትግል የምታገኘው ነገር የለም

ይችም አንጀራ ሆና ሚጥሚጣ በዛባት

- ይቺም ኑሮ ሆና ምቀኛ በዛባት

ይወደዋል ካሉ ይመክሯል ይወደዋል ካሉ ይመስሏል

- የወደዱትን ክፉ እንዳያጋጥመው መገሰጽ መልካም ነውይወደዋል ካሉ ይመስሰዋል አይገድምከወደዱ አብሮ መምሰል ያለ ነገር ነውይወዷል ከሆድ ይታጠቧል ከክንድ

- ሰውን ከወደዱ እስከምናምኑይውጋህ ብሎ ይማርህ
- ከበደሉ በኋላ ማባበል ተገቢ አይደለም

ይውጋህ ብሎ ይማርክህ

- ከበደሉ በኋላ ማባበል ተገቢ አይደለም

ይደርሳል ባይ ብዙ አብሳይ

- ለማግኘት መድከም ያለ ነው

ይደንቃል ይገርማል አህያ ከጅብ ጋር ይከርማል

- የማይመሰል ነገር

ይገርመኛል ገንፎ ከራቴ ተርፎ

- የማይመስል ነገር

ይጠላኝ ይመስል ይመታኛል ይወደኝ ይመስል ይመታኛል

- አይጠላምም አይወድምም

ይጥሉሀ አትጥላቸው ይበድሉሀ አትበድላቸው

- ዋጋህን ከፈጣሪህ ታገኛለህ



## መልመጃ 13 /የ/

ሀ. <u>የሚከተሉትን ምሳሌያዊ አነጋገሮች አሟሉ</u>

1. ______ ግማቱ ከጭንቅላቱ
   ሀ. የዓሣ ለ. የዓሣማ ሐ. የጉማሬ መ. የሰው
2. የሚውል ሆድ ______
   ሀ. በማለዳ ይበላል ለ. በማለዳ ይጮሃል
   ሐ. በማለዳ ይርበዋል መ. በማለዳ ይጠግባል
3. ______ በሽማግሌ ይታረቃል
   ሀ. የቤተዘመድ ጠብ ለ. የነገር ጠማማ
   ሐ. የትዳር ጉባጣ መ. የተጣላ ጉረቤት
4. ______ ኢየሩሳሌም
   ሀ. ያንካላ ልቡ ለ. የአማኝ ልቡ
   ሐ. የጸሎተኛ ልብ መ. የኃጢያተኛው ልቡ
5. የሚዜ ፈዛዛ ______
   ሀ. የሰውም ለዛ ለ. ሽቶ አይገዛ
   ሐ. ጥሎሽ አይገዛ መ. አይዘፈንም ለዛ
6. ______ ያፍንጫ ዕዳ ለእጅ
   ሀ. የአባት ዕዳ ለልጅ ለ. የእናት ዕዳ ለልጅ
   ሐ. ያገር ዕዳ ለልጅ መ. የንጉሥ ዘውድ ለልጅ
7. ______ አደባልቀህ ውቃ
   ሀ. የሌባን ዕቃ ለ. የሌባን ጠንቃቃ
   ሐ. የሌባን ጠበቃ መ. የሌባን ጓደኛ
8. የቡና ቀዝቃዛ ______
   ሀ. የሽም ፈዛዛ ለ. የቀን ደንጋዛ
   ሐ. ያልጠራ ጠራ መ. የፉንጋ ፉንጋ
9. ______ መፋጀቱ
   ሀ. የቡና ስባቱ ለ. የቡና ጥቁረቱ
   ሐ. የቡና ጥማቱ መ. የቡና ጣዕሙ
10. የቤት ቀጋ የውጭ ______
    ሀ. አልጋ ለ. ወላንሳ ሐ. በርጩማ መ. ወንበር
11. የሚያልፍ ውኃ ____
    ሀ. ያዋርዳል ለ. አደረገኝ ድሃ
    ሐ. ይረጫል ለንስሐ መ. ገንዘቤን ወሰደው

12. የሴት ዘንገኛ ______ ምቀኛ
ሀ. የጐረቤት ለ. የእናት ሐ. የዘመድ መ. የወዳጅ

13. የሴት ጉልበቷ ______
ሀ. ምላሷ ለ. እጇ ሐ. ባሏ መ. መልሱ የለም

14. የሴት ጠጪ ______ ፈንጪ
ሀ. የአህያ ለ. የእንቦሳ
ሐ. የግመል መ. ሁሉም መልስ ነው

15. የሥንዴ አራራ ______ መራራ
ሀ. የሬት ለ. የሴት ሐ. የስኳር መ. መልሱ የለም

16. የሰድብ ______ የለውም
ሀ. ምርቃት ለ. ቡራ ከረዩ
ሐ. አበጥ መ. ሁሉም መልስ ነው

17. የሥጋ ትል ______ ጥል
ሀ. የከብት ለ. የወዳጅ ሐ. የዘመድ መ. ባዕድ

18. የሥጋዬ ቁራጭ ___
ሀ. የብርሌ ጭላጭ ለ. የእጥንቴ ፍላጭ
ሐ. ሀ እና ለ መልስ ይሆናሉ መ. መልሱ የለም

19. የሸንጐ ዓይን ______ ይሰብራል
ሀ. ጉድን ለ. እጅ
ሐ. ጉልበት መ. ሁሉም መልስ ነው

20. የሹም ሰነፍ ______
ሀ. ያወራ ለ. ይለማመጥ
ሐ. ይለፈልፍ መ. ያሠራል

21. የሺህ አካላት መሰብሰቢያው ______
ሀ. እናት ለ. አቤት
ሐ. እጐረቤት መ. መልሱ የለም

22. የሺህ ፍልጥ ማሰሪያው ______
ሀ. ገመድ ለ. ልጥ
ሐ. ሲባጐ መ. ሁሉም መልስ ነው

23. የሽሮ ድንፋታ ______ እስኪመጣ
ሀ. በርበሬ ለ. እንጀራ ሐ. ዳቦ መ. ቂጣ

24. የቀበረ ______
ሀ. ተንጓገለ ለ. አከበረ ሐ. ተቀበረ መ. ከሐሳብ አረፈ

25. የቀበጡ ዕለት ______
ሀ. ሞት አይገኝም ለ. አይገኝ ሞት
ሐ. ይሰባበሩ መ. ሀ እና ለ መልስ ይሆናሉ



26. የቂል ______ ቂል
ሀ. ጓደኛው ለ. ገንዘብ ሐ. ሀብት መ. ለ እና ሐ

27. የቁጥር መጨረሻ ______
ሀ. ዝም ለ. እልፍ ሐ. ሚሊዮን መ. መልሱ የለም

28. የቀጂ ልጅ ______
ሀ. ጠጭ ለ. አስቀጂ ሐ. አጣጪ መ. መልሱ የለም

29. የቂስ ምንደኛ ______ በትረኛ
ሀ. የሞኝ ለ. የቂል ሐ. የሴት መ. ሀ እና ለ መልስ ይሆናሉ

30 የቂስ ቀማኛ ______ ምቀኛ
ሀ. የጐረቤት ለ. የእናት ሐ. የወዳጅ መ. የዳኛ

31. የቂስ ነጋዴ______
ሀ. ይመስላል ወንበዴ ለ. ይመስላል ቅልስልስ
ሐ. ይመስላል አትራፊ መ. መልሱ የለም

32. የቆቅ አውራ ይውላል ______
ሀ. ጐረቤት ለ. ተራራ ሐ. ጫካ መ. እመንደር

33. የቆረጠ ______
ሀ. ተመነጠረ ለ. አመለጠ ሐ. አስመለጠ መ. ተለማመጠ

34. የበላበትን ______ ሰባሪ
ሀ. እጅ ለ. ወጪት ሐ. ሣህን መ. ምጣድ

35. የቆዳ ጓንታ ______ ሠርጉ ነው
ሀ. ለውሻ ለ. ለጅብ
ሐ. ለአህያ መ. ሀ እና ሐ መልስ ይሆናሉ

36. የበላ ቢያብል ______ ይናገር
ሀ. ፊቱ ለ. ጀርባው ሐ. ገላው መ. ሁሉም መልስ ነው

37. የበላች ብትዘፍን ______ ታዝን
ሀ. ያልበላች ለ. የቀላወጠች ሐ. እያበደች መ. ያበላች

38. የበሬ ቀንዱ ______ ግንዱ
ሀ. የወላጅ ለ. የወይራ ሐ. የግራር መ. የዋንዛ

39. የበሬ ሆዳም ______ አይጐዳም
ሀ. ቢሸለም ለ. ቢሸልሙት ሐ. ቢሞት መ. ቢጠፋ

40. የበላይ ______
ሀ. አካባጅ ለ. አዳባይ ሐ. አዛዥ መ. ተናዛዥ

41. የበሬ ሳቢ ______ አሳቢ
ሀ. የቤት ለ. የጐረቤት ሐ. የልጅ መ. መልሱ የለም

42. የበሬ ዳተኛ ________
ሀ. ተደራርቦ ተኛ  ለ. እመሀል ይተኛ
ሐ. ሮጦ ከተኛ  መ. ይሞታል በዳኛ

43. የበሬ ዕቃ ________ አለቃ
ሀ. የባለቤቱ ለ. እየራሱ ሐ. የአህያ መ. መልሱ የለም

44. የበሰበሰ _____ አይፈራም
ሀ. ባለቤቱን ለ. አለቃን ሐ. ዝናብ መ. ጀግና

45. የቡና ቀዝቃዛ ______
ሀ. የሹም ፈዛዛ  ለ. የልጅ ፈዛዛ
ሐ. የዐዋቂ ፈዛዛ  መ. መልሱ የለም

46. የባለጌ ባለሟል _____ ያያል
ሀ. ሀብት  ለ. ገንዘብ
ሐ. ቂጥ ገልቦ  መ. ሀ እና ለ መልስ ይሆናሉ

47. የባለ አለ _______ አትፍታ
ሀ. ጥጃሀን  ለ. ፍየልሀን
ሐ. ሚስትሀን  መ. ሀ እና ለ መልስ ይሆናሉ

48. የባዕድ ፍቅር _______ አንድ ነው
ሀ. የውኃ ጌጥ ለ. የከብት ሐ. የነገር መ. የሰው ጌጥ

49. የቤቴ መቃጠል ______ በጀኝ
ሀ. ለልመና  ለ. ለትኋኑ
ሐ. ለእርዳታ  መ. ሀ እና ሐ መልስ ይሆናሉ

ለ. <u>ለሚከተሉት ምሳሌያዊ አነጋገሮች ፍቺ ምረጡላቸው</u>

1. የወደቀ ዛፍ ምሳር ይበዛበታል
ሀ. አንበሳ ሲያረጅ የዝንብ መጫወቻ ይሆናል
ለ. ለተሾመ ይሟገቱለታል ለተሻረ ይመለከሩበታል
ሐ. እግዜር የጣለውን እናት አታነሳውም
መ. ሀ እና ለ መልስ ይሆናሉ

2. የእንቶሎ ቶሎ ቤት ግድግዳው ለንበሌጥ
ሀ. አለባብሰው ቢያርሱ በአረም ይመለሱ
ለ. የቸኮለ አፍሶ ለቀመ
ሐ. የጅብ ችኩል ቀንድ ይነከሳል
መ. ሁሉም መልስ ነው

3. የምበላው ሳጣ ልጄ ጥርስ አወጣ
ሀ. ዓባይ ማደሪያ የለው ግንድ ይዞ ይዞራል
ለ. የላጭን ልጅ ቅማል በላው
ሐ. ራስ ሳይጠና ጉተና
መ. ሀ እና ለ መልስ ይሆናሉ



4. የአብዬን እከክ ወደእምዬ ልከክ
ሀ. የራሷን አበሳ በሰው ላይ አብሳ
ለ. ያለዋዛ ዋዛ ቅቤም አያወዛ
ሐ. ለሃምሣ ጋን አንድ አሉሉ
መ. መልስ የለውም

5. የወረወርኩት እንካሴ ተመልሶ በራሴ
ሀ. ተንጋለው ቢተፉ ተመልሶ ባፉ
ለ. ድንጋይ ቢያጉኑት ተመልሶ ባናት
ሐ. ሀ እና ለ መልስ ይሆናሉ
መ. መልሱ የለም

6. የቸገረው እርጉዝ ያገባል
ሀ. የተቸገረ ዱቄት ከንፋስ ይጠጋል
ለ. አተርፍ ባይ አጉዳይ
ሐ. በእንቅርት ላይ ጆሮ ደግፍ
መ. መልሱ የለም

7. ያሰደግሁት ውሻ ነከሰኝ
ሀ. ለፍቅር ብተኛት ለጠብ አረገዘች
ለ. ባጉረስኩኝ እጄን ተነከስኩኝ
ሐ. እጸድቅ ብዬ ባዝላት ተንጠልጥላ ቀረች
መ. ሁሉም መልስ ነው

8. የቆጡን አወርድ ብላ የብብቷን ጣለች
ሀ. በገዛ ራሱ እባብ ጠመጠመ
ለ. አተርፍ ባይ አጉዳይ
ሐ. ዓሣ ጉርጓሪ ዘንዶ ያወጣል የሰው ፈላጊ የራሱን ያጣል
መ. ሁሉም መልስ ነው

9. የሞተ አይከሰስ የፈሰሰ አይታፈስ
ሀ. ላለፈ ክረምት ቤት አይሠራም
ለ. ላለፈ አይጸጸቱም ለሚመጣው አይበለጡም
ሐ. ከሞተ ወዲያ ማልቀስ ድንጋይ ማቀፍ
መ. ሁሉም መልስ ነው

10. ያላሰበ ተመነደበ
ሀ. ያልጠረጠረ ተመነደበ
ለ. ፍየል ከመድረሷ ቅጠል መበጠሷ
ሐ. ከቆረሰ የጉረሰ
መ. መልሱ የለም

ሐ. <u>የሚከተሉትን ምሳሌያዊ አነጋገሮች አዛምዱ</u>

| | |
|---|---|
| 1.ያባይን ልጅ ውኃ ጠማት | ሀ. ተንጋለው ቢተፉ ተመልሶ ባፉ |
| 2.የታጠቀ ሳለ ያልታጠቀ ያማርራል | ለ. የቸኮለች አፍሳ ለቀመች |
| 3.ያልተገላበጠ ያራል | ሐ. ለሃምሳ ጋን አንድ አሎሎ |
| 4.የሆድ ምቀኛ አፍ ነው | መ. ካለመናገር ደጃዝማችነት ይቀራል |
| 5. የጠሉት ይወርሳል የፈሩት ይደርሳል | ሠ. በሬ ሆይ ሣሩን አየህና ገደሉን ሳታይ |
| 6. ያብዱን እከክ ወደ እምዬ ልክክ | ረ. የላጭን ልጅ ቅማል በላት |
| 7. የሺ ፍልጥ ማበሪያው ልጥ | ሰ. ፍየል በልታ በበግ አበሰች |
| 8. ያገሩን ሰርዶ ባገሩ በሬ | ሸ. በሰው ቁስል ዕንጨት ስደድበት |
| 9. የጅብ ችኩል ቀንድ ይነክሳል | ቀ. የቤት ቀጋ የውጭ አልጋ |
| 10. ያልጠረጠረ ተመነጠረ | በ. ጅብ የማያውቁት አገር ሔዶ ቁርበት አንጥፉልኝ ይላል |
| 11. የራሷ ጊዜ አለቀሰች የሰው ጊዜ ሣቀች | ተ. ያሳሰበ ተመነደበ |
| 12. የፈሰሰ ውኃ አይታፈስም | ቸ. ያለባለቤቱ አይነድም እሳቱ |
| 13. የግፍ ግፍ በእንቅርት ላይ ጆሮ ደግፍ | ኀ. ሰው በመልካም ሥራው ይወደዳል |
| 14. ያይጥ እንግዳ ከሰልቻ ውስጥ ጉዝጉዙልኝ አለች | ነ. ብርሌ ከነቃ አይሆንም ዕቃ |
| 15. ይገርማል እህያና ጅብ አብሮ ይከርማል | ኘ. ነገርን አዳምጦ እህልን አላምጦ |
| 16. የተከፋ ተደፋ | አ. ማን ያውቃል አገር ምን ይጠብቃል ማገር |
| 17. የሰው አገሩ ምግባሩ | ከ. በሬ ካራጁ ይውላል |
| 18. የነገር ወጡ ማዳመጡ | ኸ. ተናዳጅ እንጂ አናዳጅ አይሞትም |
| 19. የምትኮነን ነፍስ ጉረቤት ያውቃል | ወ. በቡሃ ላይ ቆረቆር |
| 20. የተነቃነቀ ጥርስ ሳይወልቅ | ዘ. ዲያቆን ከዘፈነ ፍየል አያርፍም ከቀዘነ አይድንም |



## ደ

ደህና ሲታጣ ይመለመላል ጉባጣ
- ተፈላጊው ነገር ሲታጣ ባለው ነገር መጠቀም ይገባል

ደህና ወገን ያጣ ወየው ያለበት ጣጣ
- ለክፉ ጊዜ የሆነህ ዘመድ ከሌለህ በጣም ትቸገራለህ

ደህና ጦር ያለው ለግንብ ይሞክረው
- ጥንካሬውን ሰማየት በግንቡ ላይ ይየው

ደመና ለዝናብ ድግስ ለሆዳም
- ሆዳም ድግስ አይቶ አይመለስም

ደመና በሰማይ የጨዋ ልጅ ባደባባይ
- የጨዋን ልጅ ሁሉም ሰው ያከብረዋል

ደመናን የጨበጠ ሰማይን የቧጠጠ የለም
- ሊሆን የማይችል ነገር ተስፋ መጠበቅ አይገባም

ደም ቢያለቅሱ ድንጋይ ቢነክሱ
- የፈለገ ነገር ቢመጣም የማይሆን ነገር ነው

ደም ተቃብቶ ዝንብ አይፈሩም
- ደፍረው የገቡበት ነገር ምንም አያስፈራም

ደም ተበክለህ ዝንብን አትጥላ
- አንዴ ከገባህበት በኋላ የመጣው ቢመጣ ማፈግፈግ የለብህም

ደም ከውኃ ይቀጥናል
- ሰው ለዘመዱ ይቆረቆራል

ደም ካልፈሰሰ ስርየት የለም
- ክብት ካልታረደ ዕርቅ የለም

ደሞዙ ሥንዴ ሥራው የምን ግዴ
- የሚከፈለው ደሞዝና ሥራው አይመጣጠኑም

ደሞዝተኛ አርፈህ አትተኛ
- ሥራ ሠርቶ ማግኘት ይገባል

ደሞዝ ያጣ ሎሌ ይኮበልላል በሐምሌ
- ሰው ከሠራ ማግኘት አለበት ካላገኘ ደግሞ ይከዳል

ደረስሁ ልጅ ፈላሁ ጠጅ
- ለአቅመ አዳም ደርሻለሁ

ደረቅ ይቀመጠላል እርጥብ ይጉብጣል
- አያያዙ ካላማረ ወዳልተጠበቀ ሁኔታ ያመራል

ደረቴን ቢያመኝ እግሬን አገመኝ
- የሚሆን እያለ የማይሆን ነገር ማድረግ

ደረጃ ለፍቶ መሔጃ
- በሥልጣን ከፍ ከፍ ሲሉ ፎቶ አንሺ አይጠፋም

ደስታ በሽታ
- ከመጠን ያለፈ ደስታ ያልሆነ ነገር ለመፈጸም ይገፋፋል

ደስታና መከራ ቀኝና ግራተፈራራቂ ናቸው
ደባል ሲሰነብቱ ይሆናል ባስቤት
- አንድ ሰው ራሱጋ አንድ ዕቃ ብዙ ጊዜ ከተቀመጠ የራሱ ይመስለዋል

ደባ ራሱን ስለት ድጉሱን
- ተንኮል ሠሪውን ያጠፋዋል

ደባልና ሹመት ያሰለበብ አይሔድ
- ያለምክንያት ሰው ከሥልጣን አይወርድም

ደብር ለላስታ ድግድግታ ለጌታ
- ጌታ ፊት ሲቀርቡ ማደግደግ አክብሮት ማሳየት የግድ ነው

ደብተራ ሲኮራ እቤተክርስቲያን ገብቶ ጭራ ይይዛል
- ያስቦታውና ያስሙያ መኮፈስ

ደብተራና ተማሪ ስልፍና ሱሪ
- በሰልፍ ላይ ለሰልፍ የሚሆን ትጥቅ ይዞ መገኘት ተገቢ ነው

ደብተራ የዘኬ ጕተራ ዘኬውን ሲቋጥር አነቀው ነብር
- ደብተራ ከደጀሰላም የማይጠፋ ስለመሆኑ

ደንቆሮ ከሚያጫውትሽ የሚሰማ ያውጋኝ
- ከማይም ይልቅ ጥቂት ዕውቀት ካለው ጋር ቢወያዩ መግባባት ይቻላል

ደንቆሮ የሰማ ዕለት ያብዳል
- ስለሰው ስለራሱም ወሬ የማይከታተል ሰው መጥፎ ነገር የሰማ ዕለት በጣም ይበሳጫል

ደወል ለአንበሳ ባማረሰት ታዲያ ማን ይስርሰት
- ምን ዕውቀት ቢኖር ክፍ ያለ ሰው ዘንድ ማን ያደርስዋል

ደወል እንደ ጠዋቱ ትጮኻለች
- አሁንም ቅድምም ሁኔታዎች አንድ መምሰላቸው

ደጃቸውን ሳይዘጉ ሰውን ሌባ ይላሱ
- በራቸውን ከፍተው ሰውን ሌባ ይላሱ

ደጃፉን ጥሎ በጓሮ ይመጣል
- ትክክለኛውን መንገድ ሳይሆን ያልሆነውን መንገድ ይዞ ይጓዛል

ደገኛ ሲያርስ ቆለኛ ያነፍስ
- የእርሻው ወቅት ለየቅል ወይም በተሰያየ ጊዜ በመሆኑ

ደጉ ነገር ሳያልቅ ክፉ መናገር
- ጥሩው ነገር ሳያልቅ መጥፎ መናገር አይገባም

ደግ ሰው ከእንጀራው ቆርሶ ከወጡ አጥቅሶ
- ደግ ሰው ለደግነቱ ወደር አይገኝለትም

ደግ ሳይበላ ክፉ ይመራ
- ሰው በበላው መጠን እንጂ ከዚያ በላይ እንዲሠራ አይጠበቅም

ደግና ማለፊያ ትግልና ልፊያ
- ደግና ማለፊያ ነገር እንዲሁ በከንቱ አይገኝ



ደግ አባት እርስት ያቆያል ክፉ አባት ዕዳ ያቆያል
- ደግ አባት ለልጁ ቅርስ ለማቆየት ተግቶ ለፍቶ ይሠራል

ደግ ጌታ ሲለግስ እንደፏፏቴ ያርስ
- ለስጋስ ጌታ የሚያርስ ገበሬ ሲያርስ አይለግምም

ደግ ጕረቤት ዕቃ አያስገዛም
- ሁሌ ዕቃ የሚያውስ ጕረቤት ጕረቤቱን ያዘናጋል

ደግ ጕረቤት ውሻና ድመት ያሳድጋል
- ውሻ ከውጪ ድመት ከቤት ጠላትን ይከላከላሉ

ደግ ጕረቤት ያወጣል ከመዓት
- ደግ ጕረቤት ፈጥኖ በችግር ጊዜ ይደርሳል

ደፋር ሴት ጉልቻ ረግጣ ትወጣለች
- የማታገናዝብ ሴት በጥጋቧ የሞቀ ቤቷን አቀዝቅዛ ትሔዳለች

ደፋርና ጭስ መውጫ አያጣም
- ጕበዝ ሰው ከችግር በዘዴ በመላ ይወጣል

ደፋር ወጥ ያውቃል
- ያለ የሌለውን ወጡ ውስጥ በመጨመር ያጣፍጣል /ሳይሰስት/

ዱላ ለባለጌ ምርኩዝ ለአሮጌ
- አቅመ ደካማን መንከባከብ ባለጌ መቀጣት አለበት

ዱላ የሚጠላው ሸክላ ብቻ ነው
- ቅጣትን የሚጠላ የለም ለሁሉም ቅጣት ይበጃል

ዱላ ይዞ ሌባን መጠየቅ
- ሌባ ከተያዘ በኋላ በዱላ ልቡን ማጥፋት ነው

ዱቄት በአመድ ይሥቃል
- አንዱ በአንዱ ሲሥቅ ጀምበር ጥልቅ

ዱባ ባገሩ ጋን ያህላል አሉ
- ለማንኛውም ቢሆን ኩራት በአገር ነው

ዱባና ቅል አበቃቀሉ አንድ ይመስላል አበላሉ ለየቅሉ
- አዬ ሌላ ወዬ ሌላ

ዱባና ቅል አበቃቀሉ እየቅል
- አስተዳደጋቸውና ባሕሪያቸው የተለያዩ ናቸው

ዱባና ቅል አብሮ ይበቅል አበላሉ እየቅል
- ቢመሳሰሉም የተለያዩ ነገሮች ናቸው

ዲያቆን ሲጠግብ በጧፍ ይማታል ወይፈን ሲቦርቅ ድንበር ያፈርሳል
- ጥጋብ ተገቢ ያልሆነ ድርጊት እንድትፈጽም ይገፋፋሃል

ዲያቆን ከዘፈነ ፍየል ከቀዘነ
- ጥሩ ሰው ሲበላሽ ቅራሪ የለውም

ዳሩ ምን ይሆናል ሆነና ሆነና
- አንዴ ሆኗል ምን ይደረጋል

ዳሩ ሲፈታ መሃሉ ዳር ይሆናል
- መካከሉ የተጠናከረ እንዲሆን ዳሩ የተከበረ መሆን አለበት

ዳር ዳር ያለ በመሃል የከበረ
- ክብረት ሀብት ያገኘ ዳር ዳር ይላል እንጂ ደፋር ደፋር ብሎ አይጋጭም

ዳቦ ሲበሉ ልብ ልቡን ዳገት ሲወጡ ጥግ ጥጉን
- ለሥራ ጊዜ መሸሽ ለምግብ ጊዜ መቻኮል መንገብገብ ጥሩ አይደለም

ዳቦ በገና ቡና በጀበና
- ሁሉም በየጊዜውና በአስፈላጊው የሥራ መሣሪያ ሲከወን ያስደስታል

ዳቦ ካልበሉት ድንጋይ ሎሚ ካልመጠጡት እንቧይ
- ሁሉንም ነገር በየጊዜው ካልተጠቀሙበት አላስፈላጊ ነው

ዳቦውን ጉርሶ ደሙን አብሶ
- የፈሰሰውን ደም የሚያስረሳ ወይም የሚተካ ካሣ አግኝቶ

ዳቦ ያስቅርፋት ጠላ ያለምርጊት
- በምርጊት ያልቆየ ጠላ ይነፍሰበትና ጣዕሙ መልካም አይሆንም

ዳተኛ በሬ ሀብታም ነው
- አባያ በሬ በመሆኑ በሥራ ጊዜ ለሽ ብሎ ይተኛል

ዳኛ ሁን እንደኛ
- ከሕዝብ ጋር መመሳሰል ያስፈልጋል

ዳኛ ለዳኛ ያወርሳል ጉም ተራራ ያለብሳል
- አንድ ነገር ለሚቀጥለው ሰው ወይም ባለሙያ ይሸጋገራል

ዳኛ ምን ያደላ ከተረታው ሲበላ
- ሰው ለጥቅም ሲል አድሎ መሥራት ያዘወትራል

ዳኛ ሲመረምር ከራስ ይዞ እስከ እግር
- ሕግ የያዘው ነገር በትክክል ይመረመራል

ዳኛ ሲቆጣ ማር ይዞ ከደጁ
- ከባለቀትር እትቀታተር

ዳኛ ሲያዳላ በዳኛ እህያ ሲያጋድል በመጫኛ
- ትክክለኛ ፍርድ ከሌለ ለበላይ ማመልከት ይገባል

ዳኛ ሲገኝ ተናገር ውኃ ሲጠራ ተሻገር
- ዳኛ ሲኖር ተናገር ውኃ ሲጐድል ተሻገር

ዳኛ ስበር በእጅ ከበር
- ሠርተህ ለፍተህ ጥረህ ግረህ ሀብት ለማግኘት ሞክር

ዳኛ ቢንቁ ከመከራ ይወድቁ
- ዳኛ መናቅ ከችግር ላይ ይጥላል

ዳኛ ቢንቁ የተያዘ እህል ይወቁ
- ንቀት ተገቢ ነገር አይደለም

ዳኛ ቢያጐድል በዳኛ
- ለዳኛም ዳኛ አለው

ዳኛና በሬ ሀብታም ነው
- በሬ እርሶ አምርቶ ባለቤቱን ሀብታም ያደርገዋል

ዳኛ እውጥቼ ዘንግ እቅንቼ
- በዳኛ ፊት ከባለጋራዬ ጋር ተከራክሬ



ዳኛ አያነቅፉ እሳት አይታቀፉ
- አንድን ነገር በአግባቡ እንጂ ከአግባብ ውጪ መያዝ አደጋ ያስከትላል

ዳኛ ካዳላ ጭንቱ ቀላል
- ዳኛ ካዳላ በሰውም በእግዚአብሔርም ፊት ይቀላል

ዳኛ የወል ምሰሶ የመካከል
- ዳኛ ለከሳሽም ለተከሳሽም የጋራ ነው

ዳኛ የፈረደበት መርከብ የተሰበረበት
- ዙሪያው ገደል የሆነበት

ዳኛ የፈረደው ስለት የቀደደው
- ዳኛ የፈረደው ያለቀለት ጉዳይ ነው

ዳኛ ያደላበት እሳት የበላበት
- ተመልሰው ሊያስተካክሉት የማይቻል አስቸጋሪ ነገር

ዳኛ ያፈሰሉለት ፈረስ የከለከሉላት
- ለጪ የሰጠውን ዳኛ ይቀበላል

ዳኛ ይመረምራል ጣዝማ ይለረስራል
- ቢያጥቡት ይነጣል ቢመረምሩት ይወጣል

ዳኛ ገንዘቡን ተቀማ
- ያባይን ልጅ ውኃ ጠማው

ዳኛ ፍርድ አይከላ እህል ጐታ አይሞላ
- አንድ ሰው ለፍቶ አምርቶ ጐታ ካልሞላ ከንቱ ድካም

ዳኞች ከመረመሩ ይናገራል ምድሩ ይገኛል ነገሩ
- ዳኛ ነገርን መርምሮ የሐቁን ይፈርዳል

ዳከዬ ከውኃው ፈረስን ከገለባው
- እነዚህ ሲገናኙ ያስደስቷቸዋል

ዳዊትን ያህል መዝሙር ጨለማን ያህል ጥቁር
- አይገኝም አይኖርም

ዳገት እርሙ ሜዳ ወንድሙ
- የሚከብድን ሥራ እየሸሸ ቀለል ያለውን ይሠራል

ዳገት ለወዳጁ አይሰንፍ ሀብታም ካለወዳጅ አይተርፍ
- ሁሉም ወዳጁን ያጠብቃል

ድሃ ሲቀልጥ አመድ አመድ ይሸታል
- ወዝ የሚገኘው ከሚመገቡት ነው

ድሃ ሲቀመጥ እጁን ይዘህ አወዛውዘው
- በእጁ የያዛትን ትንሿን እንዲያራግፍልህ

ድሃ ሲቀማጠል ከወገቡ ቅምጥል
- እጉል ቅንጦት ለከፋ ችግር ይዳርጋል

ድሃ ሲቆጣ እግሩ ይፈናጠራል
- ድሃ ሲከፋው የተሻለ ይሆናል ወደሚለው እግሩን አንስቶ ይሔዳል

ድሃ ሲቆጣ ከንፈሩ ያብጣል መንገዱን ያስልጣል
- ድሃ ችግር ሲደርስበት ወደሌላው መንገዱን ይቀይሳል

ድሃ ሲናገር ሬት ኮሶ ሀብታም ሲናገር የማር በሶ
- ያለው ማማሩ

ድሃ ሲንቀባረር ያለቀለ ይመስላል
- የማታውቅበትን የሰው ጃኖ ለብሳ ተመለሺ ቢሏት ወዴት ተመልሳ

ድሃ ሲያገኝ ያጣ አይመስለውም
- ምኝ የፊቱን ብልህ ያመቱን

ድሃ ቅቤ ወዶ ማን ሲሸከም ነዶ
- ድሃ ጌትነት ከፈለገ ሥራውን ማን ይሥራ

ድሃ በሕልሙ ቅቤ ባይጠጣ ኖሮ እከክ ይወርሰው ነበር
- በእውን የማይገኘውን ምኞች በሕልም

ድሃ በጉልበቱ ባለጸጋ በሀብቱ
- ሀብታም በገንዘቡ ደሃ በጉልበቱ

ድሃ ቢናገር አያደምቅ ቢጨብጥ አያጠብቅ
- ለው አክብሮት ያለው ላለው እንጂ ለድሃው አይደለም

ድሃ ባይ ዐይኔን አመመኝ
- አጉል መመጻደቅ

ድሃ ተበድሎ ማሩኝ ይላል ቶሎ
- ባለመሬት በበደለ ጭሰኛ ይከሳል

ድሃ ተበድሎ ራሱ ይታረቃል ሀብታም በድሎ መልሶ ይሥቃል
- መሔጃ ማኩረፊያ ስለሌለው ድሃ ተበድሎ ራሱ ይታረቃል

ድሃና አመቤት እልፍኝና ማድቤት
- ሁሉም እንደደረጃው

ድሃና ጌታ ተሚግቶ ቅልና ድንጋይ ተማቶ የማይሆን ነው ከቶ
- አይጥ ለሞቷ የድመት አፍንጫ ታሸታለች

ድሃን ምን ትሠራለህ እንጂ ምን ትበላለህ የሚለው የለም
- የድሃን ጉልበት የማይመኝ የለም

ድሃን ቢያስለቅሱ ከሥላሴ ይወቅሱ መንግሥተ ሰማያት አይወርሱ
- ለድሃ ማዘን መመጽወት ትሩፋትን ያስገኛል

ድሃ ከርሻ ዳቦዬን ለማንሻ
- ሀብታም እርሻውን የሚያሳርሰው በድሃ ነው

ድሃ ከንቡ ይዳራ
- ድሃ ከመሰሉ ጋር ይፋቀራል

ድሃ ካለቀሰ ቀኑ መች አነሰ
- ድሃ ሲከፋው ሌሊትና ቀን ያለቅሳል

ድሃ ካልጣረ ዶሮ ካልጫረ ማን ያበላው ነበረ
- ድሃ ጥሮ ግሮ ካልሠራ ማንም አያበላውም

ድሃ ውኃውን ጠጥቶ እሳቱን ይሞቃል ሀብታም ስለገንዘቡ ይጨነቃል
- የድሃ ነገር ኑሮ ካሉት መቃብርም ይሞቃል

ድሃ የሚበላው እንጂ የሚከፍለው አያጣም
- ድሃ ለሆዱ ይሰስታል ግብር ክፈል ሲሉት ከየትም አምጥቶ ይከፍላል



ድሃ ያልፍልኛል ይላል ጌታ ቀኑን ይቆጥራል
- ድሃ የሚኖረው በተስፋ ነው

ድሃ ያመልክት ዳኛ ያሟግት
- የዳኛ ተግባር ከሳሽና ተከሳሽን ማሟገት ነው

ድሃን ፈርቼ ደጄን በቀን ዘግቼ
- ሁኔታው የሚያዛልቅ አይሆንም

ድሀነት ካምላክ መስማማት
- በምድር የተቸገሩ በላይኛው ቤት የተሻለ ሕይወት ያገኛሉ

ድል በመታደል ሙያ በመጋደል
- የአንድ ሙያ ባለቤት ለመሆን ከፍተኛ ጥረትን ይጠይቃል

ድል ዕድል በአንድ ድልድል
- ድል ወይም አሸናፊነት አንዳንዴ የሚገኘው በአጋጣሚ ነው

ድል የባለ ዕድል
- አሸናፊነት በለስ ሲቀና ነው

ድመት መንኩሳ ዓመሏን አትረሳ
- ዓመለኛ ሰው ዓመሉን አይተውም

ድመት በታች ከሆነች ውሻን ታሸንፋለች
- ለድል የያዙት ቦታ ወሳኝነት አለው

ድመትና ቁንጫ ባዶ ቤት ይወዳል
- ባዶ ቦታ ድምጽ ያስተጋባል

ድመትና አይጥ እሳትና ጭድ
- አይስማሙ

ድመትን በቆሎ መጠርጠር
- የማይሆንና የማይታመን ነገር

ድመትን አይጥ ገደለቻት ወይ ጥቃት ወይ ጥቃት
- ጉልበተኛውን አቅመቢስ ጉዳው ሲባል ለጆሮም ይከብዳል

ድምቢጥ እንደአቅሟ በብር ትታገማለች
- ሁሉም እንዳቅሙና እንደሁኔታው ራሱን ይንከባከባል

ድምጽና ቁንጫ ባዶ ቤት ይወዳል
- ባዶ ቦታ ድምጽ ያስተጋባል

ድራቶ ከነቅማሉ መጥፎ ሰው ከነዓመሉ ወዲያ በሉ
- የማይሆንን ሰው አለማስጠጋት ነው

ድሪያ የዝሙት ዋንጫ
- የዘፈን ዳርዳሩ እስከስታ ነው

ድር ቢያብር አንበሳ ያስር
- ካንድ ብርቱ ሁለት መድኃኒቱ

ድርብርብ እንደደጋ ንብ
- በቦታና በሁኔታ ልዩ ባሕርይን ማመልከት

ድርና ማግ ለሐጭና ልጋግ
- የሚቀራረቡና አብረው የሚኖሩ

ድርጕ ራቱ ድርጕ ቢቀር ሞቱ
- የሰው እጅ ማየት የለመደ ምንጊዜም ያንን ዓመሉን አይተውም

ድርጕ የለመደች መበለት ወተት ያየች ድመት
- ለለመዱት ነገር መንሰፍሰፍ

ድርጭት ፈንጠር ምዝግዝግ ጕንደር
- የእያንዳንዱ ባሕርይና አካሔድ መለየቱ

ድሮ ካያታችን ካጤ ነው ትውልዳችን
- የንጉስ ሐረግ ዘር አለን ለማለት

ድበላ አንዳንድ ጊዜ ይበላ
- የማከማቸቱ ነገር ሁልጊዜ አይሟላም

ድንቁርና ከልብህ መካከል ተራራ ያህል
- ያለዐዋቂ ሰው ያለማወቁን አይረዳም

ድንቢጥ እንዳቅሟ በብዕር ትታገም
- ሁሉም እንደጊዜውና እንደአቅም ይወሰናል

ድንኳን ገልጦ ዙፋን ረግጦ
- ከአቅሙና ከችሎታው በላይ መዳፈር

ድንኳን ገልጦ ዙፋን ረግጦ
- ባለእቅምና ችሎታ ታማኝነትን መግለጥ

ድንገተኛ ስሕተት የቁልቁለት ውድቀት
- በድንገት የሚፈጠር ስሕተት ኃይለኛ አደጋ ያስከትላል

ድንጋይ ለረገጠ ፍለጋ የለውም ውኃ ለጠጣ ሽታ የለውም
- ድንጋይ የረገጠ ሰው ዱካው ሊገኝ ወይም ሊታይ አይችልም

ድንጋይ ላይ ተቀማጭ የባለጌ ተለጣጭ
- ያለአቅምና ያለችሎታ መንጠራራት

ድንጋይ ሲያረጅ መጭ ያበቅላል
- ሰው ሲያረጅ ባሕሪው ይበላሻል

ድንጋይ በድንጋይ ላይ ትልቅ ቤት ይሆናል
- በጥበብ ከያዙት ግዑዙ ነገር የሚያስከብር ሊሆን ይችላል

ድንጋይ ወርዶ እዘብጥ ያርፋል ያገኘው ይተርፋል
- ከሥልጣን ሲወርዱ ያው መገኛው ታች ነው

ድንጋይ ወደሰማይ ቢወረወር ተመልሶ ወደ ምድር
- እሞራ ውሎዋ ሰማይ አዳሯ ምድር

ድግርና ገባር ሲተካከል ያምር
- ሁሉ ነገር ሲስተካከል ሥርዓት ሲይዝ ያስደስታል

ድግስ የሌለው ዋዜማ ምልክት የሌለው ዜማ
- አንድ ነገር መነሻ ያስፈልገዋል

ድጥ ማንሸራተቱን ባለጌ ማሽሟጠጡን አይተውም
- ሰው ማማቱን አይተውም

ዶማ ለመማሻ ማረሻ ለመፌለሻ
- ሁሉም እንደየሥራ ባሕርዩ ሥራ ላይ ይውላል



ዶሮ ሳትበላጡ ታፈስ
- ልምድ አይተውም

ዶሮ ልጆቿን ይዛ ጓሮ ለጓሮ
- ከጠላት መሸሸግ አስፈላጊ ነው

ዶሮ ሲሉ ሰምታ ሞተች ከጢስ ገብታ
- ሰው ያደረገው አይቅርብኝ የሚል ሰው እችግር ላይ ይወድቃል

ዶሮ በልቶ ከብሳና ጕመን በልቶ በጤና
- ጥሩ ነገር በልቶ ከመታመም የሚስማማን መመገብ

ዶሮ በልጇ አንጀት ትጫወታለች
- ልጇ እየራባት ቀምታ ትበላለች

ዶሮ በማለሮ ገደል ለዝንጀሮ
- ለሁሉም ነገር ተስማሚ ዕቃ ተሠርቶለታል

ዶሮ በጋን
- ያልተመጣጠነ ነገር

ዶሮ ቢጠፋ ከቤቱ መነኮሰች እናቱ
- ከልክ በላይ ማቀማጠል ተገቢ አይደለም

ዶሮ ብትታመም በግ አረዱላት
- ለትንሽ ጉዳይ ከፍተኛ ገንዘብ ማውጣት

ዶሮና ቀበሮ ተገናኝተው ጓሮ
- ፈላጊና ተፈላጊ ሲገናኝ

ዶሮን ሲደልሏት በመጫኛ ጣሏት
- ሆድ ሲያውቅ ዶሮ ማታ

ዶሮን ቢያማት በሬ ተሳሱላት
- ለጥቂት ነገር ብዙ ወጪ ማድረግ

ዶሮ አንዱን እንቁላል በወለደችበት ወታቦ ትሞላለች
- አንድ ቦታ ከለመደች ያለዚያ ቦታ አትወልድም

ዶሮ እኔ ባልበላው ጭሬ አላፈስም ወይ አለች
- እኔ ከሞትኩ ሰርዶ አይብቀል አለች አህያ

ዶሮ ከቆጥ በሬ ከጋጥ
- ሁሉም ሠርቶ የሚያርፍበት ምቹ ቦታ ሊኖረው ይገባል

ዶሮ ከቤት ውላ ዝናብ ይመታታል
- ተጠንቅቀው ውለው በትንሽ ስሕተት ችግር ላይ ይወድቃሉ

ዶሮ ከጋጥ አህያ ከቆጥ
- የተገላቢጦሽ የማይስመሰል ነገር

ዶሮ ከጮኸ ሌሊት ከደብረታቦር ወዲያ ክረምት የለም
- ከደብረታቦር በዓል በኋላ ክረምት የለም

ዶሮ ከጮኸ የለም ሌሊት ከቡሄ ወዲያ የለም ክረምት
- ትክክለኛ ነገር

ዶሮ ካልበሏት አሞራ ናት
- ዳቦ ካልበሉት ድንጋይ ሎሚ ካልመጠጡት እንቧይ

ዶሮ ጭራ ማረጃዋን አወጣች

- የቀበጡ ዕለት ሞት አይገኝም

ዶሮ ጭራ የምታወጣው ሚስጥር

- የምትደብቀውን ነገር ማራቅ

ዶሮ ጭራ ጭራ አወጣች ማረጃዋን ካራ

- በማያገባህ ጉዳይ መግባት ችግር ላይ ይጥላል

ዶክተሮች ሲበዙ በሽተኛው ይሞታል

- ሴት ሲበዛ ጉመን ጠነዛ



## መልመጃ 14 /ደ/

ሀ. **የሚከተሉትን ምሳሌያዊ አነጋገሮች አሟሉ**

1. ዳኛ ይመረምራል ________
   ሀ. ጣዝማ ይሰረስራል  ለ. ጣዝማ ይፈውሳል
   ሐ. ፍርድ ያስተካክላል  መ. ምስክር ይመሰክራል
2. ________ ማሩኝ ይላል
   ሀ. ድሃ ተበድሎ  ለ. ጻድቅ
   ሐ. እግዜርን በድሎ  መ. ወታደር በድሎ
3. ደሞዝ ያጣ ሎሌ ________ በሐምሌ
   ሀ. ቀጠሮ ይይዛል  ለ. ይኮበልላል
   ሐ. ይከሳል ሰዳኛ  መ. መልሱ የለም
4. ደሞዝተኛ ________ አትተኛ
   ሀ. አርፊህ ለ. እንቅልፍ ሐ. ቀን መ. ሁሉም መልስ ነው
5. ደመና የጨበጠ ________ የጧጠጠ የሰም
   ሀ. እንበሳን ለ. ሴትን ሐ. ነብርን መ. ሰማይን
6. ደም ቢያለቅሱ ______ቢነከሱ
   ሀ. ልጅን ለ. ጥርስን ሐ. ድንጋይ መ. ጠጠር
7. ደም ካልፈሰሰ ______ የለም
   ሀ. ነፃነት ለ. ጦርነት ሐ. ስርየት መ. መልሱ የለም
8. ደም ተበክሰህ ______ አትጥላ
   ሀ. ወዳጅህን ለ. ሌባን ሐ. ቆሻሻን መ. ዝንብ
9. ደም ______ ይቀጥናል
   ሀ. ከውኃ ለ. ከዘይት ሐ. ከቤንዚን መ. ሁሉም መልስ ነው
10. ደረቴን ቢያመኝ ________ አገመኝ
    ሀ. ቁርጭምጭሚቴን  ለ. እግሬን
    ሐ. እጄን  መ. ሁሉም መልስ ነው
11. ድሃ ______ ይዳራ
    ሀ. ከሚስቱ  ለ. ከጋሰሞታ
    ሐ. ከንቡ  መ. ሀ እና ለ መልስ ይሆናሉ
12. ድሃ ያመልክት ________ ያሟግት
    ሀ. ጉረቤት  ለ. ዳኛ
    ሐ. ሽማግሌ  መ. ሁሉም መልስ ነው
13. ድንጋይ ላይ ተቀማጭ ________ ተሰጣጭ
    ሀ. የባለጌ ለ. የሀብታም ሐ. የድሃ መ. የስነፍ